ኃይል ይሆንላታል:: ሰዎችም በፀሐይዋ ግለት በተቃጠሉ ጊዜ ንስሃ ከመግባት ይልቅ እግዚአብሔርን ሊሳደቡ ይጀምራሉ፤ እሱንም ፈጽሞ አያከብሩትም:: 5ኛው መልአክ ፅዋውን በአውሬው ዙፋን ላይ ሲያፈስ፣ የአውሬው መንግሥት ጨለማ ይውጠዋል፤ ሰዎች ከስቃይ የተነሣ ምላሳቸውን ያኝካሉ፤ በዚህ ምክንያት እንደ ገና የሰማይን አምላክን ይራገማሉ፤ ሆኖም ንስሃ አይገቡም:: 6ኛው መልአክ ፅዋውን በታላቁ የኤፍራጥስ ወንዝ ላይ በሚያፈስ ጊዜ ከምሥራቅ ለሚመጡ ነገሥታት መንገድ እንዲሆን ወንዙ በራሱ ጊዜ ይደርቃል:: በዚያን ጊዜ ከዘንዶውና ከሐሰተኛው ነብይ አፍ፣ ጓጉንቸሮች የመሰሉ ሦስት እርኩሳን መናፍስቶች ይወጣሉ፤ እነሱም ልዩ ታምራት የሚያደርጉ የአጋንንት መናፍስቶች ናቸው:: እነዚህም ሦስት መናፍስት፣ ሁሉን በሚችል አምላክ ቀን ለሚሆነው ታላቅ ጦርነት ሰዎችን ለመሰብሰብ ወደ መላው ዓለም ነገሥታት ይሄዳሉ:: መናፍስቱም ነገሥታቱን ሰብስበው በዕብራይስጥ «አርማጌዶን» የሚባል ስፍራ ያስከትቷቸዋል::

7ኛው መልአክ ጽዋውን በአየር ላይ ሲያፈስ፣ በቤተ መቅደሱ ካለው ዙፋን «ተፈጸመ» የሚል ታላቅ ድምፅ ይወጣል:: መብረቅ፣ ድምፅ፣ ነጎድጓድና ታላቅ የምድር መናወጥም ይሆናል፤ እንዲህ ዓይነት ነገር ዓለም ከተፈጠረች ጀምሮ ፍጹም ሆኖ አያውቅም:: ታላቂቱ ከተማም ለሦስት ትከፈላለች፤ ከተሞች ሁሉ ይደመሰሳሉ፤ እግዚአብሔርም ታላቂቱን ባቢሎን ያስታውሳታል፤ ብርቱ ቁጣው የተቀላቀለበትን የወይን ጠጅ ጽዋ እንድትጠጣም ያደርጋታል:: እንዲህም ሲያደርግ ደሴቶች ሁሉ ይጠፋሉ፣ ተራሮችም ቀድሞ ከነበሩበት አይገኙም:: ቀጥሎም እያንዳንዱ በሚዛን ሲመዘን አርባ ኪሎ ግራም የሚሆን በረዶ ከሰማይ፣ በሰዎች ላይ ይወርዳል፤ መቅሰፍቱም እጅግ አሰቃቂ ስለሚሆን ሰዎች ከበረዶው መቅሰፍት የተነሣ አምላክን ይራገማሉ::

እንግዲህ ይህ ሁሉ የሚሆነው፣ በታላቁ መከራ ዘመን ነው!





ምዕራፍ ፳

# አውሬዎቹ

ከዚያም «ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ ሆነው የሚሞቱ ብጹአን ናቸው፤ ብለህ ጻፍ፤ የሚል ድምፅ ከሰማይ ሰማሁ:: መንፈስም «አዎ ሥራቸው ስለሚከተላቸው ከድካማቸው ያርፋሉ» ይላል::

በታላቁ መከራ ጊዜ በምድር ላይ ልዩ፣ ልዩ ስቃይና አበሳ የሚሆን ሲሆን፣ በእግዚአብሔርና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው የሚገኙ ሰዎች ቁጥር አነስተኛ ነው፤ እነሱም በጭንቅ የሚገኙና በእምነታቸው ምክንያት የሚደርስባቸውን ጽኑ መከራ በመቀበል ሰማዕት መሆን የተገባቸው ናቸው:: የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚጠብቁና ኢየሱስን በማመን የሚጸኑ ቅዱሳን ትዕግሥትም የሚታየው ያን በመሰለ መከራ ውስጥ ጸንተው ያለፉ እንደሆነ ብቻ ነው:: በእርግጥ በወቅቱ፣ በኢየሱስ አምነው የሚሞቱ ሰዎች ዕድለኞች ናቸው፤ ምክንያቱም ከድካማቸውም እንዲያርፉ ሥራቸው ይከተላቸዋልና ነው::[132]

የእነዚያን የመከራ ወራት አሰቃቂ ኹነቶች የሚያመለክቱት ነገሮች ማለትም፣ የሰባቱ ማኅተሞች መከፈት፣ የሰባቱ መለከቶች መነፋትና የሰባቱ የእግዚአብሔር የቁጣ ጽዋዎች መፍሰስ፣ የሚሆኑበት ጊዜ፣ በአንድ ሰዓት ይሁን፣ ወይም በየተራ፣ እርግጠኛ ለመሆን የሚቻል አይመስለኝም:: ነገር ግን በእነዚያ ጊዜአት ሐሰተኛው ክርስቶስና ሐሰተኛው ነብይ በምድር ላይ ሁነኛ ተዋንያን እንደሚሆኑ አያጠ ራጥርም:: ይኼ ሁሉ መከራ የሚሆነው በእነሱ ዘመን ነው::

[132]ራእ14:13::

## ከባሕር የሚወጣው አውሬ

133

> አንድ አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፤ አስር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፤ በቀንዶቹም ላይ አስር ዘውዶች ነበሩ፤ በራሶቹም ላይ የስድብ ስሞች ነበሩት፡

ከዚህ ምዕራፍ በፊት በነበሩት የዚህ መጽሐፉ ክፍሎች በዋናነት፣ በሴቲቱ/እስራኤል እና በዘንዶው/ሰይጣን መኻል፣ በመጨረሻው ዘመን የሚሆነውን ፍልሚያ በስፋት ተመልክተናል። በዚሁ መሠረት ሴቲቱ የወለደችው ልጅ፣ ወደ ዙፋኑ ተነጥቆ ከእጁ እንዳመለጠው ባወቀ ጊዜ፣ ዘንዶው በታላቅ ቁጣ ሴቲቱን ማሳደድ እንደሚጀምር፣ ሆኖም ለሴቲቱ ከሚደረግላት ጥበቃ የተነሣ የፈለገውን ማድረግ እንዳልቻለ ሲያውቅ ከሴቲቱ ዘር ተርፈው የእግዚአብሔር ትዕዛዛት የሚጠብቁና ለኢየሱስ በታማኝነት የሚመሰክሩትን ሊዋጋ እንደሚሄድ አይተናል። ቀጥሎም ዘንዶውና መላእክቱ፣ በሚካኤልና በመላእክቱ ተሸንፈው፣ ከአየር ወደ ምድር ከተጣሉ በኋላ በምድር ታላቅ መከራ እንደሚሆን ተገንዝበናል።[134] እንግዲህ ከዚህ ሁሉ ትዕይንት በኋላ ነው፣ ዘንዶው በባሕር አሸዋ ላይ ቆሞ የሚታየው።

ይህ በዚህ እንዳለ፣ አንድ አውሬ ከባሕር ሲወጣ ይታያል፤ አውሬው የወጣበት ባሕርም በዳንኤል ትንቢት ላይ በተደጋጋሚ የተጠቀሰውና «ታላቁ ባሕር» በመባል የሚታወቀው የሜድትራሊያን ባሕር ሳይሆን እንደማይቀር ይታመናል። ዘንዶው በባሕር አሸዋ ላይ ቆሞ መታየቱ ከዚያ ባሕር አካባቢ ለዘመናት የሚጠባበቀው አንዳች ነገር እንደ ነበረው የሚገልጥ ይመስላል። ከባሕር የወጣው አውሬም፣ አስር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ያሉት ሆኖ፣ በቀንዶቹ ላይ አስር ዘውዶች የነበሩት ነው።

[133] ራእ13፡1።
[134] እነዚህ ታሪኮች በምዕራፍ 12 እና በምዕራፍ 13 መጀመሪያ የሚገኙ ናቸው።





አስገራሚው ነገር፣ ዮሐንስ ይህን ራእይ ከማየቱ ስድስት መቶ ዓመት በፊት፣ ነብዩ ዳንኤል ተመሳሳይ ራእይ አይቶ የነበረ መሆኑ ነው። በዚያው ክፍል ዳንኤል፣ አራቱ የሰማይ ነፋሳት በታላቁ ባሕር ሲጋጩ ሳለ፣ አራት ታላላቅ አራዊቶች ከባሕር ውስጥ ሲወጡ ተመልክቶ የነበረ ሲሆን፣ አንደኛዋ ከሌላኛዋ ፍጹም ልዩ እንደነበረች ተናግሯል፤[135] ዮሐንስ ግን ከባሕር ሲወጣ የተመለከተው አንድ አውሬ ብቻ ነው። ሁለቱን ትንቢቶች እያነጻጸርን ስናጠና ደግሞ፣ በዳንኤል ትንቢት ተጠቅሰው ከነበሩት አራት የአሕዛብ መንግሥታት ሦስቱ እንዳለፉና፣ በዮሐንስ ዘመን አንዱ ብቻ እንደቀረ እንገነዘባለን።

አውሬው ከባሕር መውጣቱ፣ እንዲሁም በሚወጣበት ጊዜ ባሕሩ መናወጡ፣ የመጨረሻው ዘመን መሪ ከሕዝብ መኻል እንደሚወጣና በወቅቱም ኃይለኛ የሕዝብ መናወጥ እንደሚኖር ለማመልከት ታስቦ የተሰጠ ገለጣ ሳይሆን እንደማይቀር ተመልክተናል። ዳንኤል ስለዚህ አውሬ ምንነት በተናገረ ጊዜ እርሱ አራተኛው የአሕዛብ ታላቅ መንግሥት እንደ ሆነ ሲያመለክት፣ በተጨማሪም የሚያስደነግጥ፣ የሚያስፈራ፣ እጅግ የበረታና ታላላቅ የብረት ጥርሶች ያሉት እንደ ሆነ ገልጦታል። አውሬው ያገኘውን ሁሉ እንደሚበላና እንደሚያደቅ የቀረውንም በእግሩ እንደሚረጋግጥ ዓይነት ከመሆኑም ሌላ ከእርሱ በፊት ከነበሩት አውሬዎች እጅግ እንደሚለይ አስታውቆ ነበር።

መቼም ብዙ ሰዎች «አውሬ» ሲባል በአእምሮአቸው የሚሳለው፣ የሆነ ቀንድ ያበቀለ፣ ጅራታም ወይም ከሰው የተለየ ተፈጥሮ ያለው ፍጡር ነው። ከዚህ አንጻር ይህ፣ በዮሐንስና በዳንኤል መጽሐፍ በተደጋጋሚ «አውሬ» ተብሎ የተጠቀሰው ፍጡር ማንነትና ምንነት፣ ከብዙ ሰዎች አሳብ ፈጽሞ የተለየ ሆኖ ይታያል። ሆኖም ከዚህ በፊት በምድር ያለፉትን መንግሥታት በትኩረት ያየን እንደ ሆነ አውሬ የተባሉት በአገዛዝ ባሕርያቸው እንጂ፣ በአካላዊ መልክና ቅርጻቸው እንዳልሆነ በሚገባ እንረዳለን። በተለይም የዚህን የመጨረሻውን

[135] ዳን7፡3፤4። አራቱ የሰማይ ነፋሳት ታላቁን ባሕር ሲያናውጡት ሌሊት በራእይ አየሁ፤ እርስ በርሳቸው የማይመሳሰሉ አራት ታላላቅ አራዊት ከባሕሩ ወጡ።

አውሬ መልክ ልብ ብለን ስንመለከት፣ ከዚህ በፊት በምድር ያለፉ ታላላቅ መንግሥታትን ከፉ ባህርይ አንድ ሳይቀር አሟልቶ እንደያዘ እናስተውላለን።

በዚሁ መሠረት ዮሐንስ፣ የአውሬው ፊት «የነብር» እንደሚመስል ይነግረናል። በዳንኤል መጽሐፍ ላይ እንደታየው ደግሞ፣ ነብር የግሪክ መንግሥት ምሳሌ ነበር። አውሬው ፊቱ የነብር መምሰሉ፣ ባሕርይው፣ ከሌሎቹ ሁሉ ይልቅ የግሪክ መንግሥትን የሚመስል እንደሚሆን ይጠቁማል። ነብር ከሌሎች አውሬዎች ከሚለይባቸው መሠረታዊ ጠባዮቹ መኻል፣ ቁጡነቱ፣ ፈጣንነቱ፣ ጉልበቱና ብልሃቱ በዋናነት የሚጠቀስ ነው። ወደፊትም በሜድትራሊያን ባሕር አካባቢ የሚነሣው ታላቁ የዓለም መሪ፣ በዚህ በግሪካውያን የቆየ የማንነት ባሕርይ የሚገለጥ እንደሚሆን ይጠበቃል። እርሱም ቁጡ፣ ኃይለኛ፣ ጦረኛ፣ ብልህና በአእምሮ ጥበብ የተካነ ሆኖ ነው የሚመጣው። ይኼም ነገሩ የሰዎችን አእምሮ ለመቆጣጠር የሚያስችለው ይሆናል።

በሌላም በኩል ይህ የመጨረሻው ዘመን መንግሥትና ንጉሥ መገለጫ የሆነው አውሬ፣ እግሮቹ እንደ «ድብ እግሮች» እንደሚመስሉ ተነግሯል። በዳንኤል መጽሐፍ ላይ እንደታየው ድቡ የፋርስና የሜዶን መንግሥት ምሳሌ ነው። ድብ፣ በሰሜን አውሮፓና በኢስያ በኃይለኝነታቸውና በጉልበታቸው ከሚታወቁ እንስሳት አንዱ እንደ መሆኑ፣ የመጨረሻው ዘመን መንግሥት፣ እግሮቹ በዚህ መልክ መገለጣቸው፣ በረገጠው ስፍራ ሁሉ፣ ኃይሉና ጉልበቱን ምን ያህል ታላቅ እንደሚሆን የሚገልጥ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። በዚያ ላይ የፋርስና የሜዶን መንግሥት ተለይቶ የሚታወቅበት ባለጠግነት እና በርካታ ሠራዊት እንደሚኖረው ይገመታል። ይኼም የመጨረሻው ዘመን መንግሥት፣ በባለጠግነቱና በሠራዊቱ ብዛት ሁሉን ማድረግ እንደሚችል የሚያስብ መሆኑን የሚገልጥ ይመስላል።

ዳንኤል በተመለከተው ራእይ፣ አንበሳ የባቢሎን መንግሥት ምሳሌ ሆኖ የታየ ቢሆንም፣ ዮሐንስ ግን የአውሬው አፍ ብቻ «እንደ አንበሳ አፍ» እንደሚመስል ነው የገለጠው። በዚሁ መሠረት የመጨረሻው ዘመን የዓለም መንግሥት የተወሰኑ ባሕርያት፣ ከባቢሎን መንግሥት





ባሕርይ ጋር የተለየ መመሳሰል እንዳላቸው እንረዳለን። አንበሳ፣ የአራዊቶች ሁሉ ንጉሥ ሲሆን፣ ንግሥናውን የተጎናጸፈው ደግሞ በተፈጥሮው ካገኘው ከፍተኛ ጉልበትና ኃይል የተነሣ ነው። የአንበሳ ሌላው መታወቂያ ኩራቱ፣ ማን አለብኝነቱና ትዕቢተኛነቱ ነው፤ በአንበሳ ድምፅ ውስጥ ታላቅ ሞገስና አስፈሪ ግርማ ስላለ፣ ሊመታው ያሰበውን መንጋ በድምፁ ብቻ በማሸበር መበታተንን ተክኖበታል። ልክ እንዲሁ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር እጅግ ጉልበተኛ ብቻ ሳይሆን፣ አንባገነን እንደነበር ይታወቃል። በመጨረሻው ዘመን የዓለም መሪ ሆኖ የሚገለጠው ሰው ከሚታይበት ከፉ ባሕርያት አንዱ ኩራቱና ትዕቢቱ ነው። ራሱን ከአምላክ ጋር በማስተካከል ቅዱሳኑን ይሳደባል፣ ያስፈራራል። ለጥቂት ጊዜአትም ሁሉን ማድረግ የሚችል መስሎ ይታያል። ሲናገር፣ በዘንዶው መንፈስ ይናገራል፤ ንግግሩ ቃልና ድምፅ ብቻ ሳይሆን የክፉው መንፈስ ያለበት ስለሚሆን፣ በምድር የሚኖሩትን ሁሉ እጅግ ያሸብራል።

አውሬው አስር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት። እንደ ዳንኤልና ዮሐንስ ትንቢት፣ ራሶችና ቀንዶች የሚያመለክቱት ነገሥታትንና ግዛትን ነው። በዚሁ መሠረት በአውሬው ላይ የሚታዩት አስር ቀንዶች፣ በመጨረሻው ዘመን ከሚነሣው የዓለም አንባገነን መሪ ጋር አብረው የሚነግሡ አስር መንግሥታትን የሚጠቁሙ ናቸው። ምንም እንኳ እነዚህ መንግሥታት፣ ራሳቸውን የቻሉ አስር መንግሥታት ቢሆኑም፣ ጊዜው ሲደርስ ግን በኮንፌደሬሽን አንድ መሆናቸው የማይቀር ነው። በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ተርጓሚዎች ዘንድ እንደሚታመነው፣ መንግሥታቱ የመጨረሻው ዘመን ዓለም አቀፍ ኅብረት አካላት ሲሆኑ ብዛታቸውም ከአስር አይበልጥም፣ አያንስም። ሆኖም ሮም ዳግመኛ በአዲስ መልክ እስክትገለጥ ድረስ፣ ወደ እውነተኛ መልኳ ገና እንዳልደረሰች መረዳት ያሻል።

«ዘንዶው» የተባለው ዲያቢሎስ፣ ከባሕር ለወጣው አውሬ የራሱን ኃይልና ዙፋን፣ ትልቅም ሥልጣን እንደሚሰጠው ተገልጧል። ይኼም በመጨረሻው ዘመን የሚነሣው መንግሥት ሙሉ ለሙሉ የሚሠራው በዲያቢሎስ ኃይልና ሥልጣን መሆኑን የሚገልጥ ነው። ይሁን እንጂ

ከአውሬው ራሶቹ አንዱ፣ ለሞት የሚያደርስ ቁስል እንደነበረው ሆኖ ይታያል፤ ነገር ግን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ለሞት የሚያደርሰው ቁስሉ ይድናል:: በዚያን ጊዜም ዓለም ሁሉ በመደነቅ አውሬውን ይከተላል:: ለአውሬው ሥልጣን በመስጠቱ፣ ሰዎች ሁሉ ዘንዶውን በፍርሀት ያከብሩታል:: «አውሬውን የሚመስል ማን ነው? ከእርሱስ ጋር ማን ሲዋጋ ይችላል?» እያሉም በግለጥ ይሰግዱለታል::

በእርግጥ ስለዚህም ጉዳይም ቢሆን አንዳንድ ግምታዊ አስተያየቶች መሰንዘራቸው አልቀረም፤ ይሁን እንጂ በአውሬው ላይ እንደሚሆን የተተነበየው ይህ ትዕይንት እምብዛም ግልጥ አይደለም:: ያም ሆኖ ግን፣ አውሬው በሚገለጥበት ሰዓት ዓለምን የሚያስደንቅበት አንዳች ታምራዊ ትርኢት ይኖረዋል ተብሎ እንዲጠበቅ ሆኗል:: ታዲያ በወቅቱ ይህን የሚመለከቱ የዓለም ሕዝቦች አውሬውን ሁሉን እንደሚችል አምላክ ስለሚቆጥሩት እርሱን ከልባቸው እያመለኩ ይሰግዱለታል:: የዚህ ሁሉ ትርኢት ዓላማም ይኼው ብቻ ነው::[136]

ከዚህ ቀጥሎ ዘንዶው፣ ከባሕር ለሚወጣው አውሬ፣ የትዕቢትና የስድብ ቃል የሚናገርበትን አፍ ጨምሮ፣ ለአርባ ሁለት ወራት እንዲሠራ ሥልጣን ይሰጠዋል:: አውሬውም እግዚአብሔርን፣ ስሙን፣ ማደሪያውንና በሰማይ የሚኖሩትን መሳደብ ይጀምራል:: ቅዱሳንን ተዋግቶ ድል እንዲነሣቸውም ይፈቀድለታል:: በነገድ፣ በወገን፣ በቋንቋና በሕዝብ ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኖረዋል:: ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ስማቸው በታረደው በግ የሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፈ፣ በምድር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ለአውሬው ይሰግዳሉ::

[136] ራእ13:4::





## ዘንዶውና አውሬው

በመጨረሻው ዘመን ከሚሆኑ አስገራሚ ክስተቶች አንዱ፣ በዘንዶው እንዲሁም ከባሕርና ከምድር በሚወጡት አውሬዎች መኻል ያለው ፍጹም ኅብረትና አንድነት ነው:: የእነዚህ ሦስት አካላት ማለትም የሰይጣን፣ የሐተኛው ክርስቶስና የሐሰተኛው ነብይ ፍላጎትም ለዓለም ራሳቸውን በ«ሥላሴነት» ወይም በ«ሦስትነት» መግለጥ እንደሆነ ጥርት ብሎ ይታያል:: ይኼም ነገር ብዙ ሰዎችን የሚያስት ነው:: ዲያቢሎስ ወይም ሰይጣን እግዚአብሔር አብን፣ ሐሰተኛው ክርስቶስ ደግሞ እግዚአብሔር ወልድን፣ ሐሰተኛው ነብይም መንፈስ ቅዱስን ለመምሰል የሚሞክሩባቸው እነዚያ ወራት እንዴት አስጨናቂ ናቸው?

ከዚህ በተጨማሪ በዚያ ዘመን ዘንዶው፣ ከባሕር ለሚወጣው አውሬ ሙሉ ለሙሉ ሥልጣኑንና ኃይሉን የሚሰጠው በመሆኑ፣ ሰውየው፣ ከዚህ በፊት በምድር ላይ ከተነሡ ሰዎች ሁሉ ይልቅ፣ እጅግ የተለየ እንደሚሆን የሚያከራክር አይሆንም:: ሰይጣን ይኼን የሚያደርገው ደግሞ፣ እርሱ በምድር ላይ በራሱ ተፈጥሮና አካል ለመንቀሳቀስ ስለ ማይፈቀድለት ወይም ስለማይችል ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ልብ ብለን ያየን እንደሆነ፣ በየትኛውም ዘመን በምድር ለመገለጥ የሚፈልግ የትኛውም አካል፣ በምድር ላይ ለመኖር ሕጋዊነት ያለው የሌላ ፍጡር አካል እንዲጠቀም ሲገደድ እናያለን:: ይህም ፈጣሪ በምድር እንዲሆን የደነገገው የፍጥረቱ ሥርዓት ጽኑና የማይፋለስ እንደሆነ ያሳያል:: እውነት ለመናገር እግዚአብሔር ራሱ እንኳ በዚህ ድንቅ የፍጥረት ሥርዓቱ ጣልቃ ሲገባ አልታየም:: ሌላው ቀርቶ ክርስቶስን ለዓለም በላከ ጊዜ እንኳ ሥርዓቱን አላፋለሰም::

ከዚህ አንጻር ሰይጣን፣ ከሰውና ከዚህ ዓለም ጋር የነበረው የዘመናት የግንኙነት መስመር ሲመረመር፣ ሰውን ጨምሮ በምድር ለመኖር ሕጋዊነት ያላቸው የተለያዩ አካላትን በመዋስ ሲሠራ ኖረ እንጂ፣ በየትኛውም ዘመን በራሱ አካል ሊሠራ የቻለበት ጊዜ እንደሌለ እንገነዘባለን:: ይኼም ሥርዓት ጥንት ሔዋንን ካሳተበት ጊዜ አንሥቶ

እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ የሚዘልቅ ነው የሚሆነው:: በዚህ ምክንያት ሰይጣን፣ በመጨረሻው ዘመን የዓለም መሪ እንደሚሆን በሚጠበቀው ሰው አካል በኩል ዓለምን ከመግዛት ውጪ፣ ሌላ አማራጭ እንደሌለው እንረዳለን:: ያም ሆኖ፣ በሚመጣው ዘመን ከዚህ በፊት ካደረገው የተለየ ነገር ለማድረግ የሚያስብ ይመስላል:: ይኼውም ክርስቶስ በምድር፣ ፍጹም ሰው፣ ፍጹም አምላክ ሆኖ እንደኖረ፣ ሰይጣንም፣ በሐሰተኛው ክርስቶስ ውስጥ በመሆን፣ ፍጹም ሰው፣ ፍጹም አምላክ መስሎ ለመታየት የሚሞክርበት ተግባሩ ነው::

ሰይጣን ክርስቶስን ሊመስል ወይም ሊፎካከር በሚያስብበት በዚያ ዘመን ደግሞ፣ ቆስሎ በሚፈወሰው ራሱ ላይ የሚሆነውን ታምር እንደ ዋነኛ ማስታወቂያ ሊጠቀምበት እንደሚችል ይገመታል:: እርግጥ ነው፣ በየትኛውም ዘመን በነበሩ የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎች ዘንድ፣ ጉዳዩን በተመለከተ አንድ ዓይነት መረዳትና ትርጉም ኖሮ አያውቅም:: ይኼም በትንቢቱ ምስጢራዊነት ምክንያት የተከሰተ እንደሆነ የታወቀ ነው:: ለምሳሌ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች፣ ለጥቂት ጊዜ ቆስሎ ከታየ በኋላ፣ መልሶ የሚፈወሰው የአውሬው ራስ *«ወደ ፊት በአዲስ መልክ የሚገለጠውን የሮም መንግሥት የሚመለከት ነው»* ብለው ያምናሉ:: በእርግጥ አሁን ማንም ሰው በቀላሉ እንደሚመለከተው፣ ሮም ቀድሞ የነበራት ዝናና ክብር ላይ አይደለችም:: *ሥልጣንና ኃይሏም* «ወደፊት ትሆናለች» ተብሎ ከሚገመተው አንጻር እጅግ በጣም ውስን ነው:: ይሁን እንጂ አንድ ቀን ተመልሳ ከሺ ዓመታት በፊት በነበራት ዝናና ገናናነት መገኘቷ አይቀርም፤ ይህም ሲሆን፣ ዜናው በዓለም ሁሉ መገረምና መደነቅ የሚፈጥር ስለመሆኑ አያጠራጥርም:: ከሮም መንግሥት አንጻር ይኼ ታምር የሚሆን ከሆነ ደግሞ፣ ለእርሷ ከሞት የመነሣት ያህል ነውና ማንንም የሚያስደምም ነው፣ የሚሆነው:: እነዚህም *ሰዎች «ቆስሎ የሚሽረው የአውሬው ራስና የሮም እንደገና ማንሰራራት ጽኑ ትስስር አላቸው»* ብለው እንዲያምኑ ያደረጋቸው ምክንያትም ይኼው ነው:: ሆኖም ይኼን የትንቢት ክፍል በተመለከተ፣ ሌሎች የመጽሐፉ ቅዱስ ትንቢት አጥኚዎች ደግሞ የተለየ አሳብ ነው ያላቸው:: እነዚህ ሰዎች





ጉዳዩ በመጨረሻው ዘመን ከሮም እንደገና ማንሰራራት ጋር አብሮ ከሚገለጠው መሪ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው፣ ብለው ያስባሉ:: በእነሱ እምነት የቆሰለው ራስ ምሳሌነቱ፣ ለሐሰተኛው ክርስቶስ ነው:: *«በመጨረሻው ዘመን የሚነሣው ሐሰተኛው ክርስቶስ በሁሉ ነገር ክርስቶስን መምሰል ይፈልጋል:: ስለዚህም ሰውየው ወደ ሥልጣን ከወጣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ በሆነ መንገድ በሰው እጅ ይቆስላል፣ ወይም ጨርሶ ይሞታል፤ ከዚያ ግን የማታለል ኃይሉን በመጠቀም ከሞት እንደተነሣ መስሎ ለመታየት ይሞክራል፤ በዚህም ዓለምን  ያታልላል:: ብዙዎችም ፈርተውና ተደንቀው ይከተሉታል፤ ያመልኩታል»* ይላሉ::

በእርግጥ ነገሩ እንዲህ የሚሆን ከሆነ ድራማው የዓለም ታላላቅ የዜና አውታሮችን ትኩረት እንደሚስብና እነሱም አጋነው እንደሚዘግቡት ጥርጥር የለውም:: እንዲያውም አሁን፣ አሁን እየተዘወተረ እንዳለው ትዕይንቱ የቀጥታ የዜና ሽፋን የማግኘት ዕድሉም ሰፊ ነው:: ምናልባት መሪው፣ መቁሰሉና መሞቱ ከዚያም አልፎ መቀበሩ ከዜና አውታሮች ከተሰማ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከሞት የመነሣቱ ዜና ለዓለም ይታወጅ ይሆናል:: ማን ያውቃል?! እንግዲህ ትንቢቱ እንዲህ የሚፈጸም ከሆነ ደግሞ *«አውሬው ይኼን የመሰለ ድራማ መሥራቱ ምን ይጠቅመዋል?»* የሚለውን አሳብ መመርመር ተገቢ ይሆናል::

በመሠረቱ በመጨረሻው ዘመን የሚነሣው የዐመጽ ሰው ተቀናቃኝነቱ ለክርስቶስ ብቻ ሳይሆን፣ በጌታ ለሆኑት ቅዱሳን ጭምር ነው:: ከዚህ አንጻር ያየነው እንደሆነ ከዚያ ቀደም ብሎ ራሱ የገደላቸውንና በአደባባይ ጥሎ ለዓለም ሲያሳያቸው የነበሩትን የጌታ ምስክሮች ወይም ሁለቱን ወይራዎች ለማስታወስ እንገደዳለን:: በወቅቱ ሬሳቸው ለሦስት ቀናት ያህል ለዓለም ከታየ በኋላ፣ ከሞት ተነሥተው ወደ ሰማይ እንዳረጉ ይታወቃል:: ታዲያ በእነዚህ የእግዚአብሔር ታማኝ ሰማዕታት በኩል ዓለም ያየውን ታምር ለማቃለል፣ አውሬው ይኼን የመሰለ ትርኢት ሊተውን ይጣደፍ ይሆናል:: ደግሞም በእነዚያ ታማኝ ነብያት በኩል ከሆነው ታምር የተነሣ፣ አንዳንድ ሰዎች ወደ እውነተኛው አምላክ መመለሳቸውን ሲያይ፣ ታምሩን ለማጣጣል ለብልሃት የሚፈጥረው ዘዴም ሊሆን ይችላል:: ለነገሩ አውሬው፣

በእርሱ የሚበልጥ ተአምር እንደተገለጠ ለማስመሰል የራሱን ቴአትር እንዲህ አሳምሮ ቢተውን ምን ይደንቃል? ይኼን ማድረጉ የዓለምን ሕዝብ ለማረጋጋትና የሰውን ሁሉ ትኩረት ወደ እርሱ ለመሳብ እንደሚረዳው ግልጥ ነው:: በዚያ ላይ ሥነ ልቦናዊ ፋይዳውም ቢሆን ቀላል አይደለም:: ምናልባትም ተውኔቱ ከተሳካለት፣ ዓለም በእነዚያ «ሁለት ወይራዎች» በተባሉ የጌታ ምስክሮች ለተፈጸመው ድንቅና ታምር ከሰጠው ክብር ይልቅ፣ ይኼኛውን የበለጠ ያደንቅ ይሆናል::

ያም ሆነ ይህ፣ ለሞት ደርሶ የነበረው የአውሬው ቁስል በአስደናቂ ሁኔታ መፈወሱን ባዩ ጊዜ ብዙ ሰዎች በመደነቅ እንደሚስቱ እሙን ነው:: በወቅቱ ሰዎች እጅግ ከመገረማቸው የተነሣ «አውሬውን ማን ይመስለዋል?» እያሉ አውሬውን ማምለክ ይጀምራሉ:: ሆኖም ይህ የሰይጣን ማታለል ከዘመናት ጀምሮ የነበረ እንጂ፣ አዲስ አይደለም:: አውሬው ተናጋሪና አንደበተ ርቱዕ ይመስላል፤ በአንደበቱ በማታለል ሰዎችን ተከታዮቹ ያደርጋቸዋል:: አያሌ ሰዎችም ታላቅ ነገር የሚናገር መስሎአቸው በንግግሩ ይደመማሉ::

አውሬው በምድር በሚሰለጥንባቸው ወራት እግዚአብሔርንና ስሙን መሳደብ ዋነኛ ተግባሩ ሆኖ ይታያል:: በተለይም ከስሞች ሁሉ በላይ ታላቅ የሆነውን «ኢየሱስ» የተሰኘውን ስም አምርሮ ይሳደባል:: እዚህ ላይ እሱ በየትኛውም ጊዜ «ሐሰተኛው ክርስቶስ» እንጂ «ሐሰተኛው ኢየሱስ» እንዳልተባለ ያስተውሏል:: ከዚህ አንጻር ተቀናቃኝነቱ መሲህነትን ወይም ክርስቶስነትን ነው ማለት ይቻላል፤ በመጨረሻው ዘመንም እውነተኛው መሲህ ወይም ክርስቶስ እሱ እንደሆነ ራሱን ይሰብካል:: ይኼም ታላቅ ስድብ ነው:: ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ባለ ጊዜ አይሁዶች ምን ያህል እንደተቆጡ እናስታውሳለን::[137]

ይኼ ለጥፋት የተመደበው የዐመጽ ሰው በዚያ ዘመን ከሚፈጽማቸው አያሌ እኩይ ተግባራት አንዱ የእግዚአብሔርን ማደሪያዎች ሁሉ መሳደቡ ነው:: እነዚህ የእግዚአብሔር ማደሪያዎች የተባሉት ደግሞ

[137]ዮሐ10:36የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልሁ እናንተ አብ የቀደሰውን ወደ ዓለምም የላከውን ትሳደባለህ ትሉታላችሁን?





አስቀድሞ «እናንተ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናችሁ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በእናንተ ይኖራል» በማለት ስለክብራቸው የተነገረላቸው ቅዱሳን ወይም ክርስቲያኖች እንደሚሆኑ ይታመናል:: እነዚህ ቅዱሳንም በዚያን ጊዜ በምድር ላይ የሚኖሩ ቅሬታዎች፣ አለያም ተነጥቀው ወደ ሰማይ የሄዱት ሊሆኑ ይችላሉ:: እናም አውሬው እነርሱም ሆኑ ሥራቸው፣ እንዲሁም የሚያመልኩት አምላክ ትክክል እንዳልነበረ የሚገልጡና ተጨባጭ የሚመስሉ ነገሮችን በማስረጃ እያቀረበ፣ በምድርና በዓለም የቀሩትን ሰዎች ሁሉ እንደሚሞግት ይጠበቃል::

አውሬው በሰማይ የሚኖሩትን ቅዱሳንን ሁሉ ይሳደባል፤ እነዚህኞዎቹ ቅዱሳን ምናልባት በሰማይ የሚኖሩ የእግዚአብሔር መላእክት እንደ ሆኑ ነው የሚታሰበው፤ እነርሱም በዘመናት መኻል ለአንድ አፍታ ሳያርፉ እግዚአብሔርን «ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ» እያሉ ሲያመሰግኑት፣ ሰይጣን ዲያቢሎስ ግን በትዕቢቱ ምክንያት ስፍራውን ተነጥቋል፤ በመጨረሻው ዘመንም ከመልአኩ ሚካኤል ጋር ተዋግቶ ወደምድር ይጣላል:: ከዚህ የተነሣ በመላእክቱ ላይ የመረረ ጥላቻ አለው፤ እናም በዚያ ክፉ ሰው ውስጥ ሆኖ ይኼንኑ በብዙ ስድቦች ይገልጣል ተብሎ ይጠበቃል:: ይሁን እንጂ ይኼን ሊያደርግ የሚችለው በተወሰነለት አርባ ሁለት ወራት ውስጥ ብቻ ነው:: ልብ በሉ! እርሱ «እኔ እግዚአብሔር ነኝ» በማለት አዋጅ እያስነገረ በቅዱሱ ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ አምላክ ከተባለውና ሰዎች ሁሉ ከሚያመልኩት በላይ ራሱን ከፍ፣ ከፍ የሚያደርግ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው::[138]

በሌላም በኩል፣ በወቅቱ ቤተ ክርስቲያን በድንገት የምትነጠቅ ከሆነ፣ በምድር ላይ ከቁጥጥር ውጪ የሚሆን መመሰቃቀልና ግራ መጋባት መከሰቱ አይቀርም:: እንዲሁም ከዚያ ቀጥሎ በዓለም በሚኖሩ ሁሉ፣ በእነዚያ የመጨረሻ ወራት፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሚሆነው ቁጣ የተነሣ፣ በሰዎች ላይ የሚደርሰው መከራ የሚፈጥረው ምሬት ብዙ ነው:: እናም በምድር ያሉ ሰዎች፣ አውሬው ብቸኛው የመፍትሔ ሰው መስሎ ስለሚሰማቸው እምነታቸውን በእርሱ ላይ ለመጣል

[138] 1ኛቆሮ3:16:: ኢሳ6:1-4:: 2ኛተሰ2:4::

ይገደዳሉ:: አውሬው፣ በወቅቱ በምድር የሚኖሩ ቅዱሳንን ተዋግቶ ለተወሰነ ጊዜ ድል እንዲያደርጋቸው ስለሚፈቀድለትና በተለይም እነዚያን ሁለት የመጨረሻው ዘመን ነብያት ለመግደል በመቻሉ፣ ለጊዜውም ቢሆን የልብ ልብ ይሰጠው ይሆናል:: ደግሞም ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ስሞቻቸው በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፉና በምድር የሚኖሩ ሁሉ ለአውሬው ይሰግዳሉ::

የሰው ሁሉ ደኅንነት ዓለም ሳይፈጠር በፊት የታወቀ ቢሆንም፣ ለሰው ግን በዘመን መጨረሻ ተገለጠ:: ዳሩ ግን ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ሳልተቀበሉ፣ የአውሬው መምጣት በታምራትና በምልክቶች፣ በሐሰተኞች ድንቆችም በዐመጽም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው:: ስለዚህም ምክንያት በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዐመጻ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፣ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ፣ እግዚአብሔር የስህተት አሠራርን ይልክባቸዋል:: ሰዎችም አውሬው የሚከተሉትና ለእርሱ የሚሰግዱት ከዚህ የተነሣ ነው:: እግዚአብሔር ግን ለሁሉም ነገር ጊዜ ወስኖለታል፤ ይማረክ ዘንድ ያለው ማንም ቢኖር ወደ ምርኮነት ይሄዳል፤ በሰይፍ የሚገደል ቢኖር እርሱ ራሱ በሰይፍ እንዲገደል ይገባዋል፤ ከሌላው ጊዜ ይልቅ የቅዱሳን ትዕግሥትና እምነት የሚፈተነው በዚያን ጊዜ ነው::[139] በዚህ ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ የሚያደርግ ሰው፣ ምንኛ ምስኪን ሰው ነው?

ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ በአሁን ሰዓት እንኳ በዓለም እየሠራ ነው:: ዳሩ ግን በግልጥ እንዳይሠራ የሚከለክለው ነገር ገና ከመንገዱ ላይ ስላልተወገደለት እስከ አሁን በስውርና በሚስጥር እንዲሠራ ተገዷል:: ደግሞም ሰዎችን በተለያየ መንገድ፣ ማለትም በሳይንስ በቴክኖሎጂ፣ በልዩ ልዩ ሃይማኖት፣ በልማድና በባህል ስም ተብትቦ የሚያጭበረብረው ይኼው መንፈስ ነው:: ለአብነት ያህል እንኳ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ስም ወደ ምድር እየደረሱ ያሉ አንዳንድ ነገሮችን በአንክሮ ብናስተውል *«ለከርሞ የሚያብድ ዘንድሮ ድንጋይ*

[139] ራእ13:10::





*ያቀብላል»* የሚለውን አገራዊ ብሂል የሚያስታውሱ ናቸው:: ከነዚህ መኻል እስቲ «ክሎኒንግ» ስለሚባለውና የ«ጄኔቲክ ኢንጅነሪግ» ቴክኖሎጂ አካል ስለሆነው ጉዳይ ትንሽ እንመልከት::

«ክሎኒንግ» የሚባለው «ቴክኖሎጂ» ያለ ወንድና ሴት ግንኙነት ወይም የወንድ ዘርም ሆነ የሴትዋ ዕንቁላል ሳያስፈልግ ሰውን ከአንድ ሕዋስ ብቻ ለመፍጠር የሚያስችል «ጥበብ» ነው:: ይህም ማለት፣ ፅንሱን ለማጎልበት ተግባር ብቻ ማህፀንዋን ካከራየችዋ ሴትና ሕዋሱን ከለገሰው ሰው በቀር/ወንድ ወይም ሴት ሊሆን ይችላል/ ወደ ዓለም ለሚመጣው አዲሱ ሰው፣ ምንም ዓይነት ዘመድ ወይም ቤተሰብ የለውም ማለት ነው::

ምንም እንኳ ቴክኖሎጂው እስከአሁን በአሜሪካና በምዕራብ አውሮፓ አገራት መንግሥታት የሰላ ተቃውሞ እየደረሰበት የከረመ ቢሆንም፣ በተወሰኑ እንስሳት ላይ ተሞክሮ ባሳየው ውጤት ተስበው አንዳንድ አገሮች ጥለውት የነበረውን እገዳና ለምርምሩ የከለከሉትን የገንዘብ ድጋፍ ቀስ በቀስ በመልቀቅ ላይ መሆናቸው ይነገራል:: በተጨማሪም *«ምርምሩ ከሰው አካላት ውስጥ በአደጋ፣ በበሽታ፣ በእርጅና ወይም በሌላ ምክንያት አገልግሎታቸው ለተስተጓጎለ ብልቶች መለወጫ ለማግኘት እጅግ ይረዳናል»* የሚለው የተመራማሪዎቹ መከራከሪያ አንዳንድ በክልከላው አክራሪ አቋም የነበራቸውን ሰዎች በአቋማቸው እንዳይጸኑ እጅግ እየተፈታተናቸው ይገኛል:: ከዚህ በተረፈ ግን አንዳንድ ሰዎች የምርምሩን አቅጣጫ ሌላ መልክ እንዲኖረው ሊያደርጉት ስለሚችሉ ጉዳዩን በአንክሮ መከታተል ይገባል፣ የሚል አሳብ አለኝ:: ደግሞም አሁን፣ አሁን ከዚሁ «ቴክኖሎጂ» ጀርባ አንዳች የሰይጣን ስውር እጅ እንዳለበት እየተመለከትን ነው:: ለምሳሌ በአንድ ወቅት በድረ ገጽ ተለቆ የተገኘ አንድ አስገራሚ ጽሑፍ እንዲህ ይነበባል::

> *የምንኖረው ጎዶሎና በኃጢአት በተበላሸ ዓለም ውስጥ ነው:: ከዚህ የተነሣ ወደየትኛውም አቅጣጫ ብንመለከት ዓይኖቻችን መልካም ነገር ለማየት አልታደሉም:: ሬዲዮና ቴሌቪዥኖቻችን በየዕለቱ ስለጦርነት፣ ረሀብ፣ ድህነት፣ ሁከት፣ ሙስናና ልቅ ወሲብ ከመሳሰሉ የሰይጣን*

*ሥራዎች በቀር የሚያወሩት ደግ ወሬ የላቸውም:: እነዚህ ዝርዝር ሁኔታዎች የዓለምን ፍጻሜ የሚያፋጥነው የአርማጌዶን ጦርነት እየቀረበና እየመጣ እንደሆነ የሚያመለክቱ ናቸው:: ለእኛ ግን የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ዋነኛ ተስፋችን ነው፤ ነገር ግን የእርሱን መምጣት ብቻ ቁጭ ብለን መጠበቅ የለብንም፤ ክርስቶስ፣ እኛው ራሳችን እንድናመጣው መንገዱን ሰጥቶናል፤ «እግዚአብሔር ደግሞ ራሳቸውን የሚረዱትን ይረዳል!» ክርስቶስ የተገነዘበት የከፈን ጨርቅ ተገኝቷል፤ በላዩም ላይ የደሙ ነጠብጣብ እንዳለ ነው፤ ከደሙ ውስጥ ደግሞ የክርስቶስን ዲ.ኤን.ኤ ማግኘት ይቻላል:: ስለዚህም ዕድሜ ለሳይንስና ለቴክሎኖጂ ክርስቶስን በክሎኒንግ ዳግመኛ ልናመጣው ወይም ልንፈጥረው ከመቻላችም በላይ፣ ለእኛ ብቻ ሳይሆን ክርስቶስን ለሚፈልጉ ሁሉ ደግመን ልናመጣላቸው እንችላለን:: ማንኛዋም ሴት፣ /ድንግል እንኳ ብትሆን/ ክርስቶስን አርግዛ መውለድ ትችላለች፤ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔርን ስንፈልግ ወደ ፓስተሮቻችን ወይም ቄሶቻችን መሄድ አስፈላጊ አይደለም፤ ጥያቄ ሲኖረን ክርስቶስን ወደ ቤታችን መጥራት ብቻ! እናም ጥያቄአችንን መጠየቅ:: እስቲ እናስበው ክርስቶስ በሁሉ ቦታ፤ በየሰው ሁሉ ቤት! ምድር ራስዋ ገነት ሆነች ማለት አይደለምን?! ስለዚህ ለምታውቁት ሁሉ ስለ ክርስቶስ ንገሩ፤ ከየትም መጠበቅ አያስፈልግም፤ እነሱም የራሳቸው ክርስቶስ ሊኖራቸው ይችላሉና::*

ይህ «ቴክኖሎጂ» ተብዬ ነገር፣ የፈጣሪንና የተፈጥሮን ሕግ ምን ያህል እንደሚጻረር መታዘብ ይቻላል:: ታዲያ እኛስ *«አጋንንታዊ ሴራ አለበት»* በማለት ደፍረን መናገራችን፣ አላዋቂ የሚያሰኘን ይሆን? በዚያ ላይ ወደፊት በዚህ በኩል ሰርጎ ገብቶ ዓለምን የሚያሸብር አንዳች ሚስጥራዊ አሠራር ሊኖር እንደሚችል መገመት እንችላለን:: ምናልባትም አንድ ቀን *«አንዲት ወንድ የማታውቅ ድንግል፣ ወንድ ልጅ ወለደች»* ይባል ይሆናል! ቀጥሎም ይኼው ልጅ ድንገት *«እኔ ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የሰላም አለቃ ነኝ»* ብሎ አደባባይ፣ በድፍረት ይደሰኩር ይሆናል:: *«ጠርጥር ከገንፎም አይጠፋም ስንጥር»* የተባለው እንዲህ ዓይነቱን አይደለምን?





## ከምድር
## የሚወጣው አውሬ
140

ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፤ የበግ ቀንዶች የሚመስሉ ሁለት ቀንዶች ነበሩት፤ እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር፤ በፊተኛውም አውሬ ሥልጣን በእርሱ ፊት ሁሉን ያደርጋል::

ከዚህ አስቀድሞ የታየው አውሬ፣ ከባሕር የወጣ ሲሆን፣ ይኼኛው ግን ከምድር የሚወጣ ነው:: *«ሁለተኛው አውሬ ከምድር መውጣቱ፣ ምናልባት ከተስፋው አገርና ሕዝብ መኻል የሚነሣ እንደሚሆን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም»* ተብሎ ስለሚታሰብ፣ በአሁኑ ጊዜ ከአይሁዳውያን መኻል ይነሣ ይሆናል፣ ተብሎ እንዲጠበቅ ሆኗል:: የመጀመሪያው አውሬ፣ ሮምን ጨምሮ በተመሳሳይ ሰዓት በሚነግሡ መንግሥታት ላይ ተሹሞ የሚመጣ ከመሆኑም በላይ፣ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ሥልጣን ያሉት ነው፤ በአንጻሩ ሁለተኛው አውሬ ትኩረቱ ሃይማኖታዊው ሥርዓት እንዲሁም የንግድና የኢኮኖሚው መዋቅር ናቸው::

አውሬውም የበግ ቀንዶች የሚመስሉ ሁለት ቀንዶች ያሉት ሆኖ መቅረቡ፣ ምናልባት እንደ በግ የዋህና ሃይማኖተኛ መስሎ የሚገለጥ መሆኑን የሚያመለክት ይሆናል:: በብሉይ ኪዳን ሆነ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በግ ለክርስቶስ ማንነት ምሳሌ ሆኖ ሲያገለግል እንደ ቆየ ይታወቃል፤ ለምሳሌ ዮሐንስ መጥምቁ ክርስቶስን ገና እንዳየው «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስተሰርይ የእግዚአብሔር በግ» ብሎ ነበር የጠራው:: ከዚህ አንጻር ሁለተኛው አውሬ፣ እንደ ክርስቶስ የዋህና ትሁት ለመምሰል የሚሞክር ይመስላል:: አንዳንድ መምህራንም አውሬው፣ ሐሰተኛው ክርስቶስ እንደሆነ የሚያስተምሩት ከዚህ የተነሣ ነው::[141]

[140] ራእ13:11::
[141] ማቴ7:15:: ማቴ21:24::

ከምድር የሚወጣው አውሬ፣ እንደዘንዶ ይናገራል፤ አስቀድሞ ከባሕር በወጣው አውሬ ሥልጣንም ልዩ፣ ልዩ ታምራት ያደርጋል:: ስለዚህ ከእርሱ ጀርባ ሆኖ ሁሉን የሚሠራው ያው ዘንዶው ወይም ዲያቢሎስ ነው ማለት ነው:: አውሬው እሳት ከሰማይ እስኪያወርድ ድረስ በሰው ፊት ታላላቅ ምልክቶችንና ድንቆችን ያደርጋል፤ ዓላማውም እርሱ ከማንኛውም አምላክ በላይ እንደሆነ በማሳየት፣ የእግዚአብሔር ነብያትና ሐዋርያቱ በጌታ መንፈስና ኃይል ያደረጓቸውን ታምራት ዋጋ ማሳጣትና ማጣጣል ነው:: በእርግጥም ከጥንት እስከ ዛሬ እንዲህ ዓይነት ምልክቶች ማድረግ የቻሉ ነብያት በጣት የሚቆጠሩ ብቻ ናቸው፤ ለአብነት ያህል እንጥቀስ ብንል እንኳ በጥንት ዘመን ኤልያስ በታላቁ መከራ ዘመን ደግሞ «ሁለቱ ወይራዎች» የተባሉትን ነብያት ብቻ ነው የምናገኘው:: በመሆኑም ብዙ ሰዎች ምልክቶቹን ሲያዩ፣ የሚነግራቸውን ሁሉ «አሜን» ብለው ይቀበላሉ::

በመጨረሻው ዘመን እንደ የዋህ በግ መስሎ ዓለምን የሚያስተው ይህ ሰው፣ ሐሰተኛው ነብይ በመባል ይታወቃል፤[142] የእሱ ቀዳሚ ተግባር ሰዎች ሁሉ ሐሰተኛው ክርስቶስን እንደመሲህ እንዲቀበሉት ማድረግ ነው:: በሚያደርጋቸው ልዩ፣ ልዩ ታምራት ብዙዎችን ከማሳቱ በላይ በሰይፍ ቆስሎ ለዳነው የመጀመሪያው አውሬ ምስል እንዲሠሩ፣ በምድር የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ ያዛቸዋል:: እናም በጥንት ዘመን ናቡከደነፆር በባቢሎን ምድር በዱራ ሜዳ እንዳቆመው፣ ከዚያ በኋላ የሮም ቄሳሮች ለዓመታት ሲያደርጉት እንደኖሩት ሁሉ ሐሰተኛው ክርስቶስም ምስሉን አቁሞ ለጥቂት ወራት አምልኮና ስግደትን ይቀበላል:: ሆኖም ከዚህ በፊት ምስል አቁመው አምልኮ ከተቀበሉ ነገሥታት ይኼን ሰው የሚለየው የእሱ ምስል ሕይወትና እስትንፋስ ያለው መሆኑ ነው:: ይኼም የሚሆነው ሐሰተኛው ነብይ ለሐሰተኛው መሲህ፣ ምስል በሚያቆምበት ጊዜ ምስሉ ሕይወትና እስትንፋስ እንዲኖረው የሚያስችል ሥልጣን ስለሚሰጠው ነው:: ደግሞም ምስሉ ሕይወትና እስትንፋስ ያለው ብቻ ሳይሆን መናገር የሚችል ሆኖ

[142] ራእ19:20::





በየስፍራው ስለሚቆም ለእርሱ የማይሰግዱትን ሁሉ ራሱ እየጠቆመ ወይም ለአውሬው እያስታወቀ እንዲገደሉ ያደርጋል:: ይኼም ነገሩ በዘመኑ ለአውሬው ታላቅ ክብርና መፈራትን ያስገኝለታል::

በዚህ ዓይነት መንገድ የአውሬው ምስል በየስፍራው ተገኝቶ፣ ሁሉን ለመቆጣጠር መቻሉ፣ የእውነተኛውን አምላክ ሙሉዕነት ለመሸራረፍ ወይም ዋጋ ለማሳጣት የሚጠቀምበት ሌላው የማታለል ዘዴ መሆኑ ግልጥ ነው:: ጉዳዩን በአሁኑ ዘመን ካለው ዕድገት አንጻር ያየነው እንደሆነ፣ ምናልባት የመንፈስ አሠራር ብቻ ሳይሆን የረቀቀ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ድብልቅ ውጤት ሊሆን እንደሚችል እንጠረጥራለን:: ሆኖም ግን ይህ ገና ወደፊት የሚገለጥ በመሆኑ፣ ስለጉዳዩ እርግጠኛ ሆኖ መናገር አይቻልም:: አቤት ያ ዘመን ግን እንዴት አስጨናቂ ነው?! ከዚያ አምልጠው በሰማይ የሚገኙ ቅዱሳንስ በእውነት እንዴት የታደሉ ናቸው?

6561

> ጥበብ በዚህ አለ:: አእምሮ ያለው የአውሬውን ቁጥር ይቍጠረው፤ ቁጥሩ የሰው ቁጥር ነውና፣ ቁጥሩም ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ነው::[143]

ሁለተኛው አውሬ ለመጀመሪያው አውሬ ምስል በማቆም ብቻ ረክቶ አይወሰንም፤ ከዚህ በተጨማሪ ሰዎች የአውሬውን ስምና ምልክት እንዲቀበሉ ያስገድዳል፤ ነገሩ ደግሞ ሃይማኖታዊ ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግዴታ እንዲሆን ወዲያው ይደነግጋል:: በታላቁ መከራ ጊዜ ከሚሆኑ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች ሌላ፣ ከሰዎች የግል ውሳኔ አንጻር ታላቅ ፈተና የሚሆነው ይኼ ነገር መሆኑ ገና ከአሁኑ ጎልቶ ይታያል:: በዚያ ዘመን የሚኖሩ ሰዎች የወደዱትን ዓይነት አምልኮም ሆነ የፈቀዱትን አምላክ ለማምለክ ፈጽሞ አይፈቀድላቸውም:: በወቅቱ፣ አውሬውን ማምለክና የእርሱ ጋሻ ጃግሬ የሆነውን ሐሰተኛ ነቢይ ቃል መታዘዝ ጽኑ ግዴታ ነው:: በእርግጥ በእነዚያ ወራት በሕይወተ ሥጋ በምድር የተገኘ ሰው፣ በሕይወት ለመቆየት ከፈለገ፣ የአውሬዎቹን ቀጭን ትዕዛዝ የማክበር ግዴታ ውስጥ ይገባል:: እያንዳንዱ ሰው ደግሞ ትዕዛዙን መፈጸሙ የሚታወቀው ለዚሁ የተዘጋጀውን ምልክት በግንባሩ ወይም በቀኝ እጁ ላይ ያደረገ እንደሆነ ነው:: ምልክቱን ያደረገ ሰው፣ ያለ ምንም ችግር መግዛትና መሸጥ ሲችል፣ ምልክቱን ያላደረገ ሰው ግን፣ ምንም ዓይነት ነገር መግዛትም ሆነ መሸጥ አይችልም:: ነገሩም እንዲህ ይሆናል፤ በእነዚያ አውሬዎች ዘመን፣ */አውሬ የተባሉት በላያቸው ላይ ከሚገለጠው ክፋት የተነሣ መሆኑን ልብ ይሏል/* ታናናሾችም ሆኑ ታላላቆች፣ ድኾችም ሆኑ ሀብታሞች፣ ጌቶችም ሆኑ አገልጋዮች፣ በቀኝ እጃቸው ወይም በግንባራቸው ላይ ምልክት እንዲያደርጉ ይገደዳሉ:: የአውሬው ስም የሆነው ምልክትና የስሙ ቁጥር የሌለው ማንም ሰው፣ መግዛት ወይም መሸጥ አይችልም::

[143] ራእ13:11-18::





ምልክቱ በተለይ ዮሐንስ በኖረበት ዘመን ከነበረው የባሪያ አስተዳደር ሥርዓት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ሆኖ ይታያል:: የጥንት ዘመን ባሮች በጌቶቻቸው ዘንድ የሚታዩት፣ ሕይወት እንዳለው ቋሚ ንብረት ነበር:: በዚህም ምክንያት ጌታው፣ በባሪያው ላይ የፈለገውን ምልክት የማኖር መብት ነበረው:: በሌላም በኩል ሰዎች ለአማልክቶቻቸው ያላቸውን ታማኝነት ለማሳየት ሲፈልጉ፣ በአካላቸው ላይ ምልክት ይታተምባቸው እንደነበር ይነገራል:: ልክ እንደዚሁ ከባሕርና ከምድር የሚወጡት እነዚያ አውሬዎች በሚሰለጥኑባቸው የመጨረሻ ወራት በምድር የሚገኙ ሰዎች ሁሉ፣ የዘንዶው አንጡራ ንብረቶች እንደሆኑ ነው፣ የሚቆጠሩት፤ ይህንንም ለማረጋገጥ በሰውነታቸው ውስጥ እጅግ በረቀቀ መንገድ ሚስጥራዊ ምልክት እንዲቀበርባቸው ይደረጋል::

በነገራችን ላይ አሁን በዓለም ያለው የኑሮ ሥርዓት፣ ወደፊት ሰዎች ይኼን ጉዳይ በቀላሉ እንዲቀበሉት እያለማመዳቸው ከመሆኑም በላይ አንዳንድ ሁኔታዎችም የሥርዓቱን መዘርጋት የሚያስገድዱ እየሆኑ ነው:: ስለዚህ በሚመጡት ዓመታት ሰዎች የተጠቀሰውን ዓይነት ምልክት መቀበልን እንደቀላል ነገር ቢቆጥሩት አያስደንቅም:: እናም ጥበብ ያለው አእምሮ የሚያስፈልገው እዚህ ላይ ነው:: በመጨረሻው ዘመንም የሰይጣንን ማታለልና የስህተት አሠራር አውቀው እንቢ ማለት የሚችሉት ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች ብቻ ናቸው::

እርግጥ ነው፣ በዚያ ዘመን ቤተ ክርስቲያን እንደምትነጠቅ ለሚያምን ሰው፣ በእንዲህ ዓይነት የሕይወት ሥርዓት ውስጥ የማለፍ ዕድሌ የመነመነ ነው ብሎ ቢያስብም፣ ምናልባት ነገሮች እንደጠበቀው ሳይሆኑ ቀርተው በሆነ ምክንያት በወቅቱ በምድር ቢገኝ፣ ብቸኛው የማምለጫ መንገድ አስቀድሞ ይኼን ጥበብ ማወቁ ነው:: በሌላም በኩል በአንዳንድ ስፍራዎች እንደሚታየው ክርስቲያኖች መንፈሳዊ በመሆናቸው የተነሣ አእምሮአቸው ምንም እንደማይጠቅም አድርገው ሲያስቡ ይታያሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን አንድ ሰው በጌታ ኢየሱስ ሲያምን፣ በአእምሮው መታደስ እንደሚለወጥ እንጂ አእምሮውን እንደሚጥል አይነግረንም:: አእምሮው በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ ሰው፣ አስተሳሰቡ የተለየ ስለሚሆን፣ መላው የሕይወት ሥርዓቱ፣ አካሄዱና

አረማመዱ ፍጹም የተለየ ሆኖ ሲመላለስ ነው የሚታየው::[144] ከዚህ አንጻር በመጨረሻው ዘመን የሚሆኑትን ነገሮች ሁሉ ለማስተዋል ጥበብ የሞላበት አእምሮ እንደሚያስፈልግ የሚያከራክር አይደለም::

አውሬው የራሱ ቁጥር ያለው ሲሆን፣ ቁጥሩም 666 እንደ ሆነ ታውቋል:: ዳሩ ግን በየዘመናቱ የነበሩ የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎችን ግራ ከሚያጋቡና ለመተርጎምም አስቸጋሪ ከሆኑ ክፍሎች አንዱ ይህ ክፍል ሆኖ እንደመሆኑ፣ ምንነቱን ለመረዳት ቀላል አይደለም:: በዮሐንስ ራእይ፣ በብዙ ቦታዎች የተጠቀሰ አንድ ቁጥር አለ፤[145] ይኼም ሰባት ቁጥር ነው:: ብዙ ሰዎች ግን ይኼ የሆነው በአጋጣሚ ሳይሆን ሰባት ቁጥር የእግዚአብሔርን ፍጽምናና ሙሉነት የሚያሳይ ቁጥር በመሆኑ ነው ይላሉ:: ዳሩ ግን ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ጊዜ ስድስት ቁጥር የተጠቀሰው በዚህ ክፍል ነው:: ስድስት ደግሞ ለሰባት አንድ የጎደለው ቁጥር ነው::

ለመሆኑ፣ አውሬው በሰዎች ላይ ለሚያደርገው ምልክት ስድስት ቁጥር የተመረጠው ለምን ይሆን? ምናልባት ሰይጣን በሰው አድሮ፣ ራሱን ከአምላክ እኩል አስመስሎ ቢገለጥም፣ እርሱ መቼም ቢሆን ወደ አምላክነት ሙላት ሊደርስ እንደማይችል ለማመልከት ታስቦ ይሆን? ደግሞስ «ቁጥሩ የሰው ቁጥር ነው» መባሉ ሐሰተኛው ክርስቶስ ለአምላክ ብቻ የሚገባውን አምልኮ ቢፈልግም እንኳ፣ አምላክ ሊሆን እንደማይችል ለመግለጥ ተፈልጎ ይሆን? በእውነት ሚስጥሩ ብዙም ግልጥ አይደለም:: በእርግጥ አንዳንድ ሰዎች *«ሰው በስድስተኛው ቀን ስለተፈጠረ፣ ቁጥሩ "የሰው ቁጥር" መባሉ ለዚህ ነው»* ይላሉ:: ምናልባት ሊሆን ይችላል::

ሆኖም ግን ይህ 666 የሚባለው ነገር፣ ዓለም በአሁኑ ሰዓት እጅግ እየፈለገችው ካለ አንድ ነገር ጋር የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም ተብሎ ይታመናል:: ይኼም እንከን የለሽ የፋይናንስ ሥርዓትንና አስተማማኝ የገንዘብ ዝውውርን የሚመለከት ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነ በአሁኑ

[144] ሮሜ12:1-2::
[145] ከሃያ ጊዜ ያለነሠ





ጊዜ ማንም ሰው በእጁ ስለያዘው ገንዘብ ትክክለኛነት እርግጠኛ ሆኖ መናገር እስከማይችል ድረስ ሐሰተኛ ገንዘቦች ከእውነተኛው ገንዘብ ተመሳስለው እየተሠሩ ነው፤ ከዚህም በላይ ስርቆት፣ ዝርፊያና ቅሚያ በዓለም ሁሉ ተስፋፍቷል፤ ይኼን ለመከላከል ደግሞ ረቀቅ ያለ ቴክኖሎጂ እንሚያስፈልግ ብዙዎች ይስማማሉ:: ከዚህ በተጨማሪ ዓለማችንን አስጨንቀዋት ካሉ ጉዳዮች አንዱ የሆነው ሙስና፣ ስር እየሰደደና እየተስፋፋ የመሄዱ ነገር ነው:: በአሁኑ ጊዜም *«ሙስና የሌለበት አገር ፈጽሞ የለም»* እስኪባል ድረስ በስርጭት አድማሱ በመላው ዓለም ተንሰራፍቶ ይታያል:: ከጥቂት ዓመታት በፊት በአንጻራዊነት ሲታይ ከሌሎች ይሻሉ በነበሩ አንዳንድ አገሮች ውስጥ እንኳ ሳይቀር ይህ የማኅበረሰብ ነቀርሳ እንደሰደደ እሳት እየተዛመተ ነው:: ችግሩን ለመከላከልና ለማስወገድ እንደ ቻይና ያሉ አገሮች የሙስና ወንጀል ሲፈጸሙ የተገኙ ሰዎች በሞት የሚያስቀጣ ሕግ ቢያወጡም እንዲያውም ባሰበት እንጂ፣ አልተሻለውም:: ስለዚህ «መፍትሄው ምንድነው?» የሚለው፣ ብዙዎችን የሚያብከነክን ሆኗል::

በሌላም በኩል የገንዘብ ፍሰትንና ብክነትን በጊዜ ለመቆጣጠር ካልተቻለ ዓለማችን ከቁጥጥር ውጪ ወደ ሆነ የፋይናንስ ቀውስ ልትገባ እንደምትችል በተለይ ከ2007 ወዲህ የተከሰተውን የፋይናንስ ችግር በዋቢነት የሚጠቅሱ ብዙዎች ናቸው:: በእርግጥም በ2008 እና በ2009 ብቻ በተከሰተ የፋይናንስ ቀውስ ምክንያት የዓለም ታላላቅ መንግሥታት ከአስር ትሪሊዮን ዶላር በላይ ኪሳራ ደርሶባቸዋል:: በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚከሰት የፋይናንስ ቀውስ፣ በእያንዳንዱ ግለሰብ እጅ ከሚዘዋወር ገንዘብ የሚጀምር በመሆኑ መንግሥታት ይኼን መቆጣጠር እንዳለባቸው የተረዱ ይመስላሉ፤ በመሆኑም ከአሁኑ የተለያዩ ሕጎችን ማርቀቅና መደንገግ ጀምረዋል:: ይሁን እንጂ የፋይናንስ ቀውስ ጨርሶ እንዳይከሰት፣ ከአስተማማኝ የገንዘብ ሥርዓት ባሻገር ተጨማሪ አማራጭ እንዳለ አሻግረው በመመልከት ላይ ያሉ ይመስላሉ:: ለምሳሌ በዓለም ሁሉ አንድ ዓይነት የመገበያያ ገንዘብ ብቻ ለምን አይኖርም? የሚለው አንዱ አማራጭ ሊሆን ይችላል:: ይኼም በአሁኑ ጊዜ የአውሮፓ ኅብረት አገራት

እንዳደረጉት ማለት ነው። ነገር ግን አሁን ምድር ላይ ካለው እውነታ አንጻር የአውሮፓ ኅብረትን ተሞክሮ በዓለም ሁሉ መፈጸም አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም በአገራቱ መኻል ያለው የዕድገት ልዩነት ለአውሮፓ እንኳ ምን ያህል ፈተና እንደሆነ በእነዚህ 11 ዓመታት ተፈትኖ ተረጋግጧል። ለዚህም ግሪክ፣ አየርላንድና ፖርቹጋልን የመሳሰሉ አንዳንድ የኅብረቱ አገራት ከ2009 ጀምሮ የገጠማቸውን የኢኮኖሚ ፈተና፣ እንደ አብነታዊ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪ አሁን ባለው የወረቀት ገንዘብና ሌሎች የፋይናንስ አሠራሮች ብቻ ታምኖ ወደአንድ ዓይነት የገንዘብ ምንዛሬ ዘው ብሎ መግባት፣ ዝውውሩ በቀላሉ በሕገወጦች ለመጭበርበር የተጋለጠ ከመሆኑ አንጻር ከባድ መስሎ ይታያል። ስለዚህ ጉዳዩ ያሳስበናል የሚሉ የዓለም መንግሥታት እነዚህን ፈተናዎች ለመጋፈጥ ቀድመው መዘጋጀት እንደሚኖርባቸው ተረድተውታል። ደግሞም ሙስናንም ሆነ የገንዘብ ዝውውር አደጋን ለመከላከል ከተፈለገ ሕግ ከማውጣት ባለፈ በሥራ ላይ ካለው የቁጥጥር ብልሃት በተጨማሪ የተሻለ ቴክኖሎጂ መጠቀም አዋጪ መፍትሄ ሊሆን እንደሚችል እየታመነ መጥቷል። ምንም እንኳ ሚስጥራዊ መዘዛቸው እንዳለ ቢሆንም፣ አሁን፣ አሁን እየተፈለሰፉ ያሉ ቴክኖሎጂዎች ለእነዚህ መሠረታዊ የማኅበረሰብ ችግሮች መልስ ያላቸው መስለው እየታዩ ነው፤ ከእነዚህ መኻል ደግሞ እንደ «ማይክሮ ቺፕ» ያሉት የቴክኖሎጂ ግኝቶች በተለይ ጎልተው የሚጠቀሱ ናቸው። ምክንያቱም ቴክኖሎጂው እያንዳንዱ ሰው ወደ ኪሱ የሚያስገባትን ሳንቲም ከየትና እንዴት እንዳገኛት ለማወቅና ለመተንተን ቀላል ስለሚያደርግ ነው። በአሁኑ ጊዜ ዓለም እንዲህ «ልብን የሚያሳርፍ» ነገር እየፈለገች በመሆኑ ከጥቂት ጊዜአት በኋላ «ቴክኖሎጂው» በመንግሥታትና በሕዝቦች ሁሉ ዘንድ አማራጭ የሌለው ብልሃት ሆኖ ሊታይ ይችላል።

በእርግጥ አንዳንድ ሰዎች *«ቴክኖሎጂው የግል መብታችንን የሚጻረር ነው»* ብለው ተቃውሞአቸውን ሊያቀርቡ ይችላሉ፤ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችም ጉዳዩን አጋነው መከራከራቸው አይቀርም። ነገር ግን በዓለም ላይ እየደረሰ ካለው ኪሳራና ወደ ፊትም ሊሆን ከተደቀነው





አደጋ አንጻር የቱንም ዓይነት ጩኸት ሰሚ የሚያገኝ አይመስልም። በተጨማሪም *«የእያንዳንዱ ሰው ሚስጥር ጉዳዩ በሚመለከታቸው በተወሰኑ አካላት ዘንድ በጥብቅ እስከተጠበቀ ድረስ አሳሳቢነቱ ምኑ ላይ ነው?»* የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ አቅም ላይኖራቸው ይችላል።

ከዚህ ባለፈ ግን ቴክኖሎጂው በእያንዳንዱ ሰው መኻል የሚኖረውን የገንዘብ ዝውውር በተመለከተ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ስለሚያሰፍን እንኳን በሥራ ላይ ውሎ እንዲሁ ሲታሰብ እንኳ ያጓጓል። ልብ በሉ! ይህን ዓይነት ቴክኖሎጂ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ማንም ሰው እናንተ ለዓመታት የደከማችሁበትን ገንዘብ ሰርቆ፣ ዘርፎ ወይም ቀምቶ የራሱ ማድረግም ሆነ መሸሽግ አይችልም። በየመሥሪያ ቤቱ ጉዳያችሁን ለማስፈጸም በገባችሁ ቁጥር ለመማለጃ «ይኼን ያህል ገንዘብ ካላመጣህ» ተብላችሁ ኢፍትሐዊ ውሳኔ ሊተላለፍባችሁ አይችልም። በአጭሩ ማንም ሰው በላቡና በድካሙ ሠርቶ ባገኘው እንጂ፣ በሰው ሐቅ የሚኖርበት ሁኔታ ጨርሶ አይኖርም። «አዲሱ ቴክኖሎጂ ለዚህ ሁሉ መፍትሔ ይኖረዋል» ይባልለትም ይሆናል። ሆኖም የቴክኖሎጂው አስፈላጊነትና ጥቅም በንግድ ወይም በገንዘብ ሥርዓቱ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይመስልም። በመሆኑም እንደ የጤናና የመታወቂያ ወረቀት፣ ፓስፖርት፣ የትምህርት፣ የመንጃ ፈቃድ፣ የፖሊስ ማስረጃዎችንና የመሳሰሉትን ሁሉ በአንድ ላይ አጠቃሎ እንዲይዝ ሆኖ ስለሚሠራ፣ ነገርየው በሁሉ ዘንድ ተመራጭ እንደሚሆን የሚያጠያይቅ አይደለም።

በእርግጥ ነገሩን ሲሰሙት የሳይንስ ልቦለድ የመስማት ያህል ዘና ሊያደርገን ይችል ይሆናል። ዳሩ ግን ይኼን ቴክኖሎጂ ተግባራዊ ለማድረግ ዓለማችን ከዓመታት በፊት ጀምራ እየተዘጋጀችበት ያለ ጉዳይ ነው። ምናልባትም ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለዘመናት እንደሚፈጸም የሚጠበቀው የ666 ትንቢት ጉዳይ ፍጻሜ ያገኝ ይሆናል። በእርግጥ ቴክኖሎጂው ከዚህ ቁጥር ጋር እንዴት እንደሚሠራ አይታወቅም። አሁን ባለው ሁኔታ ግን ወደፊት በእጅና በግንባር ላይ ሊቀበር ከታለመው የማይክሮ ቺፕ አካል ከሆነውና «ቬሪ ቺፕ» ከተሰኘው የሳይንስ ግኝት ጋር እጅግ የሚመሳሰልበት ነገር አለው።

## ቺፕ አስደርግ

አእምሮ ያለው ያስተውለው ዘንድ ስለዚህ ጉዳይ «ታይም» በተባለ መጽሔት ተጽፎ ያገኘሁትን መረጃ እንዳለ አቅርቤዋለሁ::

*የትምህርት ቤቱን ዩኒፎርም እንደለበሰ ድንቡሽቡሽና ሳሙኝ፣ ሳሙኝ፣ የሚሉትን ጉንጮቹን ሲመለከቱ፣ ዴሪክ ጀስኮብስ ተራ ትንሽ ልጅ መስሎ ሊታይዎት ይችላል:: ሆኖም ውጪውን አይተው እንዳይሳሳቱ፤ ልጁ ገና በአስራ ሁለት ዓመቱ «ማይክሮ ሶፍት» ከሚባለው ድርጅት፣ በሲስተም ኢንጅነርነት የብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቶታል:: ይህ ልጅ በአስራ ሦስት ዓመቱ፣ የራሱ የሆነና የኮምፒዩተር የማማከር አገልግሎት የሚሰጥ ኩባንያ ያንቀሳቅስ ነበር፤ አሁን አስራ አራት ዓመቱ ነው፤ ደግሞ በዚህ ዕድሜው ምን ሊያሳየን ይሆን? አዎ! በዚህ ዕድሜው ግማሽ ሰው ግማሽ ኮምፒዩተር እየሆነ ነው» ይለናል ታይም መጽሔት ማርች 11፡2002 በቴክኖሎጂ አምዱ:: መጽሔቱ «MEET THE CHIPSONS» በሚል ርዕስ ባወጣው ዘገባ፤ እንዲህ በማት ይቀጥላል «ዴሪክ እናቱና አባቱ 'ቬሪ ቺፕ' የተባለ የኮምፒዩተር መሣሪያ በሰውነታቸው ውስጥ ለማስቀበር ፈቃደኛ የሆኑ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ነበሩ:: ከጥቂት ወራት በኋላ ዶክተሮች፣ በትልቅ ሰሪንጅ መሰል መሣሪያ፣ ጥቂት ኪሎባይት የምትይዝ የሲልከን ሚሞሪና በጣም ትንሽ የሬድዮ ማስተላለፊያ በሰዎች የቀኝ ክንድ ላይ በክትባት መልክ ማኖር ይጀምራሉ:: ይኼም የማንንም ሰው ጤንነት ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ ለመከታተል የሚያስችል መሣሪያ ነው:: በእርግጥ ይህን ሲሰሙ የሳይንስ ልቦለድ እየሰሙ ሊመስልዎ ይችላል፤ 'ቬሪ ቺፕ' ግን እውን የሆነ ነገር ነው:: የጀስኮብስ ቤተሰብም በኮምፒዩተር እገዛ የላቀ የሰው ፍጡሮችና የመጀመሪያው አዲስ ትውልድ ሊሆኑ ይችላሉ::*

*ዴሪክ እንደማንኛውም የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ጥሩ ሥነ ምግባር ያለው ልጅ ነው:: ለመጀመሪያ ጊዜ የ'ቬሪ ቺፕ'ን ቴክኖሎጂ የተመለከተው 'ቱዴይ' በሚባል ዝግጅት ላይ ሲተላለፍ እንደነበረ በደንብ ያስታውሳል:: 'ትልቅ ቴክኖሎጂ መስሎኝ ነበር ደግሞም ከዚያን ቀን ጀምሮ የዚህ ቴክኖሎጂ አካል የመሆን ፍላጎት አደረብኝ' ይላል፤ ቬሪ ቺፕን እንዴት እንደተዋወቀ ሲያስረዳ::*





*አንድ ቀን የዴክ እናት 'ከአፕላይድ ዲጂታል ሶሉሺን' ኩባንያ ምክትል ፕሬዝዳንት ከሆነው «ኬን ቦልተን» ጋር የምሳ ጊዜ እንዲኖራት ሁኔታዎችን አመቻቸች:: ምክንያቱም ከቬሪ ቺፕ ጀርባ ያለው ኩባንያ የእርሱ ነውና:: በወቅቱ ቦልተን ግን በነገሩ ላይ እምብዛም እምነት አልነበረውም፤ ዳሩ ግን 'ቬሪ ችፕን' ለሕዝብ ለማስተዋወቅ ከተሠራው የመጀመሪያው ማስታወቂያ በኋላ 25ሺ ሰዎች ቺፑ እንዲደረግላቸው እንደ ሚፈልጉ ሲያውቅ እጅግ ተደነቀ:: ከነዚህ ሰዎች መኻል ደግሞ የጄስኮብ ቤተሰብ 'ቬሪ ችፕ'ን ለመሞከር ከሁሉ ይልቅ ተመራጮች ሆነው ተገኝተዋል:: ምክንያቱም ዴክ፣ በተፈጥሮው ለአንቲባዮቲክ መድሃኒቶች አለርጂ ነው፤ የዴሪክ አባት ደግሞ በሌላ በሽታ የተጸከመ ሲሆን፣ በዚያ ላይ ከጥቂት ዓመታት በፊት ከባድ የመኪና አደጋ የደረሰበት ሰው ነው፤ በወቅቱ ደግሞ ራሱን እንኳ መግለጥ እስከማይችል ድረስ ሆኖ ነበር:: በወቅቱ በውስጡ 'ቬሪ ቺፕ' ተቀብሮለት ቢሆን ኖሮ፣ በድንገተኛ ክፍል ያገኘው ዶክተር በቀላሉ የተጎዳውን የሰውነት ክፍሉን ለማከም የሚያስችል መረጃ ለማግኘት ባስቻለው ነበር::*

*ቺፑን በቀዶ ጥገና በሰውነት ውስጥ ማስገባት በጣም ቀላል የሆነ ነገር ነው:: 'ሰባት ሰከንዶች ያኸል ቢፈጅ ነው' ይላሉ የኩባንያው ሜዲካል ዳይሬክተር «ዶክተር ሪቻርድ ሲሊንግ» ምናልባትም ያጋነኑት በጥቂቱ ብቻ ነው:: አንዴ ቀዶ ጥገና የተደረገበት ቦታ ከሻረ በኋላ ቺፑ እንደ ተቀበረ በፍጹም አይታይም:: ቦልተንም ሲናገሩ 'ወደ ቺፑ የሚገባም ሆነ ከቺፑ የሚወጣ ምንም ዓይነት ፈሳሽ የለም' ይላሉ::*

*አፕላይድ ሶሉሺን ኩባንያ የንግድ ምልክቱን 'ቺፕ አስደርግ' በሚል ሐረግ አጅቦ ለዚህች ትንሽ ዕቃ ትልቅ ዕቅድ ነድፎላታል:: ኩባንያው ከጥቂት ዓመታት በኋላ አሁን ባለው ቴክኖሎጂ ላይ፣ የደም ግፊት፣ የስኳር፣ እንዲሁም የሙቀት መጠንን የሚለኩ መሣሪያዎችን ለማከል አስቧል:: በተጨማሪም በማንኛውም ጊዜ አንድ ሰው የት እንደሚገኝ ለመከታተል የሚያስችል መሣሪያ በዚች ትንሽ ቴክሎኖጂ ላይ*

*ሊጨምር ይፈልጋል:: በአሁኑ ጊዜም ይኼን 'ዲጂታል መልአክ' የተሰኘ መሣሪያ በመሥራት ላይ ይገኛሉ:: መሣሪያው በጣም ትንሽና በሰውነት ውስጥ የሚቀበር እንደ መሆኑ፣ እጅግ ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል ተማምነውበታል::*

*የደኅንነት ጉዳይ ሌላው ከ'ቬሪ ቺፕ' ዓላማዎች አንዱ ነው፤ ኩባንያው፣ ካሊፎርኒያ ውስጥ ከሚገኝ ማረሚያ ቤት የሕግ ክፍል ጋር ከውሳኔ በፊት በቁም እስረኝነት ስለሚቆዩ ሰዎች ጉዳይ አንድ ስምምነት ተፈራርሟል:: ሲሊንግ እንደሚሉት 'ቬሪ ቺፕ' በሌባ ሊሰረቅ ወይም በተመሳሳይ ሊሠራ የማይቻል ስለሆነ እንደ መንጃ ፈቃድና ፓስፖርት ያሉትን መታወቂያዎች በሰው አካል ውስጥ በመቅበር ሊያገለግል ይችላል:: 'አሸባሪዎች ወደ ውስጥ አልፈው በአየር መንገዶች ላይ ጥቃት እንዳያደርሱ ለማድረግ ወይም አብራሪዎቹ ሕጋዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ 'ቬሪ ችፕ' በውስጣቸው ሊያስቀብሩ ይገባቸዋል በማለት ይሞግታሉ':: 'ለመሆኑ አብራሪዎችና የመንግሥት ባለሥልጣናት 'ቬሪ ቺፕ' ማድረጋቸው ተገቢነቱ ምን ያህል ነው?' ተብለው ሲጠየቁም፣ 'እኔ እንደሚመስለኝ ሁላችንም ይኼን የመጠየቅ መብት አለን፤ ምክንያቱም በበረራ ጊዜ ሕይወታችን በእጃቸው ውስጥ ስለምትሆን እነርሱ የበለጠ ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች ናቸውና' በማለት ይመልሳሉ:: 'በፌደሬሽን ኦፍ አሜሪካ' አንጋፋ ተመራማሪ የሆኑት 'ስቲቨን አፍተር ጉድ' ወደድንም ጠላንም ቴክኖሎጂው ፖሊሲው ላይ ተጽዕኖ ማምጣቱ አይቀርም::' በማለት፣ ለቴክኖሎጂው አስፈላጊነት አጽንኦት ይሰጣሉ::*

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ በየትኛውም ጊዜ የነበሩ አማኞች በእነሱ ዘመን ከተከሰቱ አንዳንድ ሁኔታዎች አንጻር ተነሥተው፣ ነገሩ «*እንዲህ ወይም እንዲያ ማለት ሊሆን ይችላል ብለው*» መጠርጠራቸው የሚበረታታ እንጂ የሚነቀፍ መስሎ አይታየኝም:: ይሁን እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶችን በተመለከተ፣ የተሟላ ማስረጃ በሌለበት ጉዳይ በተጋነነ እርግጠኛነት የሚቀርብ ትንታኔና ትምህርት አደገኛ ከመሆኑም ሌላ ታላቅ ውድቀት የሚያስከትል ነው:: በተለይም «እንዲህ ነው፤ ወይም ይሆናል» የተባለው ነገር እንደተተነበየው ባልሆነ ሰዓት፣ በተናጋሪው ላይ ከሚያስከትለው ሀፍረትና መሸማቀቅ ሌላ፣





የሚሰሙት ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ላይ ያላቸውን ተስፋና እምነት አደጋ ላይ የሚጥል ነው:: በዚያ ላይ ሰይጣን አመቺ ጊዜ እየጠበቀ ሰዎችን ሲያስት እንደኖረ የታወቀ ነው:: ደግሞም የእሱ የዘመን ሁሉ ትጋት ሰዎች ትንቢቶችን ችላ እንዲሏቸው ወይም እንዳይጠባበቋቸው ማጃጃል፣ ማጭበርበርና ማዘናጋት ነው:: ለዚህም እንዲረዳው ለዘመናት በአገልጋዮቹ በኩል የተለያዩ «መገለጦች» እና ትርጉሞችን ሲያቀርብ ነው የኖረው:: በዚህ ምክንያት በአሁን ዘመን ያሉ በርካታ «ክርስቲያኖች» የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶችን እንደ ተራ ተረት የሚመለከቱ አለያም መቼም እንደማይፈጸሙ የሚያስቡ ሆነዋል:: አንዳንዶችም በአንድ ወቅት የነበራቸውን ናፍቆት ጥለው፣ ቸልተኞች ሆነው ይታያሉ::

በእርግጥ ስለዚህ «666» ስለተባለው ጉዳይ፣ ከዚህ በፊት ብዙ እንደ ተባለ እናውቃለን:: በዚህ ምክንያት አሁን፣ አሁን ሰዎች ጉዳዩን ቸል እያሉት ከመሆኑ ሌላ አንዳንዶችም ስለዚህ ነገር ሲነገራቸው ተረትና አፈታሪክ የሚሰሙ እየመሰላቸው ነው:: ይኼም ለዓመታት በሰይጣን የተቀነባበረ ሴራ ውጤት እንደሆነ ማስታወስ እሻለሁ:: ስለዚህ እንደ ቤርያ ሰዎች በልብ ስፋት ነገሩን መመርመር መልካም ነው::

> ወዲያውም ወንድሞች ጳውሎስንና ሲላስን በሌሊት ወደ ቤርያ ሰደዱአቸው፥ በደረሱም ጊዜ ወደ አይሁድ ምኩራብ ገቡ፤ እነዚህም በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና። ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ።[146]

[146] ሐዋ17:10-11::

# ምዕራፍ ፳፩

## ታላቂቱ ባቢሎን [147]

ሃሌ ሉያ! በዝሙትዋ ምድርን ያጠፋችውን ታላቂቷን ባቢሉን ስለፈረደባት፣ የባሪያዎቹን ደም ከእጅዋ ስለተቀበለ፣ ፍርዶቹ እውነተኛና ጻድቅ ናቸውና ማዳን ክብርም ኃይልም የአምላካችን ነው

ሰባቱን ጽዋዎች ከያዙ መላእክት መኻል አንዱ ወደ ዮሐንስ ቀርቦ «ና በብዙ ውኃዎች ላይ የተቀመጠችውን የታላቂቱን አመንዝራ ሴት የቅጣት ፍርድ አሳይሃለሁ፤ የምድር ነገሥታት ከእርስዋ ጋር አመንዝረዋል፤ የምድር ነዋሪዎችም በዝሙትዋ ከእርስዋ ሰክረዋል» አለው:: ከዚህ በኋላ መልአኩ፣ ዮሐንስን በመንፈስ እየነዳ ወደ በረሀ ወሰደው፤ በራሱም ላይ የስድብ ስሞች ተጽፈውበት፣ ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች ባሉት ቀይ አውሬ ላይ የተቀመጠች አንዲትን ሴት አሳየው:: ሴቲቱ ሐምራዊና ቀይ ልብስ ለብሳ፣ በወርቅና በከበረ ድንጋይ፣ በዕንቁዎች ያሸበረቀች ስትሆን፣ በእጅዋም የሚያጸይፍ ነገርና የዝሙቷ እርኩሰት የሞላበትን የወርቅ ጽዋ ይዛለች:: በግንባርዋም ላይ «የአመንዝሮችና የምድር እርኩሰቶች እናት፣ ታላቂቱ ባቢሎን» የሚል ሚስጥራዊ ነገር ያለበት ስም ተጽፎ ነበር:: ሴቲቱም በቅዱሳንና በኢየሱስ ምስክሮች ደም ሰክራ ባያት ጊዜ ዮሐንስ እጅግ ተደነቀ፤ መልአኩ ግን «ስለምን ትደነቃለህ? የሴቲቱን ሚስጥርና እርስዋ የተቀመጠችበትን ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች ያሉትን የአውሬውን ሚስጥር እገልጥልሃለሁ፤ ያየኸው አውሬ ቀድሞ ነበር፤ አሁን የለም፤ በኋላ ከጥልቁ ጉድጓድ ይወጣል፤ ወደ ጥፋቱም ይሄዳል፤ ዓለም ሲፈጠር ጀምሮ ስሞቻቸው በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፉ የምድር ነዋሪዎች፣ አውሬው ቀድሞ የነበረ፣ አሁን የሌለ፣ በኋላ የሚመጣ መሆኑን ሲያዩ ይደነቃሉ» አለው::

ዮሐንስ፣ ሴቲቱን፣ የተቀመጠችበትን አውሬና የቀረውን ሚስጥር ሁሉ ለመረዳት፣ ጥበብ ያለው አእምሮ እንደሚያስፈልግ ተናግሯል::

[147] ራእይ ምዕራፍ 17 እና ምዕራፍ 18 በጠቅላላ::





ይሁን እንጂ ሰባቱ ራሶች፣ ሴቲቱ የተቀመጠችባቸው ሰባት ተራሮች መሆናቸውንና እነሱም ሰባት ነገሥታት እንደሆኑ ገልጧል:: ዮሐንስ በተመለከተበት ዘመን ከእነሱ መኻል አምስቱ ወድቀው፣ አንዱ ብቻ ነው የነበረው፤ ሌላው ግን ገና አልመጣም፤ በሚመጣበት ወራትም ቢሆን ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው የሚቆየው፤ ስምንተኛው ንጉሥ ደግሞ ቀድሞ የነበረውና ያኔ የሌለው አውሬ ሲሆን፣ እሱም ከሰባቱ አንዱ ነው፤ በጊዜው ሲገለጥም ወደ ጥፋቱ ፈጥኖ ሊሄድ ነው::

በራእይ መጽሐፍ አስራ ሰባተኛና አስራ ስምንተኛ ምዕራፍ ላይ እንደ ሚታየው፣ ከጥንት ጀምሮ እስከዚያን ጊዜ ድረስ፣ ባቢሎን የዓለምን ፖለቲካ፣ ንግድና ሃይማኖት በስውርና በግልጥ ስትመራ እንደኖረች እንረዳለን:: ደግሞም በተለያየ ዘመን በነበሩ ነገሥታትና ልዩ፣ ልዩ ሕዝቦች ውስጥ በኃይል ስትገለጥ የኖረች ከመሆንዋም ሌላ፣ የዓለም መንግሥታትም በእርሷ ላይ ተቀምጠው ሲቀማጠሉና ሲያመነዝሩ ነው የኖሩት:: በውኃዎች ላይ የመቀመጧ ሚስጥርም ይኼው ነው:: ከዚህ አንጻር ባቢሎን፣ በአንድ ስፍራ የተወሰነች ሳትሆን፣ በየዘመናቱ መልኳን እየቀያየረች፣ በሁሉም ቋንቋ፣ ወገንና ሕዝብ ላይ ሠልጥና የቆየች መሆኗን መገንዘብ ያሻል:: በምድር ለተከሰተ ማንኛውም ዓይነት ኃጢአትና ምግባረ ብልሹ ሥርዓት ሁሉ ምንጭና መጀመሪያ በመሆንዋ የአመንዝሮችና የምድር ርኩሰቶች እናት ተብላለች::

እስከ ዛሬ በምድር የታዩ ልዩ፣ ልዩ ሃይማኖቶች፣ የዚህችው የሐሰት ሁሉ ምንጭ ከሆነችው ባቢሎን የተገኙ በመሆኑ በእርሷ ሚስጥራዊ አሠራር ተጽዕኖ ስር ወድቀዋል:: ዝሙትዋ የሞላበትን፣ የወርቅ ጽዋ መያዝዋም ለዘመናት ዓለምን ሁሉ በእርኩሰት፣ በውሸትና በስህተት አሠራር ተብትባ፣ በማታለል እንደኖረች ይጠቁማል:: የባቢሎን መንፈስ አሠራር ከላይ ሲያዩት በሚያምርና በሚያጓጓ ወርቅ የተለበጠ፣ ውስጡ ግን አጸያፊና የከረፋ ነገር የሞላበት አሠራር ነው:: ሴቲቱ የለበሰቻቸው ሐምራዊና ቀይ ቀለም ያላቸው አልባሳት በዮሐንስ ዘመን የነበሩ ነገሥታትና ካሕናት ይለብሷቸው የነበሩ ናቸው፤ ሴቲቱም በነዚህ ልብሶች አሸብርቃ መታየቷ፣ ከነገሥታቱና ከሃይማኖት መሪዎች ጋር ያላትን ጥብቅ ቁርኝት የሚገልጥ ነው::

በወርቅ በእንቁና በከበሩ ድንጋዮች መሸለሟም ከምድር ንግድና የገንዘብ ዝውውር ጋር ያላትን ጽኑ ጥምረትና ቅንጅት ያስረዳል።

በቀዩ ዘንዶ ላይ የመጋለቧ ሚስጥርም ለዘመናት በሰይጣን ኃይል፣ ጉልበትና አቅም እንደኖረች የሚገልጥ ነው። ምንም እንኳ የማታ ማታ ዘንዶው እጅግ ቢያቃልላትም ለዘመናት ግን ዋነኛ ተባባሪውና አጋሩ አድርጎ ተጠቅሞባታል። የዚህ ቀይ ዘንዶ ማንነት በአስራ ሁለተኛው ምዕራፍ የተገለጠው ነው። እርሱም ከዘመናት በፊት ጀምሮ በእርስዋ ላይ እየጋለበ ወደ ፍጻሜው ይቸኩላል።

ደግሞም በዚህም ሆነ በሌሎች ክፍሎች እርሷ ዘመንዋን ሙሉ ጸረ እግዚአብሔር የሆነ አቋም ስታራምድ እንደ ኖረች በግልጥ ይታያል። እንዲያውም ለእግዚአብሔር ወዳጅ የሆኑትን ስታሳድድ፣ ስትገድልና ስታሰቃይ በመኖርዋ በደም እስክትሰክር ድረስ ሆናለች። በቅዱሳንና በኢየሱስ ምስክሮች ደም ሰክራ የመታየቷ ምስጢርም ይኼው ነው። ነገር ግን አንድ ቀን የጠጣችው ደም ከአቅሟ በላይ ሆኖ ያሰክራትና አንገዳግዶ ይጥላታል። የዚያን ጊዜም ፍጻሜዋ ይሆናል። ምንም እንኳ የዓለምን ንግድ፣ ፖለቲካና ሃይማኖታዊ ሥርዓት ለእውነትና ለፍትህ እንዳይመች አወሳስባ፣ እንደወደደች ስትቃኘው ብትኖርም፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ፍጻሜዋ እንዲህ ተቀጥሮላታል። ዮሐንስም የጋለሞታዋ ባቢሎን ፍርድ በተከናወነ ጊዜ «ሃሌ ሉያ! በዝሙትዋ ምድርን ያጠፋችውን ታላቂቱን ባቢሎን ስለተፈረደባት የባሪያዎቹን ደም ከእጅዋ ስለተቀበለ፣ ፍርዶቹ እውነተኛና ጻድቅ ናቸውና ማዳን ክብርም ኃይልም የአምላካችን ነው» የሚል እንደ ብዙ ውኃዎች ባለ ድምፅ የሚቀርብ ምስጋናና አምልኮ ለአንዱ አምላክ ሲቀርብ፣ እንዲሁም በሰማይና በምድር ታላቅ ደስታ ሲሆን፣ የተመለከተው ከዚህ በኋላ ነው። በአንጻሩ በዚያን ጊዜ ከእርስዋ ጋር ያመነዘሩ የምድር ነገሥታትና ነጋዴዎች እጣ ፋንታም ልክ እንደ እርስዋ ይሆናል። ምንም እንኳ ከላይ ስትታይ ለዘላለም፣ ጸንታ የምትኖር ብትመስልም ከእግዚአብሔር ዘንድ ከምትቀበለው የበቀል ቅጣትና ፍርድ ግን ማንም ሊያድናት አይችልም። ከዚህ የተነሣ የምድር ነገሥታት፣ ነጋዴዎችና የሃይማኖት መሪዎች በድንገት የሆነባትን ጥፋትና መአት እያዩ ይገረማሉ፣ ያዝናሉ፣ ይጮኻሉ።





«ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፤ ወደቀች . . .»

ሴቲቱና አውሬው ኅብረታቸው ሚስጥራዊ በመሆኑ የዓለምን ንግድ፣ ፖለቲካና ሃይማኖት በምን ዓይነት መንገድ ይቆጣጠሩ እንደነበር ግልጥ አልነበረም። ሆኖም በፍጻሜው ዘመን የሚገለጠው አውሬ ቀድሞ የነበረ እንጂ ድንገት የሚከሰት አይደለም። ጻሩ ግን አንድ ጊዜ ላያዳግም ከጥልቁ ይወጣ ዘንድ አለው። በወቅቱም ስሞቻቸው በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፈ ሰዎች ሁሉ ይሰግዱለታል። ለዘመናት ማንም በማይጠረጥረው መንገድ ሲሠራ ቆይቶ፣ ከአስሩ የቃል ኪዳን ኅብረት አገሮች ጋር በመሆን መንግሥቱን በምድር ላይ በመሠረተ ጊዜ ለዘላለም የሚንሰራፋ ይመስለዋል። አስሩ ነገሥታት ተመሳሳይ አሳብ አላቸው፤ እነርሱም ኃይልና ሥልጣናቸውን ለእርሱ ያስረክቡና ከበጉም ጋር ጦርነት ያደርጋሉ። በጉም፣ የነገሥታት ንጉሥ፣ የጌቶች ጌታ ስለሆነ ድል ይነሣቸዋል፤ ከበጉ ጋር ያሉትም፣ የተመረጡና የታመኑም ስለሆኑ አብረው ድል ይነሣሉ።

አመንዝራይቱ ሴት የተቀመጠችባቸው ውኃዎች፣ ሕዝቦች፣ ወገኖችና ቋንቋዎች ናቸው። በመጨረሻው ዘመን ግን አውሬውና አስሩ ነገሥታት፣ አመንዝራይቱን ሴት ፈጽሞ ይጣሏታል፤ ወደ ጥፋትዋም ያጣድፏታል፤ ራቁቷንም ያስቀሯታል፤ ሥጋዋንም ይበላሉ፤ በእሳትም ያቃጥሏታል። ዕቅዱን እንዲፈጽሙ ይኼን አሳብ በልባቸው ያደረገ እግዚአብሔር ራሱ ነው፤ ስለዚህ ቃሉ እስኪፈጸም ድረስ እነርሱ በአንድ አሳብ ይስማማሉ።

ሆኖም «ይህቺ ሴት ማን ናት?» ለሚለው ጥያቄ ዮሐንስ የሚሰጠው መልስ አንድ ብቻ ሲሆን፣ እርሱም «በምድር ነገሥታት ሁሉ ላይ የምትነግሥ ታላቂቱ ከተማ ናት» የሚል ነው።

## ባቢሎን
## ማን ትሆን?

> በእርስዋም ውስጥ የነብያትና የቅዱሳን
> ደም፣ በምድር የታረዱ ሁሉ ደም ተገኘበት[148]

ይህቺ በምዕራፍ አስራ ሰባት መጀመሪያ ላይ የተጠቀሰችው ሴት በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ ከተገለጡ ሁለት ሴቶች አንዷ ናት:: በምዕራፍ አስራ አንድ ላይ የታየችው ሴት እስራኤል መሆንዋን አስቀድመን የተገነዘብን ሲሆን፣ እግዚአብሔር እጅግ እንዳከበራትና በመጨረሻው ዘመንም ጽኑ ጥበቃ እንደሚያደርግላት ተረድተናል:: በአንጻሩ በዚህ ክፍል የተጠቀሰችው ሴት ጋለሞታና የተዋረደች ስትሆን፣ ፍጻሜዋም በውርደትና በውድመት የሚጠናቀቅ ነው:: ምንም እንኳ እንደ ሌሎች ትንቢቶች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ዘንድ ስለዚች ሴት ማንነት ጉዳይ አንድ ዓይነት አመለካከትና መረዳት ባይኖርም፣ «ሴቲቱ» በመጨረሻው ዘመን በምድር ላይ ለምትገለጥ ለአንዲት ታላቅ የዓለም ከተማ የተሰጠች ስዕላዊ ምሳሌ እንደሆነች ብዙዎች ይስማማሉ:: ከተማዋ የተገለጠችባቸው ባሕርያት ከጥንቷ ባቢሎን መገለጫ ባህርያት አንጻር መታየት እንደሚገባውም ይታመናል::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ባቢሎን» የሚለው መጠሪያ የሚገኘው ከፍጥረት መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፎች ጀምሮ ነው:: በዚያን ጊዜ የነበረችው ባቢሎንም «ናምሩድ» በሚባል ሰው መሪነት ትገዛ የነበረች ስትሆን፣ ለመጀመሪያ ጊዜም በእግዚአብሔር ላይ የተደራጀ ዐመጽ ያደረገች ከተማ በመሆን ትታወሳለች:: ከዚህም ሌላ ባቢሎን፣ ከአንዱ አምላክ በተጨማሪ ሌሎች ብዙ አማልክትን ማመንንና የጣኦት አምልኮን ለዓለም ያስተዋወቀች ከተማ ናት:: ከዚህ የተነሣ እስከ አሁንም ድረስ በእውነተኛው እምነት ጥላ ስር ሆነው፣ ጳሩ ግን ለሐሰት እምነት መገለጫዎች በመሆን እያገለገሉ ላሉ ለልዩ፣ ልዩ

[148] ራእ18:10:17:19:: ራእ18:24::





የአምልኮ ሥርዓቶች ምንጭ በመሆን ትጠቀሳለች:: ከእነዚህም መኻል በተለይ የእናትና የልጅ አምልኮ፣ ለተለያዩ ቅዱሳን ምስል ስግደት፣ የበዓላት አከባበርና የመሳሰሉትን ማንሣት ይቻላል::

በሌላም በኩል ባቢሎን የሰው የመግባቢያ ቋንቋ የተደባለቀባት ከተማ እንደ መሆኗ መጠን አሁን ላለው ዘረኝነትና አክራሪ ብሔርተኝነት ያደረገችው አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: እንዲሁም የከተማ ግንባታና የሕዝብ አስተዳደር ለመጀመሪያ ጊዜ በሥራ ላይ የዋለው በዚህችው ጥንታዊ ከተማ ነዋሪዎች እንደሆነ ይነገራል:: ከዚህ ሌላ በናቡከደነፆር ዘመን የነበረችው ባቢሎን፣ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ያፈረሰችና የተስፋውን ሕዝብ ከአገሩ አፈናቅላ በግዞት ያኖረች መሆኗን መዘንጋት የለብንም:: አብርሃም የተባለው የእምነት አባት አስቀድሞ ተጠርቶ የወጣው ከዚህቺው ከተማ አካባቢ ሲሆን፣ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በየትኛውም ጊዜ በተከሰተው የዓለም ታሪክ ውስጥ ሁነኛ ስፍራ ያለው ነው:: ዛሬም እንኳ የዓለም የፖለቲካ፣ የሃይማኖትና የኢኮኖሚ የልብ ትርታ የሚገኘው፣ አብርሃም ተጠርቶ ከወጣበት እስከ ደረሰበት ባለው ስፍራ ተለክቶ መሆኑ፣ ስፍራውን በተለየ ሁኔታ እንድናየው ያደርገናል::

ከእነዚህ እውነታዎች በመነሣት በራእይ መጽሐፍ ላይ የተጠቀሰችው ባቢሎን ምሳሌነቷ፣ በመጨረሻው ዘመን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የሃይማኖት ማዕከል በመሆን ሁነኛ ስፍራ ለሚኖራት አንዲት የዓለም ከተማ እንደሆነ ይታሰባል:: ስለዚህም የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶችን የሚያጠኑ ሰዎች፣ ሁኔታውን አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታና ከታሪክ አንጻር እያመሳከሩ ከዓለማችን ታላላቅ ከተሞች መኻል *«እሷሌ የምትሰኘዋ ከተማ ናት»* በማለት ሲያስተምሩ ቆይተዋል:: ከእነዚህም መኻል ሮም፣ ባግዳድ፣ ኒዮርክ፣ ኢየሩሳሌም፣ ብራስልስ. . . የተሰኙት፣ ተደጋግመው ከሚጠቀሱ ከተሞች ቀዳሚዎቹ ናቸው::

ለምሳሌ ይህቺ በአውሬው ላይ ተቀምጣ የታየችው ሴት፣ ወይም «ባቢሎን» የተሰኘችው ከተማ «ሮም» እንደሆነች አስረግጠው የሚናገሩ ሰዎች፣ ይኼን ለማለት የቻሉበትን ምክንያት ሲያስረዱ፣ ከተማዋ

የተመሠረተችባቸውን ሰባት ተራሮች በዋቢነት ይጠቅሳሉ:: እነዚህ ፓላንቲን፣ ካፐቶሊን፣ አቬንቲን፣ ቪሚናል፣ ኩሪናሊን፣ ኢስኩሊን፣ ካኤሊቶን የተሰኙ ተራሮችም፣ ከስያሜአቸው ጀምሮ ከነገሥታቱ ጋር ጥብቅ ቁርኝት አላቸው ብለው ያምናሉ:: ሌሎች ደግሞ ምንም እንኳ ከተማዋ ሮም እንደሆነች ቢቀበሉም ትንቢቱን ለመተርጎም ከተራሮቹ ይልቅ ትኩረት የሚያደርጉት፣ በተለያዩ ዘመናት ነግሠው ዓለምን በገዙ የሮም ነገሥታት ላይ ነው:: በመሆኑም ከክርስቶስ ዘመን እስከ ዮሐንስ የመጨረሻ ዓመታት ድረስ የነበሩትን የሮም ቄሳሮች በመቁጠር «ተራሮች» የተባሉት እነዚሁ ነገሥታት እንደ ሆኑ ያስረዳሉ:: ከእነዚህም ነገሥታት መኻል፣ ጁሊየስ ቄሳር፣ ጢባሪዎስ ቄሳር፣ ካሊጉላና ኔሮ፣ አምስቱ ሲሆኑ፣ በዮሐንስ ዘመን አልፈው ነበር፤ ከነርሱ ተከትሎ የነገሠውና ዮሐንስ ራእይውን ባየበት ዓመት የነበረው ቄሳር ዶሚታን ስድስተኛው ነው:: ወደፊት ከሮም መታደስ ጋር የሚመጣው የአስሩ ነገሥታት ኅብረት ሰባተኛ ሲሆን በነርሱ ላይ የሚሾመው ሰውም እርሱ ስምንተኛው እንደሚሆን ያምናሉ::

በሌላኛው ወገን ያሉ ተርጓሚዎች ደግሞ *«ሴቲቱ ምሳሌ የሆነቻት ከተማ ማንም ትሁን ማን፣ የተቀመጠችባቸው ተራሮች ግን፣ ግልጽ ስለሆኑ ሌላ ምስጢር አያስፈልገውም»* የሚሉት ናቸው፤ እንደነዚህ ሰዎች እምነት ከሆነ፣ «ተራሮች» የተባሉት፣ ነገሥታት መሆናቸው በግልጥ በመታወቁ፣ ከዚህ በፊት ስማቸው ገናና የነበሩና ከእስራኤል ጋር ሁነኛ ትስስር የነበራቸውን ነገሥታትን የሚመለከቱ እንደ ሆኑ በእርግጠኛነት ያስረዳሉ:: ነገሥታቱም ለዘመናት የእስራኤል ሁነኛ ጠላት ሆነው በመኖራቸው ሕዝቡን ያሳደዱና ያሰቃዩ፣ ከአገራቸውም ያፈናቀሏቸውን መንግሥታት ናቸው:: ይህ እንዲህ ከሆነ ደግሞ «አልፈዋል» የተባሉት አምስቱ መንግሥታት፣ ግብጽ፣ አሦር፣ ባቢሎን፣ ፋርስና ሜዶን እንዲሁም ግሪክ ሲሆኑ፣ በዮሐንስ ዘመን የነበረችው ሮማ ደግሞ ስድስተኛዋ ትሆናለች፤ ነገር ግን ሮም ከአስሩ ነገሥታት ጋር እንደገና በታደሰች ጊዜ ሰባተኛ ሆና የምትቆጠር ሲሆን፣ ከሮም ጋር አብሮ የሚወጣውና እርሷም በላይዋ የምትሾመው «መሪ» ስምንተኛ ሆኖ ይገለጣል፤ ማለት ነው::





ከዚህ በተለየ «ፓትሪክ ሄሮን»[149] የተባለ ጸሐፊ በቅርብ ጊዜ ባሳተመውና ስለመጨረሻው ዘመን በሚያወሳው መጽሐፉ «ባቢሎን» ስለተሰኘችው ከተማ የራሱን ለየት ያለ አስተያየት ጽፏል:: ይኸም ሰው ሴትየዋ የአንድ ከተማ ምሳሌ መሆንዋን አምኖ ቢቀበልም፣ ከተማዋ፣ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያላትና በራእይ መጽሐፍ አስራ ሰባተኛና አስራ ስምንተኛ ምዕራፎች ላይ ያሉትን መስፈርቶች ሁሉ የምታሟላ ከተማ መሆን ስለሚገባት «ሮም ናት» በሚለው አሳብ ፈጽሞ አይስማማም:: ሰውየው *«ገና ለገና ባቢሎን ስለተባለ ብቻ ባግዳድን ወይም እዚያ አካባቢ ያሉ አገራትን ብቻ ማሰብ የለብንም»* በማለት በጽኑ ይሞግታል:: ከዚያ ይልቅ መልክአ ምድራዊ አቀማመጧንና ባሕርይዋን ብንመረምር ማንነቷን ለመረዳት ቀላል እንደሚሆንልን ይናገራል:: ስለዚህ አንድ ሰው፣ ከተማዋ ልታሟላ የሚገባትን ዋና ዋና መስፈርቶች ማወቅ ከፈለገ፣ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ የተለየ ትኩረት ማድረግ እንዳለበት ያሰምርበታል::

በእርግጥ ከተማዋ በሚመጣው ዘመን፣ በዓለም ላይ ሁነኛ ተጽእኖ የምትፈጥር ከሆነ፣ በአሁኑ ጊዜ ጭምር በዓለም ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ሃይማኖት፣ ጉልህ ስፍራ ያላት መሆን ይገባታል ይላል:: በመሆኑም ለማንነቷ መገለጫ ሆነው ከተገለጡት መሠረታዊ ባሕርያት መኻል ዋና ዋናዎቹን እየነቀሰ ለመተንተን ይሞክራል:: በዚሁ መሠረት ከተማዋ የወደብ ከተማ እንዲሁም የዓለም የንግድና የገንዘብ ማዕከል ከመሆንዋም በላይ ታላላቅ ህፃዎች ያሉባት ብርቱ ከተማ መሆን ይጠበቅባታል[150] ብሎ ያምናል:: በተጨማሪም በራእይ መጽሐፍ እንደ ተገለጠው፣ የዓለም ነጋዴዎች ከእርስዋ ጋር ለዘመናት ጽኑ የንግድ ቃል ኪዳንና ትስስር የነበራቸውና በእርስዋ ምክንያት ትርፋማና ባለጠጋ እንደሆኑ በግልጥ መታየት ይገባዋል:: ባቢሎን ሁሉ ነገር የሚሸጥባት የዓለም የንግድ መዳረሻና የሸቀጦች ሁሉ ማራገፊያ ናት:: በዚህም ምክንያት ስትቃጠልና ስትወድም ከማንም ይልቅ አምርረው የሚያዝኑትና የሚደነግጡት የምድር ሀብታም ነጋዴዎች መሆናቸው

[149] The Return of Antichrist by- Patric Heron

[150] ራእ18:10:: አንቺ ታላቂቱ ከተማ ወዮውልሽ! አንቺ ባቢሎን ብርቱይቱ ከተማ፣ ...

ተመልክቷል[151] ደግሞም ከተማዋ የልዩ፣ ልዩ አገሮችን ቋንቋና ባህል በአንድ ላይ የያዘች መሆን አለባት ይላል፤ ምክንያቱም ዮሐንስ፣ ሴቲቱን አይቶ በገለጣት ጊዜ በልዩ ልዩ ቋንቋና ሕዝቦች ላይ ተቀምጣ ስላያትና ይህም መፈጸም ስላለበት ነው:: ከዚህ ሌላ ከተማዋ የሐሰተኛው መሪ ርዕሰ መዲና ለመሆን ትችል ዘንድ የመንግሥታት መቀመጫ መሆን ይገባታል፤ ይላል:: ከሁሉም በላይ ይህቺ ከተማ የዓለም የዝሙትና የእርኩሰቶች ሁሉ ምንጭና መናኸሪያ መሆንዋ ሌላው ለእርሷነቷ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ነው:: በማለት አሳቡን ያጠናክራል::

እንግዲህ «ፓትሪክ ሔሮን» ከነዚህ ሁሉ ምልክቶች በመነሣት በአሁኑ ጊዜ ስለባቢሎን የተነገረውን የትንቢት ቃል በጠቅላላ የምታሟላው «ኒው ዮርክ ሲቲ» ለመሆንዋ እርግጠኛ ሆኗል:: በእርግጥ ከተማዋን ደኅና አድርገው ሲመለከቷት ከላይ የተጠቀሱትን ዝርዝር ጉዳዮች ሁሉ የምታሟላ መስላ ትታያለች:: ከተማዋ የወደብ ከተማ ከመሆንዋ ሌላ የዓለም ዋነኛ የንግድ መዳረሻ ናት፤ እንደሚባለውማ ከጠቅላላው የአሜሪካ ኢኮኖሚ ጋር ሳይደመር እንኳ የኒው ዮርክ ኢኮኖሚ ብቻውን ከብዙ የዓለም ባለጠጋ አገሮች ኢኮኖሚ ይበልጣል:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሚወጡ መረጃዎች፣ አሜሪካ ከዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ ብዙ እጅ ድርሻ እንዳላት የሚያመለክቱ ናቸው:: ስለዚህ የአሜሪካ ኢኮኖሚ አይደለም ሙሉ ለሙሉ ተሽመድምዶ፣ ትንሽ ጉንፋን ሲይዘው፣ በእነርሱ ብሶ የሚያስነጥሱ የዓለም መንግሥታት ቁጥራቸው ቀላል አይደለም:: በተጨማሪም ብዙ የዓለም ሀብታሞች በ«ዎል ስትሪት» የአክሲዮን ገበያ ምክንያት ባለጠጋ ሆነዋል:: ደግሞም ኒው ዮርክ የብዙ ሕዝቦችና ቋንቋዎች መናኸሪያ በመሆን በዓለም ላይ የሚወዳደራት ያለ አትመስልም:: ብዙ ታላላቅና ውብ ህንፃዎች የሚገኙባት ኒው ዮርክ የዚያኑ ያህል የእርኩሰትና የነውር ከተማ መሆንዋ ይነገርላታል:: በተጨማሪም ከተማዋ የታላላቅና የዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ዋና ቢሮ መቀመጫ ከመሆንዋም ሌላ፣

[151] ራእ18:3:: ራእ18:11::





የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት የሚገኘው በዚችው ከተማ መሆኑ ይታወቃል:: ምን ይኼ ብቻ፣ በተባበሩት መንግሥታት ጥላ ስር ያለውና በ1998 የተመሠረተው[152] «የዓለም ሃይማኖቶች አንድነት» የተሰኘው ድርጅት የሚገኘው እዚያው ነው:: በእርግጥ ወደፊት አቅሙ ምን ያህል ሊፈረጥም እንደሚችል ባይታወቅም ድርጅቱ የተባበሩት መንግሥታት አካል ሆኖ የተቋቋመው በዓለም ባሉ የሃይማኖት ድርጅቶች መኻል ያለውን አለመግባባትና አክራሪነትን ለመከላከል እንደ ሆነ ሊታወቅ ይገባል::

እንግዲህ ከእነዚህና እነዚህን ከመሳሰሉ ሌሎች ምክንያቶች የተነሣ እንደ ፓትሪክ ሄኖን ያሉ ሰዎች «ባቢሎን» የተባለችው ከተማ፣ ኒው ዮርክ መሆንዋን በእርግጠኛነት ይናገራሉ:: ሌሎች ደግሞ «አይደለም ሮም ናት» ሲሉ፣ አንዳንዶች ኢየሩሳሌም ስለመሆንዋ ይሞግታሉ፤ እንዲሁም የተወሰኑ ሰዎች ለመካከለኛው ምሥራቅ ያላትን ቀረቤታና የንግድ ማዕከል መሆንዋን በመጥቀስ ከተማዋ ዱባይ እንደምትሆን ሲገምቱ፣ ሌሎች ደግሞ የአውሮፓ ኅብረት መቀመጫነቷን ከግምት ውስጥ በመከተት ብራስልስ ልትሆን እንደምትችል የሚናገሩ አሉ:: እንደዚሁም ትንቢቱን በቀጥታ በመተርጎም የጥንትዋ ባቢሎን የምትገኝበት ስፍራ ላይ ያለችው ኢራቅ በመሆንዋ ባግዳድ መሆን አለባት ብለው ይከራከራሉ፤ የዛሬን አያድርገውና «ባግዳድ ናት» የሚለው አመለካከት በተለይ በሳዳም ሁሴን የሥልጣን ዘመን ተአማኒነቱ ከፍ ብሎ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው::

ያም ሆነ ይህ፣ ብዙ ሰዎችን የሚያስማማ አንድ እውነት ግን አለ፤ ይኸውም ዓለምን ወደ መጨረሻዋ ከሚያፋጥኗትና በቀሩት ወራት መሆን ከሚገባቸው መሠረታዊ ነገሮች በተለይ ሦስቱ የግድ መሆን እንዳለባቸው ነው:: እነዚህ ነገሮች በፍጥነት መፈጸም በሚጀምሩበት ዘመን ትንቢቶቹን ለመረዳት ያን ያህል አስቸጋሪ ላይሆን ይችላል:: በዚህም መሠረት ዓለም ወደመጨረሻው በተቃረበች ጊዜ ከሚኖራት ነገር የመጀመሪያው፣ አንድ የዓለም ርዕዮትና መንግሥት ሲሆን፣

[152] United Religions incentive

<u>ሁለተኛው አንድ የኢኮኖሚ ሥርዓት ነው፤ ሦስተኛው ደግሞ አንድ የዓለም ሃይማኖት ወይም እምነትና አምልኮ መሆኑ መታወቅ አለበት።</u> ደግሞም በዘመናት ሁሉ እነዚህ ነገሮች ባልተሟሉበት ሁኔታ ዓለምን አንድ አድርጎ መግዛትና ማስተዳደር ፈጽሞ እንደ ማይቻል በተደጋጋሚ ተፈትኖ ታውቋል። ከዚህ አንጻር የባቢሎን ሕልውናና መገለጥ በዚሁ የመጨረሻው ዘመን ክስተት ላይ የተመሠረተ ሆኖ ይታያል።

እርግጥ ነው፣ ከላይ በተጠቀሰው ክፍል ሴቲቱ፣ በምድር ነገሥታት ሁሉ ላይ የምትነግሥ ታላቂቱ ከተማ ስለመሆኗ ተነግሯል፤ እርሷም በመጨረሻው ዘመን ውስጥ ለዓለም የፖለቲካ፣ የንግድና የሃይማኖት ማዕከል ሆና የምትገለጥ ከተማ ናት፤ ፍጻሜዋም በአንድ ሰዓት ሲሆን፣ ጥፋትዋም አስደንጋጭ እንደሚሆን ተመልክቷል። እንደ ፓትሪክ ሄሮን ያሉ ሰዎችም ጉዳዩን ከኑክሌር ጦርነት ጋር በማያየዝ ባቢሎን በኑክሌር አረሮች ልትወድም እንደምትችል ይገምታሉ። ማን ያውቃል? ዳሩ ግን ይህቺ ከእግዚአብሔር ዘንድ አስቀድሞ ፍርዷ የተነገረላት ከተማ፣ ባግዳድ ትሆን? ሮም? ዱባይ? ወይስ ኢየሩሳሌም? ኒው ዮርክ ናት? ወይስ ብራስልስ? ለሚለው ጥያቄ፣ አሁን ባለንበት ዘመን እርግጠኛ ሆኖ ስፍራውን ማመልከት አስቸጋሪ ይመስለኛል፤ ሆኖም የባቢሎን መንፈስ አሠራር በዓለም ፖለቲካ፣ ንግድና ሃይማኖት ላይ በሚስጥር እየሠራ ስለመሆኑ ግን አንዳች ጥርጣሬ አይግባችሁ። በመጨረሻው ዘመን መዛግብቶቿ ሲፈተሹ የሚገኘውም ይኼ ብቻ ነው።



# መጽሐፍ ፭

# እስራኤል፣ አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ

**በዚያች አገር ጥላ ስር!**

## መግቢያ

*አንድ ሀብታም፣ ለቆየ ወዳጁ «የትኛው ይሻልሃል? ዛሬውኑ አምስት ሳንቲም በመስጠት ጀምሬ፣ ነገ ደግሞ እጥፉን አስር ሳንቲም፣ ከነገ ወዲያም የዚያን እጥፍ አድርጌ ሃያ ሳንቲም፣ በአራተኛው ቀን አርባ ሳንቲም፣ በአምስተኛው ቀን ሰማኒያ ሳንቲም . . . እያደረኩ ለአንድ ወር ያህል በዚህ ስሌት መሠረት ገንዘብ ልስጥህ? ወይንስ ነገውኑ በአንድ ጊዜ አንድ መቶ ሺ ብር ብሰጥህ ይሻልሃል?» ብሎ ጠየቀው:: ያም ሰው ብዙም ሳይመራመር «ኧረ ዛሬውኑ አንድ መቶ ሺ ብር ብትሰጠኝ ይሻለኛል» ሲል የሚሻለውን ተናገረ:: ነገር ግን ሰውየው ሒሳቡን ረጋ ብሎ ሲያሰላው ምርጫው ስህተት እንደነበር አወቀና እጅግ ቆጨው:: ምክንያቱም በየቀኑ ታግሶ አንድ ወር ድረስ ቢዘልቅ ኖሮ ከአምስት ሳንቲም የተነሣችው ጥቂት ገንዘብ የሌላውን ቀን ሳይጨምር በሠላሳኛው ቀን ብቻ፣ ሃያ ስድስት ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ ሦስት ሺ አምስት መቶ አርባ ስድስት ብር /26,843,546/ ልትሆንለት ትችል ነበርና ነው::*

ይህ የሒሳብ ስሌት፣ ባለንበት ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች እንዴት ባለ ፍጥነት እየተፈጸሙ እንደ ሆነ ለማስረዳት ቀላል ምሳሌ ይመስለኛል:: በእርግጥ ስለጌታ ኢየሱስ ዳግም ምጽአትና ስለዘመን ፍጻሜ ከተነገሩ ትንቢቶች አብዛኛዎቹ ተፈጽመዋል:: የቀሩትም በፍጥነት ከሚቀያየረው ዓለም ጋር ወደ ፍጻሜአቸው እየገሰገሱ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉ ትንቢቶችን በጥልቀት የመረመሩ ሰዎች እንደሚናገሩት፣ ስለመሲሁ የመጀመሪያ መምጣት በመቶ የሚቆጠሩ ትንቢቶች ተነግረው የነበረ ሲሆን፣ ሙሉ ለሙሉ ተፈጽመዋል:: ስለዳግም ምጽአቱም ከመጀመሪያው ከስምንት እጅ በላይ የሆኑ ትንቢቶች ተጽፈው የነበረ ቢሆንም፣ በአሁኑ ጊዜ አብዛኛዎቹ ተፈጽመው የቀሩት እጅግ በጣም ጥቂት ብቻ ናቸው::

በዚያ ላይ ባለንበት ዘመን በትንቢቶቹ አፈጻጸም የጊዜ ስሌዳ ላይ የሚደንቅ ፍጥነት እየታየ ነው:: ካለፈው ጋር ሲነጻጸር በቀደሙት ዘመናት የትንቢቶቹ ፍጻሜ አዝጋሚ መስሎ ይታይ የነበረ ሲሆን፣ በዛሬው ጊዜ ግን ለማሰብ እንኳ ከባድ የነበሩ ትንቢቶች እንደ ቀላል





ነገር ሲፈጸሙ እየታዩ ነው:: ይህም ለትንቢቶቹ መፈጸም ጉልህ አስተዋጽኦ ባለው የዓለምና የምድር ሥርዓት ላይ የሚንጸባረቅ ሆኗል:: ለምሳሌ ዛሬ በዓለም ሁሉ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ውጤቶች ቶሎ ቶሎ የሚቀያየሩና ዕድገታቸውም ፈጣን የሆነ ነው:: ለዚህም ከጥቂት ወራት ወይም ዓመታት በፊት በጥቂት ሰዎች ዘንድ ብቻ ይገኙ የነበሩ ብዙ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በአሁኑ ጊዜ በብዙዎቻችን እጅ እንደ ቀላል ነገር መገኘታቸውን ማየት ይቻላል::

በተጨማሪም የምድራችን የኤኮኖሚ ለውጥ እንቅስቃሴ የቅድሚያ ትንበያዎችን ሁሉ ከንቱ እያደረገ የራሱን ሥርዓት የሚከተል በመሆኑ፣ የወደፊቷ ዓለም ምን እንደምትመስል ለመገመት አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን ግራ የምታጋባ እንድትሆን አድርጓታል:: ለምሳሌ በ2008 ነዳጅ ዘይት ባልታሰበ ፍጥነት ድንገት ተተኩሶ በበርሜል 147 ዶላር እስኪደርስ ንሮ ነበር፤ ዳሩ ግን በጥቂት ወራት ልዩነት ውስጥ በበርሜል ከ40 ዶላር በታች ሲሸጥ ታየ:: ወዲያው ደግሞ የፋይናንስ ቀውስ ተከስቶ የዓለም ኢኮኖሚ ተናጋና ብዙ ሀብታም አገሮች ተቸግረው ታዩ:: ይህም ፈጽሞ ያለተጠበቀ ጉዳይ ነበር::

የዓለማችን ፖለቲካም ቢሆን ተለዋዋጭና የነገውን ማንም መገመት እስከማይችል ድረስ ሚስጥር እንደ ሆነ ነው:: ምንም እንኳ አንዳንዶች እንዲህና እንዲያ ይበሉ እንጂ ማንም እርግጠኛ ሆኖ ምክንያቱን መናገር የሚችል የለም:: ለአብነት ያህል ቢል ላደንን ጨምሮ ለልዕለ ኃያልዋ አገር አሜሪካ ከፍተኛ የስጋት ምንጭ የሆኑ አብዛኛዎቹ መንግሥታትና ግለሰቦች ከጥቂት ዓመታት በፊት ወዳጆችዋ የነበሩ ናቸው:: በቅርቡ በብዙ የአረብ አገራት የተከሰተው ሕዝባዊ ዐመጽና ፖለቲካዊ አለመረጋጋትም በማንም የዘርፉ ጠቢብ ነኝ ባይ ያልገመተና ያልተጠበቀ ነገር ነው::

በአጭሩ እነዚህ ሁኔታዎች ዓለማችን በፍጥነት ወደ መጨረሻው ጊዜ እየተጣደፈች እንደሆነ ይጠቁማሉ:: በመሆኑም በመጨረሻው ዘመን እንደሚሆኑ ለሚጠበቁት ነገሮች፣ እስራኤል፣ አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ ሁነኛ ስፍራ እንደሚኖራቸው ማስተዋል ይገባል፤ በመሆኑም

ይኼ የልዕልት ዲያና የሕይወት ሕልፈት ታሪክ እጅግ የሚያሳዝን ቢሆንም፣ ዓለማቀፋዊ ትስስሩ ምን ደረጃ እንደደሠ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ በመሆኑ፣ በምሁሩ ዘንድ ተመራጭ ምሳሌ ሆኖ ቀርቧል:: እንደ እውነቱ ከሆነ በዛሬው ጊዜ የሁላችም ዕለታዊ እንቅስቃሴና ኑሮ እንዲህ ከብዙ አገሮችና ሕዝቦች ጋር የተሳሰረ ነው:: ዓለምም እጅግ ጠባብ ሆናለች:: ተመልከቱ፣ በአንድ ስፍራ የሚደረግ ምንም ነገር፣ በሌላው ስፍራ በቀጥታ ሊተላለፍ ይችላል:: በየትኛውም አገር ያሉ ነጋዴዎች፣ በአገራቸው ካሉ ነጋዴዎች ጋር ብቻ ሳይሆን፣ በዓለም ዙሪያ ካሉ ሌሎች ነጋዴዎች ጋር ነው የሚወዳደሩት:: ምንም እንኳ አሁን፣ አሁን አንዳንድ አገሮች የገንዘባቸውን የምንዛሬ ዋጋ እነርሱ በሚፈልጉት መንገድ እየወሰኑ ለአገር ውስጥ ግብይት የበለጠ ትኩረት ለመስጠት ቢሞክሩም፣ ወይም ከውጪ ከሚያስገቡት ይልቅ ወደ ውጪ የሚልኩት ምርት ልቆ እንዲገኝ የተለያዩ ጥረቶችን ቢያደርጉም፣ ዓለማቀፍ ውድድሩን ለማስቀረት ዘላቂ መፍትሂ ያገኙ ግን አይመስልም:: ታዲያ ይኼ ነገር በዓለም ሁሉ አንድ ዓይነት የመገበያያ ገንዘብ ብቻ እንዲኖር ለሚጎተጉቱ ሰዎች ሁኔታዎችን የሚያመቻች ሆኖ ነው የሚታየው:: ይህ ደግሞ በሚመጡት ዘመናት በፍጥነት እንደሚገለጥ ለሚጠበቀው አንድ የዓለም ሥርዓት፣ ዋነኛው መሠረት መሆኑ የማይታበል ነው::

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ከጥቂት ዓመታት በፊት ዓለምን አንድ ስለማድረግ ማሰብ በራሱ እጅግ አስቸጋሪ ከመሆኑ አንጻር የዕብደት ያህል የሚቆጠር ነበር፤ ሳለንበት ዘመን ግን በፖለቲካ ሹመኞቹ በኩል ስምምነት ከተደረሰ ጉዳዩ የጥቂት ዓመታት ተግባር መስሎ ነው የሚታየው:: ደግሞም በአሁኑ ጊዜ ዓለምን አንድ ለማድረግ «ወሳኝ ናቸው» ከሚባሉት ነገሮች መኻል በተለይ ለሦስቱ፣ ማለትም ለአንድ የዓለም ሃይማኖት፣ ለአንድ የዓለም የፖለቲካ ሥርዓትና ለአንድ የዓለም ኢኮኖሚ፣ የሚባሉት ልዩ ትኩረት ተሰቷቸዋል:: ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትም ወደ ፍጻሜው ለማድረስ ደፋ ቀና እያሉ እንደሆነ እየታየ ነው:: በተለይም ከ1948 ጀምሮ ያለውን የዓለም ታሪክ በአንክሮ ስንከታተል ነገሮች የሚጓዙበት ፍጥነት እጅግ





አስጊ እንደሆነ እናያለን:: እንደሚታወቀው ይህ ዓመት «እስራኤል» በይፋ የተመሠረተችበት ዓመት በመሆኑ በአስደናቂነቱ ወደር የለውም:: በመሆኑም ከ1948 በኋላ በዓለም እየሆኑ ያሉት መሠረታዊ ጉዳዮችን መመርመር፣ የመጨረሻውን ዘመን ለሚያጠና ሰው አስፈላጊ ነው ተብሎ ይታመናል::

በ1948 የአውሮፓ የትብብር ምክር ቤትን የመመሥረት አሳብ ሲነሣ፣ ነገሩ እውን እንደሚሆን ስላልታያቸው ይመስላል፣ ብዙዎቹ የአውሮፓ አገራት አልተሳተፉበትም፤ ስለሆነም በወቅቱ የአባላቱ ቁጥር ከሦስት የሚበልጥ አልነበረም:: ምክር ቤቱ በተመሠረተ ጊዜ ግን በውሳኔ ቁጥር 7 ላይ እንደተመለከተው <u>«የአውሮፓ አንድ መሆን ለዓለም አንድ መሆን እጅግ አስፈላጊና ዋና ነገር ነው»</u> የሚል ዓላማ የነበረው ነው:: በእርግጥ በዓይን የሚታይ ተጨባጭ ተስፋ በሌለበት በዚያ ዘመን እንዲህ ዓይነት አሳብ መታሰቡ በራሱ ዓለምን አንድ የማድረግ ጉዳይ የአሁን ዘመን ሳይሆን፣ የረጅም ጊዜ ዕቅድ እንደነበር የሚያስረዳ ነው:: ለመጀመሪያ ጊዜ የአውሮፓ ምክር ቤት ሲቋቋምም አባላቱ ኔዘርላንድ፣ ሉክሰንበርግና ቤልጂየም ብቻ እንደነበሩ ሲታወስ ደግሞ፣ አሳቡን ያረቀቁት ሰዎች ተራ ህልመኞች እንዳልነበሩ እንገነዘባለን:: ደግሞም እነዚያ ጥቂት አገራት የተጠቀሰው ዓመት ከማለፉ በፊት ታላቋ ብሪታኒያንና ፈረንሳይን ጨምረው የብራስልሱን ስምምነት ለመፈራረም ችለዋል:: በዚያ ላይ የህልመኞቹ ህልም ሰምሮ፣ በ1954 የምዕራብ አውሮፓ ኅብረት /W.E.U /[2] እውን ሲሆን፣ እመርታው ብዙዎችን አፍ አሲዟል::[3]

በሌላም በኩል አፕሪል 4 1949 የተመሠረተው የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት ማለትም /N.A.T.O/[4] የአሜሪካንና የምዕራብ አውሮፓን ሁለንተናዊ ትስስር በእጅጉ አጠንክሮት ታይቷል:: ምንም እንኳ አንዳንዶች *«ከቀዝቃዛው ጦርነት ፍጻሜ በኋላ ወሳኝነቱም ሆነ*

[2] W.E.U western Eropian Union
[3] www.fulfilledprophecy.com. about the 666 and europe
[4] North Atlantic Treaty Organization

*አስፈላጊነቱ ያን ያህልም አይደለም»* ቢሉም፣ ሌሎች ግን *«በወደፊቷ ዓለም ያለው ሚና የሚናቅ አይደለም»* በማለት ይከራከራሉ::

ከዚህም በተጨማሪ በ1957 ሕልውናውን ያገኘውና አንድ መቶ የሚሆኑ የምድራችንን ሁነኛ ሰዎችን በአባልነት የሚያቅፈው የ«ሮም ክለብ» የተሰኘው ተቋምም ቢሆን፣ በዓለም ላይ ለሚሆኑ ቀጣይ ድርጊቶች አንጻች ሚስጥራዊ ተግባር እንዳለው ይጠረጠራል:: ይህ ክለብ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ *«በየጊዜው የሚከሰቱ የሰውን ልጅ ችግሮችን እንዴት እንፍታ?»* በሚለው ጉዳይ ላይ ለመምከር ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜም መድረሻ ግቡንና ሚናውን ቀስ በቀስ እየለየ የመጣ ይመስላል:: የሚገርመው ደግሞ በዚህ ክለብ ውስጥ እስከ ዛሬም ድረስ እስራኤል ያልተካተተች የመሆንዋ ጉዳይ ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ በዚህ ክለብ አባላት ልብ ውስጥ የኖረው ፍላጎት «አንድ የዓለም የኢኮኖሚ ሥርዓት መፍጠር» የሚል ነው:: የሮም ክለብ አባላት ዓለምን በአስር ትልልቅ የኢኮኖሚ ክልሎች የከፋፈሏት ሲሆን፣ ከ1974 ወዲህ አስቀድሞ በእነርሱ ልብ ከታሰቡት አሕጉራዊ የኢኮኖሚ ክልሎች መኻል የተወሰኑት እውን ሆነዋል:: በዚሁ መሠረት፣ በ1993 የአውሮፓ ኅብረት/E.U/፣ በ2002 የአፍሪካ ኅብረት/A.U/፣ በ2008 የደቡብ አሜሪካ መንግሥታት ኅብረት/U.S.A.N/ ሕልውናቸውን ያገኙ ሲሆን፣ የሰሜን አሜሪካ ኅብረትም/N.A.U/[5] በምሥረታ ላይ ነው:: እነዚህ ክፍለ አሕጉራዊ ኅብረቶች ደግሞ አዲስ ለሚፈጠረው አንድ የዓለም የኢኮኖሚ ሥርዓት፣ ፖለቲካዊ መሠረት ይኖራቸዋል፣ ተብሎ ይታመናል::

ከዚህ ጋር ዓለምን አንድ ሊያደርግ የሚችል ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት የመመሥረቱ ጉዳይ ጎን ለጎን እየተሠራበት ነው፤ በተለይ ከ1948 ጀምሮ የኮምፒዩተር በእያንዳንዱ ድርጅትና ግለሰብ እጅ በቀላሉ መገኘት የተነሣ፣ የታሰበው ዓይነት የንግድ ግብይት ሥርዓት ለመመሥረት ቀላል እንዲሆን ቅድመ ሁኔታው ተሟልቶለታል:: በዚሁ ታሪካዊ ዓመት፣ የዓለምን የኢኮኖሚና የንግድ ጉዳዮችን

[5] Europeans union, Africans union, The Union of South Americans Nations & The North Americans Union.





የሚወስኑ ሌሎች ድርጅቶችም ተቋቁመዋል:: ከእነዚህም መኻል፣ የዓለም የንግድ ድርጅት/W.T.O/፣ የዓለም የንግድና የቀረጥ ጠቅላላ ስምምነት /G.A.T.T/ የዓለም የገንዘብ ድርጅት/I.M.F/ እና የዓለም ባንክ/W.B / ሳይጠቀሱ የማይታለፉ ናቸው::[6]

በሌላ በኩል «የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት» የተመሠረተበት ዓመት በመሆኑ 1948 በተለየ ሁኔታ ይታወሳል፤ ኅብረቱ ሲመሠረት ዓላማዬ ብሎ የያዘው *«በአብያተ ክርስቲያናት መኻል ያሉት ልዩነቶች እንዳሉ ሆነው፣ አንዱ የሌላውን እምነት በማክበር ተቻችለው የሚሠሩበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር»* የሚል ነበር:: ከዚህም በኋላ በ1998 ደግሞ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጥላ ስር «ዩናይትድ ሬሊጂየስ ኢኒሼቲቭስ»[7] የተባለና የዓለም ሃይማኖቶችን ሁሉ ወደ አንድነት የሚያመጣ ተቋም ተመሥርቶ እስከ አሁን እየሠራ ነው::

እነዚህ ሁሉ መገጣጠሞች ለአዲሱ የዓለም ሥርዓት መሠረቶች ናቸው እንጂ፣ በአጋጣሚና በድንገት የሆኑ አይደሉም:: እንደ ሚባለውማ ከዚህ ጋር በተያያዘ በሚስጥር የሚከናወኑት ተግባራት በግልጥ ከሚታወቁት በብዙ እጅ የላቁ ናቸው:: ይህም ነገር የዚህ ዓለም ገዢ የተባለው ዲያቢሎስ በመጨረሻው ዘመን ላለው ዕቅድ ሁኔታዎችን እያመቻቸ ስለመሆኑ ዋቢ ማስረጃ ነው:: ከእነዚህ ሁሉ በላይ በአሁኑ ጊዜ በአውሮፓ እየሆኑ ያሉ አያሌ ነገሮች የማንንም ሰው ዓይንና ጆሮ የሚስቡ ናቸው:: ስለዚህ አውሮፓን ልብ ብላችሁ ተመልከቱ።።

[6] World Trade Organization, General Agreement on Trade & Tariff, International Monetary Fund, Wold Bank

[7] United Religions Incentive

ምንም እንኳ ከ፪ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ኃያል ሆና የተነሣችው አሜሪካ፣ ቀደም ብሎ አውሮፓ በዓለም ኢኮኖሚና ፖለቲካ ላይ በነበራት የወሳኝነት ሚና ላይ ተጽዕኖ እንዳሳረፈችበት ባይካድም፣ በመጨረሻው ዘመን ክንውኖች ግን አውሮፓ እንደገና ሁነኛ ስፍራ እንደሚኖራት ይጠበቃል:: እርግጥ ነው አሜሪካ ባላት ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ አቅም ምክንያት በአውሮፓም ሆነ በመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ ተደማጭ ሆና ቆይታለች፤ ሆኖም የእስራኤል ጽኑ አጋር መሆንዋን ተከትሎ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከብዙ የአረብና ከሙስሊም አገራት ጋር ያላት ወዳጅነት ብዙም የሚያወላዳ አልሆነላትም:: በተለይ እንደሳዳም፣ ቢንላደን፣ አልቃይዳና ታሊባንን ከመሳሰሉ «ሽብርተኞች»[8] ጋር ያደረገችውና በማድረግ ላይ ያለችው ጦርነት፣ በመካከለኛው ምሥራቅ የነበራትን ተቀባይነት በከፍተኛ ሁኔታ እንደ ሸረሸረው እየታየ ነው:: ከዚህም ሌላ አዲስ ስጋት ሆና ብቅ ያለችው ኢራን፣ ለዓመታት ልቧን አልሰጥ ያለችው የሦሪያ ጉዳይ፣ ውሉ ያልተገኘው የአፍጋኒስታን እጣ ፋንታ፣ ወዳጅ ትሁን ጠላት ያለየላት የፓኪስታን ነገር ከአውሮፓውያኑ ይልቅ የአሜሪካ ራስ ምታት ነው::

በአንጻሩ መጪው ጊዜ በየኛውም አቅጣጫ ለአውሮፓ የተሻለ ነገር ይዞላት እንደሚመጣ ይጠበቃል:: ለምሳሌ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማከተም በኋላ በምሥራቅና በምዕራብ አውሮፓ መኻል የነበረው የልዩነት ግድግዳ የተወሰነ ክፍል በመፍረሱ፣ የምዕራብ አውሮፓ አገራት በአሜሪካ ላይ የነበራቸው ተደጋፊነት እንዲገደብ ከማድረጉ በላይ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ በራስ መተማመናቸው ከፍ እያለ ነው:: ይኼ ደግሞ ቀድሞም የአሜሪካ የበላይነት ለማይዋጥላቸው ፈረንሳይን ለመሳሰሉ አገራት የልብ ልብ እንደሰጣቸው መታየት ጀምሯል:: ለዚህም የኢራቁን ጦርነት በተመለከተ አንዳንዶቹ ከአሜሪካ በተጻራሪ

[8] ሽብርተኛነት በራሱ ትርጉሙ አከራካሪ መሆኑ ሳይዘነጋ ይተርጎም::





የቆሙበትን ሁኔታ እንደ አንድ ማስረጃ ልንጠቅሰው እንችላለን:: በዚህም ምክንያት በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ አውሮፓ፣ በዓለም ፖለቲካና ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ የመወሰን አቅምና ኃይል እንደሚኖራት እንዲጠበቅ ሆኗል:: ከመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች አንጻርም ቢሆን የወደፊቷ አውሮፓ፣ በኢኮኖሚዋም ሆነ ወታደራዊ አቅሟ ዓለምን ለመምራት የሚያስችል የላቀ ደረጃ ላይ እንደ ምትደርስ ነው የሚታመነው:: እስቲ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን አንዳንድ የታሪክ ማስታወሻዎች ልብ ብላችሁ ተመልከቱ:: ምናልባት ስለአውሮፓ የወደፊት ዕጣፈንታ የሚጠቁሙት ነገር ይኖር ይሆን?[9]

ጥር 1 1995 የአውሮፓ ኅብረትና የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ኅብረት አባላት የሆኑ አስር የአውሮፓ አገራት የተለየ ኅብረት ለብቻቸው መሠረቱ:: የዚህ ኅብረት ስያሜም በ1948 ተመሥርቶ ቀስ በቀስ ሕልውናው በመክሰም ላይ ከነበረ ድርጅት የተወሰደ ሲሆን «የምዕራብ አውሮፓ ኅብረት»/WEU/ ይሰኛል:: አገራቱም፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ሉክሰንበርግ፣ ቤልጂየም፣ ኢጣሊያ /ሮም/፣ ፖርቱጋል፣ ስፔን፣ ግሪክና ሆላንድ ናቸው:: ሆኖም ብዙ ሰዎች ኅብረቱ ስለመኖሩ እንኳ ምንም የሚያውቁት ነገር የለም:: እሱ ግን አስቀድሞ የነበረ ሲሆን፣ በአውሮፓ ኅብረት መስፋፋት ምክንያት ዝናው ደብዝዞ የቆየ ነው::

በታህሳስ ወር 1998 የአውሮፓ ኅብረት በቬና ባደረገው ስብሰባ፣ በጸጥታና በውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ የሚሠራ አንድ ቢሮ ከፈተ፤ ቢሮው በተለይ በሩሲያ፣ በዩክሬንና በሜድትራሊያን አካባቢ አገሮች ላይ ልዩ ትኩረት እንዲያደርግ ታስቦ የተከፈተ ነው፤ ይህ ቢሮ እንዲከፈት ውሳኔ የተላለፈውም በውሳኔ ቁጥር «666» ነው:: እናም ጥር 1999 «የኔቶ»/NATO/ ዋና ጸሐፊ የነበሩት ጃቪር ሶላና የዚህ ቢሮ የመጀመሪያው ባለሥልጣን ሆነው ሲሾሙ፣ በወቅቱ «የአውሮፓ ኅብረት»/EU/ ዋና ጸሐፊ ሆነው ያገለግሉ ነበር፤ ደግሞም የአስሩ

[9] ከዚህ በታች ያሉት አብዛኛዎቹ ሀሳቦች እንዳለ የተወሰዱት፣ www.fulfilledprophecy.com. ከተባለ ድረ ገጽ *about the 666 and Europe* ከተሰኘው ጽሑፍ ነው::

«የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ኅብረት»/WEU/ ዋና ጸሐፊም ነበሩ:: ይህ ማለት ውሳኔው ሶላናን በሦስቱም ቁልፍ ሥልጣኖች ማለትም በኔቶ፣ በአውሮፓ ኅብረትና በምዕራብ አውሮፓ ኅብረት ውስጥ ቁልፍ ሰው እንዲሆኑ አስችሏቸዋል::

ጥር 1 2000 የአውሮፓ ኅብረት አባል አገራት ከጥቂቶቹ በስተቀር አዲሱን የመገበያያ ገንዘባቸውን ማለትም «ዩሮ»ን በሥራ ላይ አዋሉ፤ ይኼም ለኅብረቱ እንደ ታላቅ ድል ተቆጥሮለታል:: በተጨማሪም በዚያው ዓመት ሰኔ 5፡ 2000 «የምዕራብ አውሮፓ ኅብረት» ውሳኔ «666»ትን ተቀብሎ ያጸደቀው ሲሆን፣ ይህም የምዕራብ አውሮፓ ኅብረት/WEU/ የአውሮፓ ኅብረትን/EU/ የሚቆጣጠር አስመስሎታል::[10]

የካቲት 28 2002 የአውሮፓ ኅብረት በወደፊቷ አውሮፓ ጉዳይ ለመነጋገር የመጀመሪያ ስብሰባውን አካሂዶ ነበር፤ በስብሰባው መጨረሻ የኅብረቱ ካውንስል በ2004 እውን ስለሚሆነው፣ የኅብረቱ ሕገ መንግሥት ጉዳይ በሰፊው ተነጋግሮ ውሳኔ ማሳለፍ ችሏል:: ይኼም በአንዳንዶች ዘንድ «ለሮም ኢምፓየር» ዳግም ልደት እንደ አንድ እርምጃ ተደርጎ ተወስዷል::

መጋቢት 12 2002 የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት «ውሳኔ 1397» የተሰኘ ውሳኔ አስተላለፈ፤ ውሳኔውም የፍልስጥኤም መንግሥት ምሥረታን የሚመለከት ነው:: እጅግ በሚደንቅ ሁኔታ አሜሪካ የዚህ ውሳኔ አሳብ ዋነኛ አቀንቃኝ ሆና መገኘቷ ነው:: ምንም እንኳ ከስብሰባው በኋላ እስራኤልና አሜሪካ አዲስ ነገር እንዳልተፈጠረ ቢያስመስሉም ቃላት ሊደብቀው ያልቻለ ሐቅ ፍጥጥ ብሎ ይታይ ነበር፤ ይህም በዋሽንግተንና በኢየሩሳሌም ፍቅር መኻል ጽኑ ነፋስ መንፈስ መጀመሩን የሚያመለክት ነበር::

[10] ሁኔታው በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ ደግሞ ምናልባት ከእስፉአልና ከቀረው ዓለም ጋር የሰባት ዓመት የሚጸናውን ስምምነት የሚፈራረመው በእነዚህ አገሮች ላይ የሚሸመው ሰው ይሆናል::





ሐምሌ 1 2002 የመጀመሪያው የዓለም ፍርድ ቤት ተመሠረተ፤ የሚገርመው ፍርድ ቤቱን ለማስጀመር አስፈላጊ የነበረው ድምፅ 60 አገራት ድምፅ ብቻ የነበረ ቢሆንም ተጨማሪ 6 ድምፅ ተገኝቷል::[11]

መስከረም 12 2002 ወደፊት ተግባራዊ በሚሆነው የአውሮፓ ኅብረት ሕገ መንግሥት ፕሬዚዳንት ይሆናሉ ተብሎ የሚጠበቁት «ቫለሪይ ጊስካርድ» አነጋጋሪ አሳብ አቀረቡ፤ ይኼም የአውሮፓ ኅብረት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ዋና ኃላፊ የሆኑት «ጃቬር ሶላና» የተሻለ አቅም ማግኘት እንዳለባቸው የሚያሳስብ ነበር፤ በወቅቱ ጊስጋርድ ያቀረቡት አሳብ፣ ሶላና እንደማንኛውም አባል አገር በኅብረቱ ውስጥ ወንበር እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል:: ይህ ደግሞ በግለሰብ ደረጃ ከፍተኛው የሥልጣን እርከን መሆኑ ነው::

ጥቅምት 7 2002 ሶላና፣ ስለኅብረቱ ወታደራዊ ሚስጥር ጉዳይ በሐምሌ 2000 አቅርበውት የነበረው አንድ ሰነድ ውሳኔ አገኘ፤ ሰነዱ «የኅብረቱ ወታደራዊ ሚስጥሮች ጉዳይ» በመባል የሚታወቅ ሲሆን፣ በወቅቱ ሦስት የኅብረቱ አገሮች አሳቡን በመቃማቸው ሳይጸድቅ እየተንገዋለለ ቆይቶ ነበር:: ሆኖም በዚህ ጊዜ ለውሳኔ የቀረበው አሳብ ቀድሞ ስምምነት ለማድረግ ባስቸገሩት ጉዳዮች ላይ ማሻሻያ ተደርጎ በመቅረቡ፣ የተቃወሙትን ልብ ሁሉ ሊማርክ ችሏል:: በዚሁ መሠረት የመጀመሪያው ሰነድ የኅብረቱን ወታደራዊ ሚስጥሮች ከጥቂቶች በቀር ማንም እንዳያይ ይከለክል የነበረ ሲሆን፣ ተሻሽሎ የቀረበው ሰነድ ግን «ሚስጥራዊነቱን በተመለከተ ካውንስሉ እንዲወስን» የሚል አንቀጽ እንዲካተትበት ተደርጓል:: ታዲያ ውሳኔው ለሶላናና ለመማክርት ጉባኤው እንደ ታልቅ ድል ነበር የተቆጠረው::

ጥር 1 2003 ግሪክ የስድስት ወራት ዕድሜ ያለውን የኅብረቱን የፕሬዚዳንትነት ሥልጣን የተረከበች ሲሆን፣ ሐምሌ 1 2003 ደግሞ ኢጣሊያ ከግሪክ ሥልጣኑን ተቀብላለች:: በዚህ ውስጥ ሁለት ዓይንና ጆሮ የሚስቡ ጉዳዮች ነበሩ፤ አንደኛው፣ በታሪክ እንዳለፈው ከግሪክ

[11] ይህም 60+6 ማለት ነው፤ ምናልባት አንዳች የሚጠቀመው ነገር ይኖር ይሆን?

ቀጥሎ ኢጣሊያ /ሮም/ መሪነቱን መረከቧ ሲሆን፣ ሌላው ስብሰባው የተደረገው በጥንታዊቷ የግሪክ ከተማ በተሰሎንቄ መሆኑ ነው።[12]

የካቲት 14 2003 ዋሽንግተንና ለንደን በኢራቅ ኃይል እንዲሰማራ ያቀረቡትን አሳብ ባልተለመደ ሁኔታ ፈረንሳይና ጀርመን እጅግ ተቃወሙት። ይህም በአውሮፓና በአሜሪካ መኻል ውስጥ ውስጡን ሲብላላ የከረመውን ልዩነት ይፋ ያወጣ ሆኖ ተቆጠረ። በዚያ ላይ መጋቢት 20 2003 ከመንግሥታቱ ማኅበር ዕውቅናና ፈቃድ ውጪ አሜሪካ፣ በኢራቅ ላይ ወረራ መፈጸሟን ተከትሎ በርካታ የአውሮፓ አገራት ድርጊቱን አወገዙ። ሆኖም ግን ሦስት የአውሮፓ አገራት፣ ማለትም እንግሊዝ፣ ስፔንና ፖርቹጋል ለአሜሪካ ፍጹም ድጋፋቸውን ሰጥተዋል። በሌላም በኩል የኢራቅን ወረራ አጥብቀው የተቃወሙ አገራት ማለትም ቤልጂየም፣ ሉክሰንበርግ፣ ፈረንሳይና ጀርመን ሚያዝያ 29 2003 የተናጥል ስብሰባ አደረጉ፤ ዓላማቸውም «ጠንካራ ድንጋይ» ብለው የጠሩትን ኅብረት መፍጠር ነበር። የአገራቱ አሳብም አሜሪካ በአውሮፓ ያላትን የቆየ ፍላጎትና ተጽዕኖ ለመቋቋም ብሎም ለማደብዘዝ ያለመ ነው። ምንም እንኳ ጃቪየር ሶላና በስብሰባው ባይገኙም፣ የዓላማው ደጋፊና አቀንቃኝ መሆናቸውን አስታውቀዋል። ሰኔ 13 2003 ረቂቅ አሳቡ ለአውሮፓ ኅብረት ባለሥልጣናት ቀረበ፤ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የአውሮፓ ኅብረት ፕሬዚዳንትና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሆነውን ሰው ጠራ፤ ሰውየውም ከምክር ቤቱ አባላት እኩል የመወሰንና በልዩ ልዩ ሰነዶች ላይ የመፈረም ሥልጣን ያለው ነው።

ሰኔ 19 2003 በተደረገው የአውሮፓ ኅብረት ስብሰባ ላይ ጃቬር ሶላና የጸጥታ ጉዳዮችን የሚመለከት ባለአስር ገጽ ሰነድ ለስብሰባው አቀረቡ፤ ሰውየው፣ በዚያው ዓመት ማለትም ሰኔ 25 ቀን ከአሜሪካ ጋር በጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎችና በሽብርተኞች ጉዳይ አብሮ መሥራት የሚያስችል ስምምነት ተፈራረሙ።

[12] ጳውሎስ ለዚህችው ከተማ በተለየ ጊዜ የጻፋቸው ሁለት መልዕክቶች በአዲስ ኪዳን ላይ ይገኛሉ፤ በመልዕክቶቹም ስለመጨረሻው ዘመንና በዚያው ወቅት እንደሚገለጥ ስለሚጠበቀው የዐመጽ ሰው ሰፊ ትምህርት ሰጥቷል። ታዲያ ይህ ነገር መገጣጠሙ በራሱ አንዳች የማስጠንቀቂያ መልዕክት ይኖረው ይሆን?





በሐምሌ ወር 2003 የአውሮፓ ኅብረት አገራት ስብሰባቸውን በግሪክ ሲያደርጉ «ኅብረቱ ምን ዓይነት ቅርጽ ይኑረው» በሚለው ጉዳይ ላይ ለመግባባት ተቸግረው ነበር። ይኼ ደግሞ ለጃቬር ሶላና «ደኅንነቷ የሚያስተማምን አውሮፓ፣ ለተሻለች ዓለም» የተሰኘ ባለ 900 ገጽ ጹሑፍ ለማቅረብ ምቹ ጊዜ ሆኖላቸዋል። ጽሑፉም ሦስት ክፍሎች ያሉት ሆኖ፣ የመጀመሪያው ክፍል «ኅብረቱ አስፈላጊውን አቅርቦት በማሟላት፣ ለጎረቤት አገሮች መረጋጋትን መፍጠር» የሚል ርዕስ አለው። ሁለተኛው የጽሑፉ አካል ደግሞ «የአውሮፓ ኅብረት በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን የማዘዝ አቅም መገንባት አለበት» የሚል ሲሆን፣ በሦስተኛው የጽሑፉ ምዕራፍም «ኅብረቱ አፈንጋጭ ከሆኑና ጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ከታጠቁ አገራት ራሱን መከላከል ይችል ዘንድ አስተማማኝ በሆነ መልኩ የሲቪልና የወታደራዊ አቅሙን ማጠናከር አለበት» በሚል ጉዳይ የሚያጠነጥን ነው።

በእርግጥ ላይ ላዩን ብቻ ሲታይ የሶላና ዕቅድ ያን ያህል አስገራሚ ላይመስል ይችላል። የሚደንቀው ግን እነዚያ በተለያየ አመለካከትና በውጥረት ውስጥ የነበሩ አገሮች በጠቅላላ ዕቅዱን መቀበላቸው ነው። ፈረንሳይ፣ በአሜሪካ ኃያልነት ላይ ቀዝቃዛ ውኃ የሚያፈስ ሆኖ ስላገኘችው፣ ዕቅዱን በደስታ ነበር የተቀበለችው። ጀርመን፣ ዕቅዱን የወደደችው በኅብረቱ በኩል ብሔራዊ ዕዝ መመሥረት ስለሚያስችል ነው፤ እንግሊዝ፣ ፖርቹጋልና ስፔን ዕቅዱን የደገፉት፣ የአውሮፓ ኅብረት ከአሜሪካና ከሰሜን አትላንቲክ ኅብረት ጋር ጥሩ ግኑኝነት ለመመሥረት ያስችለዋል ብለው ስላሰቡ ነው። ሌላው ቀርቶ ራሷ አሜሪካ እንኳ ዕቅዱን በሙሉ ልቧ ተቀብላዋለች።

ሌላው በጣም አስገራሚው ነገር ደግሞ ዕቅዱ የቀረበበት ጊዜ ነው። በወቅቱ ኅብረቱ ስለወደፊቷ አውሮፓ መጻኢ ዕድል እየተነጋገረ ነበር፤ ከውይይቱ አጀንዳ መኻል የኅብረቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከፍተኛ ሥልጣን ሊኖረው እንደሚገባ የሚገልጥ አንቀጽ ነበረበት። እናም በመጨረሻ የተደረሰበት የስምምነቱ ሰነድ እንደሚያሳየው ሰውየው ኅብረቱን ወክሎ ማንኛውንም ዓይነት ስምምነት ማድረግ የሚያስችል ሥልጣን እንዲኖረው ተደርጓል። ይህ ማለት ደግሞ ይኼ ሰው፣ ከማንኛውም አካል በላይ የሆነ ሥልጣንና ኃይል እንዲኖረው

ያደርገዋል ማለት ነው:: በዚህ ምክንያት ውሳኔውን እንደ ተራ ጉዳይ ለማየት ያስቸግራል::

ይህ በዚህ እንዳለ ግንቦት 1 2004 የአውሮፓ ኅብረት አስር አዳዲስ አገራትን በአባልነት መቀበሉን ተከትሎ፣ የአባል አገራት ቁጥር ወደ ሃያ አምስት ከፍ አለ:: ነገር ግን በኅብረቱ ውስጥ ኃያል የሆኑት ፈረንሳይ፣ ጀርመንና እንግሊዝ ፍላጎታቸውን ሊያስከብር የሚችል የራሳቸው የዳይሬክተሮች ቦርድ አቋቁመዋል:: ይኼም ለኅብረቱ ዋና ጸሐፊ ቀላል የማይባል ፈተና እንደሆነ ግልጥ ነው::[13]

ሰኔ 15 2004 የኅብረቱ መሪዎች ተሰብስበው የአውሮፓ ኅብረት ሕገ መንግሥትን በፊርማቸው አጸደቁ፤ የፊርማ ሥነ ሥርዓቱ የተዘጋጀው ሮም ውስጥ ስለነበር በጊዜው «የሮም ስምምነት»[14] የሚል ስያሜ ተሰጠው:: ከአስራ አምስት ቀናት በኋላ ሰኔ 29 2004 ኅብረቱ የግማሽ ዓመት ስብሰባውን ሲያደርግ፣ ሶላና የኅብረቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ሥልጣን በይፋ ተሰጧቸዋል:: አዲስ በተረቀቀው ደንብ መሠረት ይህ ስፍራ ቁልፍ ሥልጣን እንደ ሆነ ልብ ይሏል::

ህዳር 30 2004 የፍልስጥኤሙ መሪ ያሲር አራፋት በድንገት ሞቱ፤ አስገራሚው ነገር ሰውየው ከመሞታቸው ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ፣ ለፍልስጥኤም፣ እስራኤል የዘመናት ችግር መፍትሄ እንዳገኙለትና ጉዳዩም የሳምንታት ዕድሜ ብቻ እንደቀረው ሶላና ሲናገሩ የተሰሙ መሆኑ ነው:: በወቅቱ እስራኤል የአውሮፓን የጉርብትና ፖሊሲ ለመቀበል ዳር ዳር ስትል ታይታለች:: በሶላና የተረቀቀው ፖሊሲ፣ ሃያ አምስቱ የአውሮፓ ኅብረት አባል አገራትንና ከኅብረቱ ውጪ የሆኑ አስራ ሰባት አገራትን የሚመለከት ነበር:: ታህሳስ 7 2004 እስራኤል የሶላናን ፖሊሲ በቃል ደረጃ በመቀበል ቀዳሚ አገር ሆነች፤ ስምምነቱ ቢጸድቅ ኖሮ ከጥር 1 2007 ጀምሮ ለሰባት ዓመት የጸና ይሆን ነበር:: የአውሮፓ ኅብረት ሰባት የበጀት ዓመት ያለው ሲሆን፣ ከጥር 2007 ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን ነበር የታሰበው::

[13] በአውሮፓ አካባቢ የተለየ ፍላጎት ያላቸውን አገሮች በትኩረት መመልከት ከፋት ያለው አይመስለኝም::
[14] The RomeTreaty





እነዚህ ሁሉ ኹነቶች፣ በሚመጣው ዓለም አውሮፓ ያላት የመሪነት ድርሻ ምን ላይ እንደ ደረሰ ፍንጭ ይሰጣሉ የሚል ግምት አለኝ:: በዚያ ላይ ከማንኛውም አሕጉር ይልቅ በመካከለኛው ምሥራቅ ባለው ነዳጅ እጅግ ተደጋፊ በመሆንዋ ስፍራው ለእርሷ የሕልውናዋ ምንጭ ነው:: ከዚህ አንጻር እስራኤልንና መካከለኛው ምሥራቅን አስመልክቶ የምትከተለው ፖሊሲ በሚመጣው ጊዜ በዓለም እንደሚፈጸም ለሚጠበቀው ትንቢት ሁነኛ ስፍራ ያለው ነው::

ከዘመናት በፊት ዳንኤል በራእይ እንደተመለከተው፣ ታላቁ ባሕር እጅግ እየተናወጠ ልዩ፣ ልዩ መልክ ያላቸው አውሬዎች ከውስጡ ይወጡ ነበር:: ይኼም ባሕር በደቡባዊ አውሮፓ የሚገኝ ሲሆን፣ የሚድትራሊያን ባሕር በመባል ይታወቃል:: ስለዚህ አውሮፓን ልብ ብለን መመልከት ያለብን አራተኛው አውሬ ከዚያ ባሕር አካባቢ እንደሚወጣ ስለሚጠበቅ ነው:: ዮሐንስም ስለመጨረሻው አውሬ በተናገረ ጊዜ፣ ከባሕር እንደሚወጣ ነው የጠቆመው:: ይኼም አውሬ በመጨረሻው ዘመን በሚነሡ አስር አገራት ላይ ተሹሞ ዓለምን የሚገዛው ሐሰተኛው ክርስቶስ ነው::

# ምዕራፍ ፳፫

## *ጎግ ማጎግ*

[15]

የሰው ልጅ ሆይ፣ ፊትህን በጎግ ላይና በማጎግ ምድር ላይ፣ በሞሳህና በቶቤል ዋነኛ አለቃ ላይ አቅናበት፤ ትንቢትም ተናገርበት።

የትንቢተ ሕዝቅኤል 38ኛ ምዕራፍ የሚጀምረው፣ ሕዝቅኤል በማጎግ ምድር ወደሚገኘውና የሞሳሕና የቶቤል ዋና አለቃ ወደሆነው «ጎግ» ፊቱን አዙሮ ትንቢት እንዲናገር በሚያዘው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ከዚያም ቀጥሎ እግዚአብሔር ጎግንና ከእርሱ ጋር የጦር ቃል ኪዳን ያላቸውን አገሮች ሁሉ ስቦ ወደ ጥፋታቸው እንደሚያወጣቸው ተጠቅሷል። ደግሞም በጎግ መሪነት የሚነሣው ሠራዊት ዘመቻውን የሚጀምረው ከብዙ ቀናት በኋላ በሚሆን በ«ኋለኛው ዘመን» እንደ ሚሆን ከመገለጡም ሌላ፣ ወረራውን የሚፈጽመውም በእስራኤል ላይ እንደሚሆን ይታያል። ወቅቱም እስራኤላውያን ለዘመናት ተበትነው ከነበሩበሩባቸው የአሕዛብ ምድር ወደአገራቸው ተመልሰው በሰላምና በመረጋጋት የሚኖሩበት ዘመን እንደሚሆን ተነግሯል።

*በዚያ ዘመን በጎግ ልብ ውስጥ ክፉት ይገባል፤ እስራኤልንም፣ ቅጥር እንደሌላትና ተዘልላ እንደምትኖር አድርጎ ይቆጥራል፤ ደግሞም «ያለ በርና ቅጥር ተረጋግቶ የተቀመጠውን ሕዝብ እወጋለሁ፣ እነጥቃለሁ፣ እዘርፋለሁ፤ እጄንም በእርሱ ላይ የማነሣበት ምቹ ሰዓት አሁን ነው» ብሎ ያስባል። ከዚህ የተነሣ ጎግና ሠራዊቱ ለእስራኤል፣ ድንገት እንደ ማዕበል የሚከሰቱ ይመስላሉ። ሆኖም የሕዝቅኤል 38ኛ ምዕራፍ ከመጠናቀቁ በፊት ባሉት ክፍሎች በስፋት እንደተገለጠው፣ በዚህ ጦርነት መኻል የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት ይሆናል። ዘመኑ በደረሰ ጊዜ እንደሚሆን የሚጠበቀው የጎግ ትዕቢት፣ የእግዚአብሔር ብርቱ ቁጣ የሚቀሰቅስበት*

[15] ሕዝቅኤል 38 እና 39 በጠቅላላ። ደግሞ በተለይ ሕዝ38:2 ይመለከቷል። የሰው ልጅ ሆይ፥ ፊትህን በጎግ ላይና በማጎግ ምድር ላይ፥ በሞሳሕና በቶቤል ዋነኛ አለቃ ላይ አቅናበት፥ ትንቢትም ተናገርበት፥





*ከመሆኑም ሌላ፣ ለእስራኤል ያለው ቅንአት የሚገለጥበት ዘመን ሆኖ ይታያል። ታዲያ እግዚአብሔር እስራኤልን ለማዳን ጽኑ ክንዱን ሲያነሣ፣ በምድር ላይ የሚኖሩ ፍጥረታት፣ ሕይወት ባላቸውና ሕይወት በሌላቸው ላይ ታላቅ ሽብር ይሆናል። እግዚአብሔር በቀድሞ ዘመናት ለእስራኤል እንዳደረገው እንዲሁ ጎግን ስለሚዋጋው በምድር ላይ ቸነፈርና የደም መፋሰስ ይሆናል፤ ዶፍ፣ ዝናብና የበረዶ ድንጋይ፣ የሚያቃጥል ድኝ፣ በጎግና በሠራዊቱ ላይ ከሰማይ ይወድቅባቸዋል። ይኼን ተከትሎም በጎግና በሠራዊቱ ዘንድ አስቃቂ የእርስ በርስ ጦርነት ሲሆን፣ አጋጣሚው ግን እግዚአብሔር ራሱን ለዓለም በክብርና በግርማ የሚገልጥበት ይሆናል፤ ብዙ ሕዝቦችም እሱ ማን እንደሆነ ያውቃሉ።*

የሕዝቅኤል ትንቢት 39ኛ ምዕራፍም ቢሆን ስለዚሁ ነገር ተጨማሪና ዝርዝር ማብራሪያዎችን በመስጠት ይቀጥላል። ጎግና ሠራዊቱ፣ የተማመኑት የጦር መሣሪያ ሁሉ ፈጽሞ ሊታደጋቸው ስለማይችል ፍጻሜና መቃብራቸው በእስራኤል ምድር እንደሚሆን የምንረዳው በእነዚሁ ክፍሎች ላይ ነው። ከዚያ በኋላ የእስራኤላውያኑ ቀጣይ ተግባር የጎግን ሠራዊት የጦር መሣሪያና የኃይል አርቅቦት ምንጭ የሆኑትን ቁሳቁሶች ከየስፍራው በመልቀም፣ መቃጠል የሚገባውን ማቃጠልና ጠቃሚ የሆነውን ደግሞ የማከማቸት ሥራ ነው። ነገር ግን የጎግና የሠራዊቱን ሬሳ ማንሣት ከባድ ስለሚሆን፣ ወራትና ዓመታትን መፍጀቱ አይቀርም። ምናልባትም እስራኤል ከውጪ አገራት ሳይቀር በዚሁ ሥራ የሚሰማሩ ሠራተኞች እንድቅጠር ትገደድ ይሆናል። በዚያ ላይ በእነዚያ ወራት በተለየ ሁኔታ የሞቱ ሰዎችን እያሰሱ ለቀባሪዎች የሚያመለክቱ ሰዎች እንደሚኖሩ ይታያሉ። ይኼም ነገር በጦርነቱ ሰዓት ጥቅም ላይ የሚውል የተለየ የጦር መሣሪያ ሊኖር እንደሚችል እንድንጠረጥር ያደርገናል።

በእርግጥ እንደ እስራኤላዊ ሆነው ሲያስቡት፣ ይህ ዘመን እጅግ በጣም የሚናፈቅና የሚያጓጓ ነው። እስራኤላውያን በሙሴ መሪነት ከግብጽ ምድር ከወጡበት ጊዜ በኋላ፣ በዓለም ሕዝቦች ፊት እንዲህ ዓይነት ክብርና መፈራት ያገኙበት ጊዜ እንደሌለ እገምታለሁ።

ከእነዚያ ዘመናት በኋላም፣ እግዚአብሔር በምንም ዓይነት ሁኔታ ቅዱሱ ስሙ በማንም እንዲቃለል አይፈቅድም::

ከምዕራፍ 40፣ እስከ ምዕራፍ 44 ባሉት ክፍሎች በአብዛኛው ስለቤተ መቅደሱና በውስጡ ስለሚፈጸመው ሥርዓት የሚዘረዝር ከመሆኑም በላይ፣ እግዚአብሔር ለዘላለም በእስራኤላውያን መኻል እንደሚሆን በሚገልጡ አሳቦች የታጨቀ መሆኑ፣ እንዲሁም በምዕራፍ 44 በቤተ መቅደሱ ውስጥ በእግዚአብሔር መንፈስ የሆነውን አስደናቂ ሥርዓት ሕዝቅኤል ማየቱ፣ በሚመጣው ዘመን እግዚአብሔር እንዴት ባለ ክብር በእስራኤል መኻል እንደሚሆን የሚያመለክት ይመስላል:: ከዚህ አንጻር በራእይ መጽሐፍ የተጠቀሱት ነገሮች፣ ከሕዝቅኤል ትንቢት ጋር ግንኙነት እንዳላቸው ወይም እንደሌላቸው መመርመር ተገቢ ነው:: በተለይም ጎግ ማነው? በሕዝቅኤልና በዮሐንስ ራእይዎች ላይ የመታየቱ ሚስጥርስ ምንድን ነው? በሁለቱ ነብያት የታዩት ራእዩዎች የሚፈጸሙት በተመሳሳይ ሰዓት ወይስ በተለያየ ወቅት? የሚሉትና የመሳሰሉት ጥያቄዎች ችላ ተብለው መታለፍ ያለባቸው አይመስሉም:: ደግሞም ጉዳዩ ከተነሣ ዘንድ የተለያዩ አመለካከቶችን አብሮ መመልከት አስፈላጊ መስሎ ይታየኛል::

በበኩሌ ይህ ትንቢት በራእይ መጽሐፍ ላይ ከተጠቀሰውና ከሁለት መቶ ሚሊዮን በላይ ሠራዊት አሳትፎ፣ የዓለምን አንድ ሦስተኛ ሕዝብ ከሚያወድመው ጦርነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ይኖረው ይሆን? የሚለው ጉዳይ ያሳስበኝ ነበር፤ ሆኖም ነገሩን ባጠናሁት ጊዜ ከጠበቅሁት በላይ የተወሳሰበና ለመረዳትም ቀላል ያይደሉ አሳቦች የሞሉበት እንደሆነ ለመገንዘብ ችያለሁ:: እንደ እውነቱ ከሆነ የትንቢቱን ጥልቀትና ስፋት ስናስተውል በነገረ መለኮት ተማሪዎች ዘንድ ያለው ሰፊ የአተረጓጎም ልዩነት፣ ብዙም አያስደንቀንም::





*ጎግ ማጎግ*

*ለአይሁድና ለሙስሊሞች*

16

ጎግ ማጎግን አስመልክቶ የተነገረው ትንቢት ከክርስቲያኖች ሌላ፣ አይሁዶችና ሙስሊሞች በየራሳቸው ታሪክና ሃይማኖታዊ ወግ በኩል እንደሚጠባበቁት መገንዘብ ያሻል:: ምንም እንኳ በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች አተረጓጎም፣ በክርስቲያኖች መኻል «ፍጹም ስምምነትና አንድነት አለ» ባይባልም ከአይሁድና ከሙስሊም ትምህርት አንጻር ግን የሰማይና የምድር ያህል የተለየ መሆኑ ግልጥ ነው:: ከዚህ አንጻር የአይሁዳውያኑና የሙስሊሞቹ እምነት መቼም ከክርስቲያኖች እምነት ጋር እንደማይስማማ የታወቀ ነው::

የአይሁድ የሃይማኖት ምሁራን የጎግ ማጎግ ጦርነት፣ በመጨረሻው ዘመን ዓለም እስራኤልን ለማጥፋት የሚያደርገው ጦርነት ነው ብለው ያምናሉ:: እንደ አይሁድ ሃይማኖት ሊቃውንት እምነት፣ የዮሴፍ ልጅ የሆነው «መሲህ» ሦስተኛውን ቤተ መቅደስ ከሠራ ከጥቂት ጊዜ በኋላ «አርሚለስ» በሚባል ሰው ይገደላል:: እዚህ ላይ አይሁዳውያኑ «አርሚለስ» የሚሉት ሰው ባሕርይ በክርስቲያኖች ዘንድ «ሐሰተኛው ክርስቶስ» ከሚባለው ሰው ጋር የሚመሳሰል ሲሆን፣ አይሁዳውያኑ ስለመሲሁ ያላቸው እምነትና ታሪክ ግን በክርስቲያኖች ከሚታወቀው ፍጹም የተለየ ነው:: እንደ አይሁዳውያኑ ትምህርት ከሆነ፣ ወደፊት የዮሴፍና የዳዊት ልጅ የሚሰኙ ሁለት መሲሆች ነው የሚኖራቸው:: ከሁለቱ መሲሆች ቀድሞ የሚመጣው «የዮሴፍ ልጅ ነው» ነው ይላሉ:: እርሱም በጠላቶቹ እጅ ተሰቃይቶ ይሞታል:: ሆኖም ቀጥሎ የሚመጣውና «የዳዊት ልጅ የሆነው» መሲህ ግን አሸናፊውና የሚነግሠው «መሲህ» እንደሆነ ያስባሉ:: "*አስቀድሞ የሚመጣው የዮሴፍ ልጅ «መሲህ» በ«አርሚለስ» ከተገደለ በኋላ እስራኤል በታላቅ መከራ ውስጥ ታልፋለች፤ ይህም ጽኑ መከራ የዳዊት ልጅ የሆነው*

[16] በዚህ ክፍል ያሉት መረጃዎች በአብዛኛው http://www.truthnet.org/Islam/Islam-Bible/ ከተባለ ድረ ገጽ የተገኙ ናቸው::

*«መሲሀ» በሚመጣበት ወቅት የሚወገድ ሲሆን፣ እሱም «አርሚለስን» ገድሎ በመሲህነቱ ሥልጣን አገዛዙን ይጀምራል።"* ይላሉ።

በሌላም በኩል ሙስሊሞች ስለጎግ ማጎግ የሚናገሩት ታሪክ አስገራሚ ነው። በእርግጥ የእነርሱን ለየት የሚያደርገው፣ እንደ ክርስቲያኖችና አይሁዶች በቀጥታ ከሕዝቅኤል ትንቢት የተወሰደ አለመሆኑ ነው። ሙስሊሞቹ የጎግ ማጎግን ታሪክ በ300 ዓ.ዓ ቅድመ ክርስቶስ በዓለም ላይ ገኖ ከነበረው ከታላቁ አሌክሳንደር ታሪክ ጋር ማያያዛቸው ግራ ያጋባል። በሙስሊም ትምህርትና በቁራን ውስጥ ተጽፎ በሚገኘው መሠረት ታላቁ እስክንድር «አ ድሁል ቁርኔይን» ተብሎ ነው፣ የሚጠራው። ይህም ሰው የብረት ቅጥር ሠርቶ ሙስሊሞችን ከሰሜን ለይቶ አኑሯቸው ነበር፤ ይላሉ። ታሪኩ ሲቀጥልም *«በመጨረሻው ዘመን ጎግና ማጎግ የተባሉ ሁለት ሰዎች በምድር ይለቀቃሉ፤ እነዚህም ሰዎች ወዲያው የእስላም ጠላቶች ሆነው ይነሣሉ፤ ሙስሊሞችንም ያጠቃሉ»* ይላሉ[17]

ነገር ግን በሙስሊሞች በሚተረከው የጎግና የማጎግ ታሪክ፣ ጎግም ሆነ ማጎግ የሰው ስሞች ሆነው ነው የተገለጡት። ሆኖም ከቁርዓን 1000 ዓመት በፊት ቀድሞ በደረሰው መጽሐፍ ቅዱስ «ጎግ» የሰውየው፣ «ማጎግ» ደግሞ የሚነሣበት አገር ስም በመሆኑ የልዩነታቸውን ስፋት የሚያሳይ ነው። ከዚህ ሌላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባለው ታሪክ ጦርነቱ እስራኤልን ለማጥፋት የሚደረግ ጦርነት ሲሆን በቁርአን ግን በሙስሊሞች አንጻር የሚደረግ ጦርነት እንደሆነ ነው የተብራራው። በእርግጥ በቁርአን ውስጥ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ቢኖሩም በመጽሐፍ ቅዱስ ካለው ፍጹም የተለዩ መሆናቸው የተለመደ ነው። ይህም *«ቁርአን ከመጽሐፍ ቅዱስ የወሰዳቸው በርካታ ታሪኮች፣ እንዲሉለት የሚፈልገውን አሳብ ብቻ እንዲሉ አሳባቸው ተቀይሯል»* ተብሎ በብዙ ክርስቲያኖች ዘንድ ከመታመኑ አንጻር የተፈጠረው የታሪክ መጣረስ ያን ያህል አስገራሚ አይደለም።

[17] O Dhul-Qurneyn.ሱራ21:95-98። ሱራ18:93-96። ሐዲሽ ቅጽ4መጽ55ቁጥ565። Midrash wa,BhM.1:56.





## ጎግ ማን ነው?
## ማጎግስ የት ነው?

---

በመጨረሻው ዘመን በእስራኤል ላይ የሚዘምቱ መንግሥታት ማንነት በተመለከተ፣ በተለዩ ዘመናት የተለያዩ አስተያየቶች ሲሰጡ ኖረዋል። ይህም ከትንቢቱ ምስጢራዊነትና ለመተርጎም አስቸጋሪነት የሚመነጭ ነው። እኛም በዘመናችን፣ ትንቢቶችን ካለንበት ነባራዊ ሁኔታ ጋር እያነጻጸርን ቢያንስ አቅጣጫውን ብናመላክት፣ ክፋት አለው ብዬ አላስብም። ከዚህ አንጻር በዚህ ክፍል ወደ ፊት በእስራኤል ላይ እንደሚዘምቱ የሚጠረጠሩ መንግሥታት ማንነትና ወሳኝ የሚባሉ ትንቢታዊ ክስተቶችን እንመረምራለን። *«ምናልባት ይኼ የጎግ ማጎግ፣ ጦርነት፣ የሙስሊምና የአረቡ ዓለም ለእስራኤል ያለው መጠን የለሽ ተቃውሞና ጥላቻ ድንገት ገደቡን አልፎ በሚገነፍል ጊዜ የሚቀሰቀስ ይሆን?»* የሚለውን የአንዳንዶች ስጋት በመጠኑ እናያለን።

መቼም በዘመናት መኻል አልፎ እዚህ የደረሰውን የእስራኤል ታሪክ ሸናጠና የዚህች ትንሽ አገር ትልቁ ችግር፣ በየትኛውም ጊዜ ከአምላኳ በቀር ሁነኛ ወዳጅ ለማግኘት አለመታደልዋ ነው። በዚህም ምክንያት እስራኤል ሉአላዊት አገር ሆና ከተመሠረተችበት ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ጦርነት፣ ሽብርና ኹከት ተለይቷት አያውቅም። ምንም እንኳ በአንጻራዊት ሲታይ በሰሎሞን ዘመን የተረጋጋች መስላ ብትታይም፣ ያ ዘመን ግን ከዚያ በኋላ ለሆነው ውድቀቷና መበታተኗ መሠረት የተጣለበት በመሆኑ፣ እሱንም ቢሆን በበጎ እንዳናየው እንገደዳለን። ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ70 ዓ.ም በሮማውያን ከደረሰባቸው ጭፍጨፋ በኋላም፣ በየትኛውም አገር ተቀባይነት ሳያገኙ ነው የኖሩት። ታዲያ በነዚያ ዘመናት ራሳቸውን የክርስቶስ አገልጋዮች እንደሆኑ ከሚቆጥሩ አውሮውያን ከደረሰባቸው መከራ አንጻር፣ በሙስሊሞች የደረሰባቸው ችግር ብዙም የሚጋነን አይደለም። ይህ ሲባል ግን ሙስሊሞች በአይሁዳውያኑ ላይ ምንም ችግር አልፈጠሩባቸውም ማለት አይቻልም። በተለይ በ19ኛው ክፍለ

ዘመን መባቻ ላይ የጽዮናዊነት እንቅስቃሴ ማቆጥቆጥና መስፋፋት እንዲሁም አይሁዶች በፍልስጤም ምድር፣ እስራኤል የምትባል አገር ለመመሥረት ጥረት ማድረጋቸውን ተከትሎ በሁለቱ ሕዝቦች መኻል የተፈጠረው የጠላትነት ስሜት በየጊዜው ሲንር ነው የቆየው::

ከዚህ አንጻር የአሁኑ ዘመን የእስራኤልና የሙስሊም አገራት ግጭት መሠረቱን ያበጀው፣ አይሁዳውያኑ በፍልስጤም ምድር በብዛት መስፈራቸውን ተከትሎ ነው፣ ማለት ይቻላል:: ደግሞም እስራኤል በይፋ ከተመሠረተችበት ከግንቦት 1948 አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ፣ ከአረብና ከሙስሊም አገራት ጋር በግልጥና በስውር ጦርነት ውስጥ ነች:: አረቦች ከእስራኤል ጋር ያደረጓቸው ተደጋጋሚ ጦርነቶች ሁሉ በእስራኤል የበላይነት ነው የተደመደሙት:: በመሆኑም እስራኤል የተመሠረተችበት ቀንና ዓመት ለብዙ አረብ አገራት፣ የሐዘንና የቁጭት ቀናቸው ሆኖ ይታሰባል:: ከዚህ በተጨማሪ በአሁኑ ጊዜ ከአረቦቹ በተጨማሪ ኢራንን የመሳሰሉ አክራሪ አገራት፣ ለእስራኤል ዋነኛ ጠላት ሆነው እየተነሡ ነው::

በሌላም በኩል እስራኤላውያን በፓለስቲን ምድር ያላቸው የይገባኛል ጥያቄና መጽሐፍ ቅዱሳዊው መሠረት፣ ለብዙዎች አሳማኝ ሆኖ አይታይም:: በመሆኑም የወደፊቷ አውሮፓ እንኳ ከዚህም በላይ የእስራኤል ተጻራሪ ሆና እንደምትገለጥ ነው የሚጠበቀው:: ለዚህም ትንበያችን ምክንያት የሚሆኑ ተጨባጭ እውነታዎችን ልንጠቅስ ብንችልም ከሁሉም ይልቅ ግን አውሮፓ በኃይል አቅርቦትና ምንጭ አንጻር በመካከለኛው ምሥራቅ ያላት ተደጋፊነት ዋነኛው ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ግልጥ ነው:: ከዚህ ሌላ ዕለት፣ ዕለት አውሮፓዊ ዜግነት ያላቸው ሙስሊሞች ቁጥር እየጨመረ በመሄዱ፣ ተጽዕኗቸው የዚያኑ ያህል ከፍ እያለ ነው፤ በአንጻሩ አይሁዶቹ እንደ ጀርመንና ራሺያ ካሉ አገሮች ጋር ያላቸው የቆየ ጠላትነት፣ አሁንም ውስጥ ውስጡን ድረስ እየተብላላ ነው:: በዚህ ምክንያት ላለፉት ስልሳ ዓመታት በዚህ ሁሉ አጣብቂኝ ውስጥ ላለችው እስራኤል፣ ከአውሮፓ ይልቅ፣ ሁነኛ ወዳጅዋ አሜሪካ እንደነበረች ታይቷል:: ሆኖም በአሁኑ ጊዜ አሜሪካም ብትሆን በዚህች ትንሽ አገር ምክንያት ለዓመታት





በከፈለችው ዋጋ ደስተኛ አትመስልም:: ወደፊትም ከተለያየ አቅጣጫ የሚደርስባት ጫናና ተጽዕኖ፣ ጨርሶ ፊት እንድትነሣት ያስገድዳት ይሆናል የሚል ግምት አለ:: በቅርቡም የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ መካከለኛው ምሥራቅን በተመለከተ ባደረጉት ንግግር *«ወደፊት የሚመሠረተው የፍልስጥኤም መንግሥት የግዛት ክልል፣ ከ1967 በፊት የነበረው መሆን ይገባዋል»* ማለታቸው እስራኤልን ክፉኛ አስደንግጧል:: ከዚህ የተነሣ እስራኤል ያለ እውነተኛ አጋርና ደጋፊ ብቻዋን ተነጥላ የምትቀርበት ዘመን የቀረበ ይመስላል::

በመሬት ላይ ያለው እውነት ይህን ቢመስልም እስራኤል ሦስተኛውን ቤተ መቅደስ ለመሥራት ከመዘጋጀት እንድትታቀብ አላደረጋትም:: አሁን እንዳለው ነባራዊ ሁኔታ ቢሆን ኖሮ ግን ይህ ጨርሶ መታሰብ አልነበረበትም:: ዳሩ ግን ጉዳዩ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር የዘመናት ዕቅድ ነውና እንዲህ ሊሆን ችሏል:: እንደ ሚባለውማ፣ አይሁዳውያኑ በአሁኑ ጊዜ የቤተ መቅደሱን ፕላን ከማዘጋጀት አልፈው፣ በመቅደሱ ውስጥ ለአገልግሎት የሚያስፈልጉ ንዋያተ ቅድሳትን ሁሉ አሟተው በመጠባበቅ ላይ ነው የሚገኙት:: ሆኖም እነርሱ ቤተ መቅደሱን መሥራት በሚፈልጉበት በቀድሞው ስፍራ ላይ፣ በአሁኑ ጊዜ «ዶም ኦፍ ዘ ሮክ» የተባለው ባለወርቃማው ጉልላት መስኪድ መኖሩ፣ አሳባቸውን ቶሎ እንዳይፈጽሙ እንቅፋት ሆኖባቸዋል:: በአንጻሩ ሙስሊሞች ከዚያ ስፍራ *«መሐመድ ወደ መንግሥተ ሰማያት ተነጥቀውበታል»* ብለው የሚያምኑ ከመሆኑ ሌላ ከመካና መዲና ቀጥሎ ሦስተኛው ቅዱስ ስፍራቸው አድርገው ነው፣ የሚያዩት:: በመሆኑም ወደ ፊት አይሁዳውያኑ እንዴት ባለ መንገድ መቅደሱን እንደሚሠሩት በዛሬው ጊዜ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው::

እንደ ባለ አእምሮ ሲታሰብ ግን ነገሩ የዕብደት ያህል የሚያስፈራ ነው:: ደግሞም ማንም ሙስሊም፣ በእርሱ ዘመን፣ መስኪዱ ፈርሶ «በቅዱሱ» ስፍራ ላይ ቤተ መቅደሱ እንዲሠራ እንደማይፈቅድ ሳይታለም የተፈታ ነው:: በርካታ የሙስሊም ተጽዕኖ ፈጣሪና ተደማጭነት ያላቸው ሰዎችም፣ መስኪዱ ያለበት ስፍራ በምንም መልኩ የተነካ ዕለት፣ ሦስተኛው የዓለም ጦርነት እንደሚቀሰቀስ

በተደጋጋሚ ዝተዋል:: በእርግጥም በአሁኑ ጊዜ ከዓለም የሕዝብ ቁጥር ሃያ ከመቶ የሚሆኑት ሙስሊሞች መሆናቸውና ከእነርሱም አብዛኛዎቹ የነዳጅ ዘይት ባመጣላቸው ድንገተኛ ብልጥግና አቅማቸው እንደመጎልበቱ መጠን፣ ዛቻቸው ተራ ዛቻ እንደሆነ ብቻ አድርጎ መቁጠር የዋህነት ነው:: ምንም ቢሆን ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች መፈጸም ስላለባቸው ቤተ መቅደሱ በስፍራው መሠራቱ አይቀርም:: ምናልባት ሦስተኛው ቤተ መቅደስ በስፍራው እንዲሠራ ይህ የዓለም ኃይል አስቀድሞ ይወገዳልን? ይህስ የጎግ ማጎግ ጦርነት ለዚያ የፍጻሜው ቀን የሚያቻኩል ይሆን እንዴ?

በእርግጥ ከ2500 ዓመታት በፊት በምድር ላይ የነበረው ነብዩ ሕዝቅኤል እንደተነበየው፣ የጎግ ማጎግ ጦርነት የሚሆነው እስራኤል ከተበተነችበት ተሰብስባ እንደ አገር መኖር ከጀመረች በኋላ በሚሆን አንድ ዘመን መኻል ነው:: ታዲያ የሕዝቅኤል ትንቢት በግልጥ እንደሚነግረን በወቅቱ እስራኤል በጠላቶች ተከባ የምትኖር አገር መሆን አለባት:: ጦርነቱም፣ የእስራኤል ዓይነተኛ ጠላቶችና እነርሱን የሚደግፉ አገሮች በአንድ ወገን፣ እንዲሁም እስራኤል በሌላው ወገን ሆና የሚደረግ ነው:: ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ ለጦርነቱ መቀስቀስ ዋነኛ ምክንያት ስለሚሆነው ነገር በግልጥ ባይነግረንም አንዳንድ ተያያዥ ጉዳዮችን በማስላት ምናልባት ጦርነቱ ከመቅደሱ መሠራት ጋር የተያያዘ ሊሆን እንደሚችል ይጠረጠራል፤ ሕዝቅኤልስ ቢሆን ስለዚያ ጦርነት ተርኮ እንዳበቃ፣ ወዲያው ስለቤተ መቅደሱ ማውሳቱ፣ ይኼኑ ለማመልከት ይሆን?

የጎግ ምድር የሆነውን ማጎግን ጨምሮ፣ በጦርነቱ እንደሚካፈሉ የተነገረላቸው አገሮች ማንነትም አከራካሪ ነው:: በእርግጥ በጦርነቱ በቀጥታ ከሚሳተፉ አገሮች መኻል በተለይ ፋርስ ወይም ኢራን፣ ኩሽ ወይም ኢትዮጵያ፣ ፉጥ ወይም ሊቢያ፣ ጎሜርና ቴርጋማን የሚባሉት አገሮች ማንነታቸው በውል ታውቋል:: በመሆኑም በርካታ የነገረ መለኮት ተመራማሪዎች፣ ከታሪክ፣ ከስምና ከመልክአ ምድራዊ አቀማመጥ አንጻር ሕዝቅኤል የጎግ ምድር እንደሆነ የጠቀሰው አገር፣ የአሁኗ ሩሲያ ያለችበት ስፍራ እንደሆነ እርግጠኛ ሆነዋል:: በእርግጥ





ከመልክአ ምድር አቀማመጥ አንጻር፣ ሩሲያ ከእስራኤል ሩቅ ሰሜን መገኘትዋ ግልጥ ነው::[18] ከሩሲያ ጋር አብረው በእስራኤል ላይ ከሚዘምቱ አገራት መኻል ኢራንና ሊቢያን የመሳሰሉትን ማካተቱ፣ ጦርነቱ በሙስሊም አገራት ኅብረትና በእስራኤል መኻል የሚደረግ እንደሆነ ተደርጎ እንዲገመት ፍንጭ ሆኗል:: ምንም እንኳ ኢትዮጵያ የምትባለው አገር በጥንት ዘመን ያላት የግዛት ክልል አሁን ካለው እጅግ የተለየ ቢሆንም፣ ከእነዚሁ አገራት ጋር ስሟ መጠቀሱ ግን አልቀረም:: ምናልባትም አሁን ባለው ሁኔታ «ኢትዮጵያ» በመባል የተጠቀሰው ቀድሞ በግዛትዋ ስር የነበሩትን፣ ሱዳንን፣ ኤርትራን፣ ሶማሊያን፣ ጂቡቲንና የመንን የሚመለከት ይሁን ወይም ያሁኗን ኢትዮጵያ ግልጥ አይደለም:: በበኩሌ ኢትዮጵያ ወደፊት ታገኛለች የሚባለውን የፈጣን ዕድገት «ትንቢት» ከመንፈሳዊ ነብያትም ሆነ ከፖለቲከኞቹ ስሰማ፣ ይህቺ አገር ለዚያ የጥፋት ቀን እየቸኮለች ይሆን እንዴ? እያልኩ እሳቀቃለሁ::

ከዚህም ሌላ የጎግ ማጎግ ጦርነት የሚሆንበትን ጊዜ በተመለከተ ሌላ እጅግ አከራካሪ ነገር አለ:: በዚሁ መሠረት አንዳንድ ሰዎች *«ጊዜው፣ ከታላቁ መከራም ሆነ፣ ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በፊት ነው»* ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ *«በቤተ ክርስቲያን መነጠቅና በታላቁ መከራ መኻል ነው»* ይላሉ:: ይህ ብቻ ሳይሆን ከዚህ የተለየ አመለካከት ያላቸውም አሉ፤ እነርሱም ጊዜው ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በኋላ በሚሆን የታላቁ መከራ ወቅት እንደሚሆን የሚያምኑ ናቸው:: በተጨማሪም ወቅቱን ከሌላኛው የጎግ ማጎግ ጦርነት ጋር የሚያያይዙትና ከሺው ዓመት ፍጻሜ በኋላ እንደሚሆን የሚናገሩ አሉ::[19]

> ሺሁም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል፤ በአራቱ የምድር ማእዘናት ያሉትን ሕዝቦች፣ ጎግንና ማጎግን አያሳተ ለጦርነት ሊያሰልፋቸው ይወጣል፤ ቁጥራቸው በባሕር ዳርቻ እንዳለ አሸዋ ነው:: እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ ወጥተው የቅዱሳንን ሰፈርና የተወደደችውን ከተማ ከበቡ፤ ነገር ግን እሳት ከሰማይ ወርዶ በላቻው::

[18] ሕዝ38: 15::
[19] ራእ20:7-8::

ይህ የጦርነት ዘመን ከመነጠቅና ከታላቁ መከራ በፊት ባለ ዘመን እንደሆነ የሚያምኑ ሰዎች፣ እስራኤላውያን ከጦርነቱ በኋላ እንደ ሚኖራቸው የተነገረው ሰባት ዓመት ዋና የመከራከሪያ ምክንያታቸው ነው:: እነዚህም ሰዎች የሚሉት እንዲህ ነው::

*እነዚህን ሰባት ዓመታት በታላቁ መከራ ዘመን ማግኘት አይቻልም:: ሕዝቅኤል፣ በእነዚያ ዘመናት በእስራኤላውያን ተሰብስቦ እንደሚቀበር የተናገረው የሬሳ ብዛትም፣ ከታላቁ መከራ በፊት በሚሆን ዘመን፣ የተለየ ጊዜ እንዳለ የሚያመለክት ነው:: ክስተቱ እግዚአብሔር በእስራኤል በኩል ሙሉ ለሙሉ ራሱን ለዓለም የሚገልጥበት ከመሆኑ አንጻር፣ የትንቢቱ ዋነኛ ክፍል አድርገን እንድናየው እንገደዳለን:: ይኼም ለብዙ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ምክንያት እንደሚሆን የተነገረለት ነው::*

ነገር ግን ወቅቱ፣ ከታላቁ መከራም ሆነ፣ ከንጥቀት በፊት ፈጽሞ እንደማይሆን የሚከራከሩ ሰዎች፣ እንዲህ የማይሆንበትን ምክንያት ሲያቀርቡ በዋነኝነት የሚያነሡት በትንቢቱ ውስጥ የተጠቀሰውን በ«ኋለኛው ዘመን»[20] የሚለውን ቃል ነው:: እነዚህም ሰዎች እንዲህ በማለት ይከራከራሉ:: ፣

*በአዲስ ኪዳን ከተነገሩ ትንቢቶች ውስጥ በየትም ስፍራ ላይ እንዲህ ያለ ታላቅ ክስተት ከመነጠቅ ወይም ከታላቁ መከራ በፊት እንደሚሆን አልተነገረም፤ በመሆኑም "የኋለኛው ዘመናት" የተባሉት፣ የታላቁ መከራ ዘመናት በመሆናቸው፤ ትንቢቱ የሚናገረው ስለሰባኛው ሱባኤ ነው:: የጎግ ማጎግ ጦርነት ከመሆኑ በፊት ባለው ጊዜ እስራኤል ከየኛውም ወገን ጥቃት እንደሚደርስባት ስለማትጠረጥር፣ ያለ ቅጥርና በር ነው የምትኖረው:: ይህ እንዲሆን ደግሞ አስቀድማ በሰባኛው ሱባኤ ከሚነሣው የዓለም መሪ ጋር የተለየ ስምምነት መፈራረም አለባት::*

ነገር ግን እነዚህ ሰዎች በሕዝቅኤል ትንቢት ላይ የተገለጡትንና ከጦርነቱ በኋላ ያሉትን ሰባት ዓመታት ከየት ሊያመጧቸው

[20] ሕዝ38:16:: ምድርን እንደሚሸፍን ደመና ሆነህ በሕዝቤ በእስራኤል ላይ ትወጣለህ:: ጎግ ሆይ፤ በፊታቸው ቅድስናዬን ስገልጥ ሕዝቦች እኔን ያውቁ ዘንድ በኋለኛው ዘመን በምድሬ ላይ አመጣሃለሁ::





እንደሚችሉ ግልጥ አይደለም:: ይኼም ከእነሱ የተለየ ዕይታ ላላቸው ሰዎች የሙግት በር ከፍቷል:: በዚህ መሠረት ሌሎች ሰዎች፣ ይህ የጎግ ማጎግ ዘመን፣ ከመነጠቅ በኋላ፣ ነገር ግን ከታላቁ መከራ በፊት እንደሚሆን በማመን አስረግጠው ይናገራሉ:: እነዚህም ሰዎች ይኼን ለምን እንደሚሉ ሲያስረዱ እንዲህ ያብራራሉ::

*በቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ምክንያት በዓለም ላይ ኃይለኛ ረብሻና ኹከት መፈጠሩ አይቀርም፤ ታዲያ ይኼን ያለመረጋጋት ተከትሉ ራሺያ ከሙስሊሞች ጋር በመሆን እስራኤልን ለመውረር ትነሣለች:: በወቅቱ እስራኤል፣ ሩሲያም ሆነች ሙስሊሞች እሷን ለመውረር የሚያስችል በቂ ምክንያት እንዳላቸው ስለማትጠረጥር፣ ያለቅጥርና በር ተረጋግታ የምትኖርበት ዘመን ይሆናል:: ቢሆንም ራሺያና ሙስሊሞች ከፉኛ ይሸነፋሉ:: ጦርነቱ ግን ለአውሮፓ ልዕለ ኃያል ሆኖ መነሣት አጋጣሚውን ይፈጥርላታል፤ በወቅቱ አውሮፓ በአካባቢው ያለውን የኃይል አቅርቦት ምንጭዋን አስተማማኝ ለማድረግ ስለምትሻ፣ የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮችን በሙሉ ተቆጣጥራ ከእስራኤል ጋር የሰላም ስምምነት የመፈራረም ዕድል ያስገኝላታል:: እስራኤልም በወቅቱ በአካባቢው ያን ያህል ተፎካካሪ ስለማይኖርባት «ዶም ኦፍ ዘ ሮክ» የተባለውን መስኪድ አፍርሳ መቅደሱን ያለ ከልካይ ሠርታ ትፈጽመዋለች::*

ሆኖም ሌሎች ሰዎች ከላይ የተባለውን ሁሉ ፈጽሞ አይቀበሉትም፤ እንደነዚህ ሰዎች እምነት ከሆነ በመነጠቅና በታላቁ መከራ መኻል የሦስት ዓመት ተኩል ጊዜ ይኖራል እንጂ፣ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በፍጹም ለታላቁ መከራ መጀመር ምክንያት አይሆንም:: *«ሰባኛው ሱባኤ ሲገባም፣ እስራኤል በአውሮፓ ከሚነሣው መሪ ጋር ለሰባት ዓመት የሚቆይ ስምምነት ታደርግና ለሦስት ዓመት ተኩል ያህል በሰላም ተረጋግታ ትኖራለች»* ነው፣ የሚሉት:: በእርግጥ እነዚህ ሰባት ዓመታት፣ በሕዝቅኤል ላይ የተጠቀሱትን ሰባት ዓመታት ይመስላሉ:: ደግሞም *«ከእስራኤል ጋር ስምምነቱን የሚፈራረመው መሪ፣ ስምምነቱን ጥሶ በቤተ መቅደሱ የጥፋት ርኩሰቱን የሚያቆመው ከዚህ በኋላ በሚሆኑት የሦስት ዓመት ጊዜአት ውስጥ ነው»* ብለውም ያምናሉ:: ይኼም በሦስት በተከፈሉና በድምሩ ከአስር ዓመት

ተኩል በላይ በሆኑ ጊዜአት ውስጥ የሚጠናቀቅ ነው:: ሆኖም ይኼን አሳብ «የኋለኛው ጊዜ» ከሚለው ዘመን ጋር ለማስማማት ቀላል አይሆንም:: በዚያ ላይ *«እስራኤል ቅጥርዋ ፈርሶና ተዘልላ የምትኖረው ከሰላም ስምምነቱ በኋላ ብቻ ነው::»* ለሚለው የአንዳንድ ሰዎችን ጽኑ እምነት ሊያሸንፍ የሚችል አቅም ሲያንሰው ይታያል:: እነዚህ በሦስት ምዕራፎች የተከፋፈሉ፣ የሦስት ዓመት ተኩል ጊዜአትም ቢሆኑ በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ውስጥ በግልጥ የሚገኙ ባለመሆናቸው «አሜን» ብሉ ለመቀበል ይፈትናሉ::

አንዳንድ ሰዎችም «ጎግ» ተብሎ የተጠራው «ሐሰተኛው ክርስቶስ» እንደሆነ ያስባሉ:: ለዚህም ማስረጃ አድርገው ከሚያቀርቧቸው ምክንያቶች አንዱ «በቀደመው ዘመን በባሪያዎቹ በእስራኤል ነብያት ስለእርሱ የተናገርኩለት ያ ሰው አንተ አይደለህምን? በዚያን ወቅት በእነርሱ ላይ እንደ ማመጣባቸው ለብዙ ዓመታት ትንቢት ተናገሩ» የሚለውን የትንቢቱን ክፍል ነው:: በእርግጥም ከዚህ ውጪ ባሉ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሐሰተኛ ክርስቶስን አስመልክቶ የቀረቡት የተለያዩ ስሞች ለዚህ ትርጉም መሠረት ሳይሆናቸው እንዳልቀረ ይታሰባል:: ከነዚህም መኻል አንዳንዶቹን ብንመለከት፣ የሚመጣው አለቃ፣ አውሬው፣ አሦር፣ የሰሜኑ ንጉሥ፣ የጥፋት ልጅ፣ ክፉው፣ የባቢሎን ንጉሥና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ:: ሆኖም *«በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ጎግ፣ ሐሰተኛው ክርስቶስ ነው»* ብሉ በእግጠኛነት ለመናገር አስቸጋሪ ነው::





## እስልምና

ተከራይቼ የምኖርበት ቤት ባለቤቶች፣ ሙስሊሞች ናቸው:: እውነት ለመናገር የቤቱ ጥራት ብዙም አልተስማማኝም:: ነገር ግን አከራዮቼ ከምንም ይልቅ ስለተመቹኝ ወደ ቤቴ ስገባ ደስ እያለኝ ነው:: ምንም እንኳ ከእምነቴም ሆነ ከባህርዬ አንጻር፣ የማንንም ሰው መብት ባለመንካት አክብሮቴን ለመግለጥ ፍላጎቴ ቢሆንም፣ እነርሱ ከእኔ ይልቅ፣ መብቴን ለመጠበቅ ምን ያህል እንደሚጠነቀቁ ሳይ እገረማለሁ:: በአንጻሩ የወላጆቼን ቤት ተከራይተው የሚኖሩት ሙስሊሞች ናቸው፤ እንደማስበው እነርሱ እንደውም ከእኔ ይልቅ የተመቻቸው ይመስለኛል:: ልጆቻቸው ከእኅቴ ልጆች ጋር አብረው እያደጉ ነው፤ በህፃናቱ መኻል መብልን ጨምሮ የክርስቲያን ወይም የእስላም የሚባል ምንም ነገር የለም:: እነዚህ ጨቅላ ህፃናት ወደፊት ሌላ ሰው እስኪነገራቸው ድረስ በመኻከላቸው ስላለው ሰፊ የእምነትና የታሪክ ልዩነት አንዳች ነገር አያውቁም:: ምንም እንኳ ዛሬ፣ ዛሬ አንዳንድ ደስ የማይሉ ነገሮች እየታዩ ቢሆንም ለዘመናት አያሌ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያንና ሙስሊም ሕዝቦች የኖሩት እንዲሁ ነው::

✡ 🕮 ✡

ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ570 «አብድ አላህ ኢብን አብድ አል ሙታሊብ» እና «አሜናህ» የተባሉ ባልና ሚስት፣ በሙሉ ስሙ «አቡ አልካዚም መሐመድ ኤቢን አብድ አላህ ኤብን አብ አል ሙታሊብ ኤብን ሐሺም» የተባለ ወንድ ልጅ በመካ ከተማ ወለዱ፤ ይኼም ልጅ እንደ ማንኛውም ህፃን ከቤሰቦቹ አብራክ ከመገኘቱ በቀር አንዳች የተለየ ምልክትም ሆነ ትንቢት አልተነገረለትም ነበር:: ዛሬ ግን በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች፣ ከአክብሮት በላይ፣ ከማምለክ በማይተናነስ ሁኔታ የሚያነሷቸው፣ የእስልምና ሃይማኖት መሥራችና መሪ ሆነዋል::

መሐመድ፣ አባታቸውን በሞት ያጡት በዚያው በተወለዱበት ዓመት ነበር፤ ስድስት ዓመት ሲሆናቸው ደግሞ እናታቸውን ሞት ነጥቋቸዋል። በዚህ ምክንያት ያደጉት በአጎታቸው እጅ ነው። የወጣትነት ዕድሜ ላይ ሲደርሱም በቆየው የአረቦች ልማድና ሥርዓት መሠረት፣ በዚያ ያለው ሕይወትና የሕዝቡን አኗኗር ተላምደው መከራ ቻይነትንና ጽናትን እንዲማሩ፣ ከነጋዴዎች ጋር ወደ በረሀ ተላኩ። የበረሀ ትምህርታቸውን በአጥጋቢ ሁኔታ ያጠናቀቁት መሐመድም ከቆዩበት ተመልሰው እንደገና ከአጎታቸው ጋር መኖር ጀመሩ። አጎታቸውም ስለንግድና መጓጓዣ ትምህርት ሰጥተው ደኅና አድረገው አሰለጠኗቸው። ቀልጣፋና ብሩህ አእምሮ እንደነበራቸው የሚነገርላቸው መሐመድ ቃላቸውን የሚጠብቁ በመሆናቸው፣ በመካውያን ዘንድ «ታማኙ ሰው» በሚለው ስማቸው ታዋቂ ሆኑ። ትንሽ እንደቆየም «ከድጃ» የተባሉ ሀብታም ሴት አግብተው ለሃያ አንድ ዓመታት አብረው ኖሩ። የቀሩትን ዘጠኝ ሚስቶቻቸውን ያገቡት ግን ከድጃ ከሞቱ በኋላ በየተራ ነው።[21]

መሐመድ በተወለዱበትና ባደጉበት ዘመን በሌላኛው ጫፍ የነበረችው አውሮፓ፣ ወደ አስከፊው የጨለማው ዘመን ታዘግም የነበረች ሲሆን ቤተ ክርስቲያንም እርስ በእርሷ ተከፋፍላ እንዲሁም ከመንግሥታት ጋር ተጋብታ በዓለም ላይ የነበራት ተጽእኖ የተገደበበት ዘመን ነበር። ይኼም ዘመን በተለይ ለቤተ ክርስቲያን የጨለማው ዘመን የጀመረበት ጊዜ ነበር ለማለት ይቻላል።

መሐመድም በመካና በአካባቢው የነበረው ማንኛውም ሃይማኖታዊም ሆነ ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ደስ ሊያሰኛቸው አልቻለም። በሰዎች መኻል ያለው ግንኙነት በራስ ወዳድነት፣ በስግብግብነትና በጀብደኛነት የተቃኘ መሆኑ ሲያዩት እርካታ አጡበት። በተለይ ሴት ሕፃናት ሲወለዱ «እርግማን ናቸው» እየተባሉ ከነሕይወታቸው የሚቀበሩበት ሥርዓት በፍጹም የሚቀበሉት አልሆነም። በዚያ የሚገኙ ሦስት መቶ ስልሳ ጣኦታት ደግሞ ለኃጢአተኞች መሸሸጊያ

[21] አብዛኛዎቹ አሳቦችን የተወሰዱት፣ The Arabs: Journeys Beyond the mirage: David Lamb 1987 ነው፤





ከመሆን ባለፈ መንፈሳዊ ጥያቄዎቻቸውን የሚፈቱ ሆነው አላገኟቸውም። በወቅቱም ጥቂት የማይባሉ አይሁድና ክርስቲያኖችም በዚህ የተዘበራረቀ ሕይወት ውስጥ እስከ አንገታቸው መዘፈቃቸውን ሲያዩ የበለጠ ግራ ተጋቡ። እናም ስለጉዳዩ ለማሰላሰል ሌሊት፣ ሌሊት በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ ዋሻ መሄድ የዘወትር ተግባራቸው እንዳደረጉት ይነገራል።

ከእነዚህም ሌሊቶች በአንዱ፣ ከደወሎችና ከድምፅ ጋር «አንብብ!» እያለ የሚወተውትና የሚጮኽ ድምፅ ሰሙም ይባላል። ጊዜውም በሮመዳን ወር 610 ላይ ነው። መሐመድ ግን በጊዜው እጅግ ተደናግጠው ያበዱም መሰላቸው። ነገር ግን በወቅቱ «ኢብን ኖፋል» የተባሉና የከድጃ የአጎት ልጅ የሆኑ ሰው፣ መሐመድን፣ እንዳላበዱ፣ ነግረው አረጋጓቸው። ደግሞም የተገለጠላቸው፣ መልአኩ ገብርኤል እንደሆነና እሳቸውም የአምላክ መልዕክተኛ እንደሆኑ ስላግባቧቸው፣ የነገሯቸውን ተቀብለው እርፍ አሉ። እኚህ የመሐመድ ታሪክ በተነሣ ቁጥር አብረው የሚነሡት ሰው ደግሞ ከ«ክርስቲያን» ወገን ነበሩ ይባላል። ምንም እንኳ የባለቤታቸው የአጎት ልጅ የሰጧቸው ምክር ቢያጽናናቸውም መሐመድ ግን ነገሩን በልባቸው እያሰላሰሉና ለዘመዶቻቸው እያማከሩ ሰነበቱ። እንግዲህ ከእነዚህ ጉልህ ክስተቶች በኋላ ነው፣ በመካከለኛው ምሥራቅ ከፍተኛ ተጽእኖ ያለው አዲስ ሃይማኖት እንዲፈጠር ምክንያት የሆኑት።

መሐመድ የጀመሩት አዲስ ሃይማኖት ማንም ከማንም የማያበላልጥ ጥብቅ በሆነ ማኅበራዊ ሥርዓት የተዋቀረና በአምላክ አንድነት የሚያምን ሲሆን «እስልምና» ይሰኛል። ስርዎ ቃሉም ከአረብኛ እንደተገኘ ሲታመን፣ ፍቺውም እጅ መስጠት እና መገዛት ማለት ነው። ደግሞም *«ከአላህ በቀር የሚመለክ የለም፤ የአምላክ መልዕክተኛም መሐመድ ብቻ ናቸው»* ብለው የሚያምኑ «ሙስሊም» ይባላሉ። የእስልምና ዋና መመሪያ መጽሐፍ «ቁርአን» ሲባል፣ እርሱም በሙስሊሞች ዘንድ ከሰማይና ከአላህ ዘንድ ለመሐመድ እንደ ወረደላቸው ነው የሚታመነው። ቁርአን 114 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ሆኖ፣ ዋና ቅጂውም በአረብኛ ተጽፎ የሚገኝ ነው። ሆኖም

ቍርአን ሃይማኖታዊ ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መመሪያዎችን ሁሉ አካቶ በመያዙ ለብዙ ሙስሊሞች ያለው ፋይዳ ብዙ ነው።

መሐመድ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት በወገኖቻቸው ዘንድ ብዙም ተቀባይነት ስላላገኙ በፈቃዳቸው የተከተሏቸው ሰዎች ብዛት ከሠላሳ አይበልጥም ነበር። እነርሱም ቢሆኑ በመካ ባሉ ጣኦት አምላኪዎች ከፍተኛ ጫናና ማስፈራሪያ ስለደረሰባቸው ለተወሰነ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ተሰደዱ። አጎታቸውና ሚስታቸው በመካ የነበራቸው ተቀባይነት ከለላ ስለሆናቸው እንጂ፣ መሐመድ ራሳቸው ለአደጋ የተጋለጡባቸው ጊዜያት ነበሩ። ሆኖም በ619 የሚስታቸው ከድጃና የአጎታቸውን አቡ ታሊብ መሞትን ተከትሎ ዋስትና ስላጡ፣ ወደ መዲና ተሰደዱ። እንግዲህ የእስልምና የቀን አቆጣጠር፣ ከ620 የሚጀምረው ይኼን የታሪክ አጋጣሚ ተከትሎ ነው።

መዲና በዚያን ዘመን «ያትሪብ» የምትባል ሲሆን ከመካ በስተሰሜን 339 ኪሎ ሜትር ርቃ ትገኛለች፤ መሐመድም በማያውቋቸው ሰዎች መኻል መገኘታቸው እምነቱን ለማሰራጨት ተመቻቸው፤ በከተማዋ በሚኖሩ ጎሳዎች መኻል የነበረውን አለመግባባት እንዲሸመግሉም ተመራጭ ሆኑ። በወቅቱ መዲና ብዙ አይሁዳውያን የሚኖሩባት ታላቅ ከተማ ነበረች። አይሁዳውያኑም በአንድ አምላክ የሚያምኑ በመሆናቸው እምነታቸውን አሜን ብለው የሚቀበሉ መስሎአቸው ነበር። ደግሞም የእርሳቸው ሃይማኖት ከይሁዲ እምነት ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ለማስረዳት ብዙ ደከሙ፤ የአይሁዳውያኑን የዮም ኩፐር ጾም ጾሙ፤ መሐመድም ሆኑ ተከታዮቻቸው ፊታቸውን ወደ ኢየሩሳሌም ዞረው መስገድ ጀመሩ። ይኼን እያደረጉ አይሁዳውያን ከእሳቸው ጋር ጣኦት አምላኪዎችን እንዲፋለሙ ጥሪ ማቅረባቸውን ቀጠሉ። አይሁዳውያኑ ግን የመሐመድን አረብነት ተመልክተው ነብይነታቸውን ለመቀበል በጄ አልል አሉ። «ተገለጠልኝ» የሚሉትም አዲስ እምነት በምንም ዓይነት ሁኔታ ከእነርሱ መጽሐፍ ጋር ሊያስታርቁት አልቻሉም። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በንግዱ አንጻር በመኻላቸው የነበረው ውድድር፣ በአይሁዶችና





በመሐመድ ተከታዮች መኻል የነበረውን አብሮነት አሻከረው። ቀስ በቀስም እርስ በእርስ የነበራቸው መከባበር እየቀረ፣ አይሁዳውያኑ በመሐመድና በተከታዮቻቸው ላይ መሳለቅ በጀመሩ ጊዜ፣ አብረው ለመኖር የምታስችላቸው እንጥፍጣፊ ተስፋ ጨርሳ ከሰመች።

በወቅቱ መሐመድና ተከታዮቻቸው፣ አይሁዳውያኑን ከዚያ በላይ የሚታገሱበት አቅም አልነበራቸውምና እነሱም በበኩላቸው ልዩነቱን በማስፋት በኩል ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ይነገራል። መሐመድም ከጥቂት ጊዜያት በኋላ በተለየ ሁኔታ እንደተገለጠላቸው በማስታወቅ ጸሎቱ ከኢየሩሳሌም፣ ወደ መካ አቅጣጫ እንዲዞር አደረጉ፤ የዮም ኮፐር የሃያ አራት ሰዓት ጾምም በሮመዳን ወር ሆኖ፣ ቀን ብቻ እንዲደረግ ወሰኑ። ደግሞም ሰባተኛውን ቀን ማለትም፣ ቅዳሜን ማክበር ትተው፣ የጸሎትና የስግደት ቀናቸው ዓርብ እንዲሆን ደነገጉ። እንግዲህ ከዚህ በኋላ ነው፣ እስልምና የራሱን መልክና ቅርጽ ከአረባዊነት ጋር የተጎናጸፈው። ቁርአንም በአንዳንድ ክፍሎቹ አይሁዶችን አጭበርባሪና የእስልምና ጠላት እንደሆኑ የሚገልጣቸው በዚህ ምክንያት እንደሆነ ይገመታል። እነዚህ ጎምዛዛ ፍሬዎች ግን ለዛሬው የሙስሊምና የአይሁድ ተቃርኖ ቀድመው የተዘሩ ፍሬዎች ነበሩ።

ይህ በዚህ እንዳለ፣ በመዲና አካባቢ በተደረገ ጦርነት አይሁዶች ሙስሊሞችን ለመርዳት እንቢ በማለታቸው ቂም ተያዘባቸው። ቆይቶም ሙስሊሞቹ አይሁዳውያኑን አባብለውና አግባብተው ትጥቅ ካስፈቷቸው በኋላ ከእነርሱ 600 የሚሆኑትን ወንዶች አንገታቸውን እየቀሉ ገደሉ፤ ሕፃናትና ሴቶችንም ባሪያ አድርገው ወሰዱ። ያም ሆኖ በጥንታዊው የአይሁድና የሙስሊም ታሪክ፣ ሙስሊሞች በተደራጀ ሁኔታ፣ በአይሁዶች ላይ ጥቃት ያደረሱት እዚህ ስፍራ ብቻ እንደሆነ ይነገራል።

ምንም እንኳ መሐመድ ፍትህን መተዛዘንንና በሰዎች መኻል ሊኖር ስለሚገባ እኩልነት ያስተማሩ ቢሆንም እስልምና ግን በአብዛኛው የተስፋፋው በግጭትና በጦርነት ነው። ከእነዚህም ጦርነቶች በ630

መካን ለመያዝ የተደረገው ጦርነት ጎልቶ ይጠቀሳል:: አስር ሺ የሚሆኑ የመሐመድ ተከታዮች መካን ከያዙ በኋላ ካባህ ውስጥ የነበሩ ጣኦታትን በሙሉ አወደሙ፤ በዚያኑ ቀን ከባርነት ነፃ የወጣና ስሙ «ቢላል» የተባለ ሐበሻ፣ እጆቹን እንደ ድምፅ ማጉያ በአፉ ላይ አኑሮ *«አላህ ታላቅ ነው፤ አላህ እንጂ ሌላ የሚመለክ እንደሌለ አምናለሁ፤ መሐመድም የአላህ ነብይ እንደሆኑ አምናለሁ»* ሲል የመጀመሪያውን የሙአዚኖች የጸሎት ጥሪ አደረገ:: ከዚያን ቀን ጀምሮ በመካ ይኖር የነበረ ሰው ሁሉ በአብዛኛው እስልምናን በውድና በግድ ተቀበለ:: ቀጥሎም መሐመድ ለዓለም መሪዎች እስልምናን እንዲቀበሉ በደብዳቤ ጥሪ አደረጉ:: ከእነዚህም መካል የኢትዮጵያ፣ የፋርስ፣ የግብጽና የባዛንታይን ነገሥታት ይጠቀሳሉ::

ይህ ሁሉ ከሆነ ከሁለት ዓመት በኋላ መሐመድ በጽኑ ታመሙ፤ በምድር ላይ የሚቆዩበት ዕድሜ አጭር እንደሆነ ባወቁ ጊዜም ተከታዮቻቸው እስልምናን በዓለም እንዲያሰራጩ አደራ አሏቸው:: ሰኔ 8 ቀን 632 መሐመድ ይህን ዓለም በሞት ተለዩና በመዲና ባለ በአንድ መስኪድ አቅራቢያ ተቀበሩ:: እስልምናን በኃይል ከተቀበሉ ጎሳዎች መካል አንዳንዶቹ የመሐመድን መሞት የሰሙ ዕለት ለማመጽ ዳድቷቸው ነበር:: ነገር ግን እሳቸውን የተኳቸው «አቡበከር አል ሰዲክ» ወታደሮቻቸውን ልከው ወደ እስልምና እንዲመለሱ ስላስጠነቀቋቸው ዐመጹ በዚያው ተዳፈነ::

መሐመድ ከሞቱ አስር ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የእስልምና ስርጭት አድማስ ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ ሰፊ ግዛት አካለለ፤ በአንዳንድ ስፍራዎችም ጭቆና ይደርስባቸው የነበሩ ክርስቲያኖች ሳይቀሩ እንደ ነፃ አውጪና የአምላክ መልዕክተኛ አድርገው ስለቆጠሯቸው ለወራሪዎቹ የሞቀ አቀባበል አደረጉላቸው:: ሙስሊሞች፣ ግን ጦርነቱን እምነትን ከማስራጨት ባለፈ ለምጣኔ ሀብት ግንባታ ተጠቀሙበት:: በዚህም ምክንያት መቶ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እስልምና ከቻይና ድንበር እስከ ስፔን ጠረፍ ዘለቀ፤ የሰሜን አፍሪካና የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮችም ሙሉ ሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ የእምነቱ ማዕከላት ሆኑ::





ለመሐመድ ከሰማይ ወረደላቸው በሚባለው ቁርአን ውስጥ ያሉ አንዳንድ አሳቦች፣ የአይሁድና ክርስቲያኖች ዋና መመሪያ ከሆነው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቃል በቃል የተቀዱ እስኪመስል ድረስ፣ አንድ ዓይነት ሆነው የሚገኙበት አጋጣሚ ብዙ ነው:: በዚህ ምክንያት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁነኛ ስፍራ ያላቸው እንደ አዳም፣ ኖኅ፣ አብርሃም፣ ኢስማኤል፣ ያዕቆብ፣ ሙሴ፣ ኢዮብ፣ ማርያምና ኢየሱስ የመሳሰሉ ሰዎች፣ በቁራን ውስጥ ይገኛሉ:: ነገር ግን ታሪካቸውና ገድላቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ተዛብቶና ብዙ ጊዜም ፍጹም ተቃራኒ ሆኖ የሚገለጥበት ሁኔታ የበዛ ነው:: ምንም እንኳ ሙስሊሞች በመንግሥተ ሰማይና በገሃነመ እሳት ፍርድ የሚያምኑ ቢሆንም፣ በመሠረታዊ እምነት አንጻር ከክርስቲያኖች ጋር በምንም ዓይነት መንገድ ሊታረቅ የማይችል ልዩነት አላቸው::

በሌላም በኩል እስልምና ልክ እንደ ክርስትና በአንድ ሰው በኩል ወደ ምድር መምጣቱ ሁለቱን ሃይማኖቶች የሚያመሳስላቸው ሌላው ጉዳይ ነው:: ይሁን እንጂ መሐመድ ከመወለዳቸው በፊት ስለ እሳቸው አንድም ትንቢት አልተነገረም፤ በምድር በነበሩ ጊዜም ምንም ዓይነት ታምራት አላደረጉም፤ እንዲሁም ራሳቸውን ለሌሎች መስዋዕት ማድረግ አላስፈለጋቸውም፤ ደግሞም በየትኛውም ሁኔታ ለተከታዮቻቸው አምላክ እንደሆኑ አላስተማሩም:: ኢየሱስ ግን ከመወለዱ በፊት አያሌ ትንቢት ተነግሮለታል፤ በምድር የነበረው አገልግሎቱም በታምራት የታጀበ ነበር፤ ዕውር አብርቷል፣ ሽባ ተርትሯል፣ ለምጻም አንጽቷል፣ ሙታንን አስነሥቷል፣ ከሰዎች ውስጥ አጋንንቶችን አስወጥቷል፣ በውኃ ላይ ተራምዷል፣ ንፋስና ማዕበል ገስጾ አቀኗል . . .:: በመስቀል ተሰቅሎ ቢሞትም፣ ከሞት ተነሥቶ ብዙ ሰዎች እየተመለከቱት ወደ ሰማይ አርጓል:: ዳግም ተመልሶ እንደሚወስዳቸው ለሚያምኑበት ሁሉ ተስፋ ሰጥቷቸዋል:: ከዚህ በላይ በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርአን፣ በክርስትናና በእስልምና፣ በኢየሱስና በመሐመድ መኻል መሠረታዊ የሚባሉ ልዩነቶች አሉ::

እንዲያም ሆኖ በአንጻራዊነት ሲታይ በርካታ ሙስሊሞች፣ በስም ክርስቲያን፣ ተብለው ከሚጠሩ አያሌ ሰዎች ይልቅ ለሃይማኖታቸው

ቀናኢ ናቸው:: አብዛኛው ሙስሊም ስለታሪኩና ማንነቱ ማሰብ የሚፈልገውም እስልምናን ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ዘመን አስልቶ ነው፣ ማለት ይቻላል፤ በብዙ ስፍራዎችም እምነቱ ከአማኙ ማንነት ጋር ፍጹም ተዋህዶ የሚታይበት ሁኔታም አለ:: ይህ ማለት ለምሳሌ ለአንድ ግብጻዊ ከፈርኦኖች ድንቅ ሥራ ይልቅ የመሐመድ ሥራ ያስደንቀዋል፤ ለአንድ ኢራናዊም ከፋርሶች ገናናነት ይልቅ የእስልምና ኃያልነት ያኮራዋል፤ ለኢራቃዊው ደግሞ ከሜሶፖታምያ ሥልጣኔ ይልቅ እስልምና ለዓለም ያመጣላት አዲስ የሕይወት ሥርዓት ያስደስተዋል፤ እንደ ማለት ነው::

ቁርአን፣ እስልምናን የተቀበሉ ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ማድረግ የሚገባቸውን አምስት ወይም ስድስት ግዴታዎችን የደነገገ ሲሆን፣ እነሱም አምላክ አንድ እንደሆነና መልዕክተኛውም መሐመድ ብቻ መሆናቸውን ማመን፣ በቀን አምስት ጊዜ ፊትን ወደ መካ አቅጣጫ አዙሮ መስገድ፣ በሮመዳን ወቅት ቀኑን ሙሉ መጾም፣ ከገቢ የተወሰነውን ለተቸገረ መስጠት፣ በሕይወት ዘመን ቢያንስ አንድ ጊዜ ወደ መካ መሄድና ሁልጊዜም ለጅሐድ ዝግጁ መሆን የሚሉ ናቸው:: ሆኖም ጅሐድን በተመለከተ በራሳቸው በሙስሊሞቹም መኻልም ሆነ በእምነቱ ውስጥ በሌሉ ሰዎች ዘንድ አንድ አይነት ትርጉም አለ ማለት አይቻልም:: ምንም እንኳ «ጂሐድ» ጥሬ ቃሉ «የተቀደሰ ጦርነት» ማለት እንደሆነ በበርካታ አማኞች ዘንድ ቢታመንም፣ ከዚያ ያለፈ የጠለቀ ትርጉም አለው:: በዚሁ መሠረት «ጅሐድ» የማያቋርጥና ብርቱ ጥረት ማድረግ ማለት ሲሆን ይኼም ከእምነት አንጻር ሲታይ፣ እስልምናን ለመጠበቅና ለማስራጨት ሁለንተናዊ ትጋት ከማድረግ ጋር የተያያዘ ነው:: ሆኖም *«አንዳንዴ አስፈላጊ ሲሆን፣ ጥረቱና ትጋቱ ጦርነትንም ሆነ ሌላ ነገር ሊጨምር ይችላል»* የሚለው አሳብ በዛሬው ጊዜ የተለያየ አተረጓጎም ሲሰጥ ይታያል:: ከዚህ የተነሣ በእምነቱ ተከታዮች መኻል እንኳ ልዩነት አለ:: አንዳንድ የሙስሊም ሊቃውንትም ጂሐድ በምንም ዓይነት መልኩ ሽብር ፈጣሪነት ወይም የሌላውን እምነትና ነጻነት መጋፋት እንዳልሆነ አጥብቀው የሚሟገቱት ይኼን መሠረት አድርገው ነው::





ከሙስሊሞች አብላጫ ቁጥር ያላቸው ወግ አጥባቂዎቹ ሱኒዎች ሲሆኑ የአረብ አገራትን ጨምሮ፣ በብዙ የዓለም ክፍሎች የሚገኙ ናቸው:: በአንጻሩ ሻኢቶች በባሕሬን፣ በኢራን፣ በኢራቅና በሊባኖስ በዛ ብለው ይኖራሉ:: ሙስሊሞች *«መሐመድን፣ ቀጥሎ የተካቸው ማነው?»* ከሚለው ነገር በቀር፣ ያን ያህል የጎላ የእምነት ልዩነት የለባቸውም:: በእርግጥ ሻኢቶች *«ወደፊት በሚሆን አንድ ዘመን፣ አስራ ሁለተኛውና የመጨረሻው ኢማም ይመጣል፤ እርሱም ለአምላክ ያደረ ዓለም ይመሠርታል»* የሚለው ትምህርታቸው፣ ለሱኒዎቹ ብዙም አይዋጥላቸውም:: በአንጻሩ ሻኢቶቹ፣ ለዘመናት በሱኒዎች በደል እንደደረሰባቸው ስለሚያስቡ በመኻላቸው ልዩነት ይታያል:: ምንም እንኳ ጉዳዩ ትንሽ መስሎ ቢታይም፣ ለብዙ ዘመናት ደም ሲያፋስስ የኖረና ለወደፊትም የሚያሳቅቅ ተቃርኖ አፍኖ የያዘ ነገር ነው:: ለአብነት ያህል በቅርብ ዓመታት በኢራቅ የተከሰተውን የመንግሥት ክፍተት ተከትሎ፣ አንዱ በሌላው መስኪድ ሳይቀር ፈንጂ እየጣለ፣ በሺ የሚቆጠሩ የእምነቱ ተከታዮች በአምልኮ ላይ ሳሉ እንኳ የተቀጠፉበትን ተግባር መጥቀስ ይበቃል::

ሙስሊሞች በአንድ ዘመን ግስጋሴአቸው እስኪገታ ድረስ፣ አውሮፓ እምብርት ድረስ ዘልቀው፣ እምነቱን ከሥልጣኔ ጋር አስፋፍተዋል:: በዚህም ተግባራቸው አውሮፓ ካንቀላፋችበት እንድትነቃ በተወሰነ መልኩ አስተዋጽዖ አድርገዋል ተብሎ ይታሰባል:: በተለይም ከ7ኛው እስከ 13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩት ዓመታት ለእነሱ ወርቃማ ዘመናቸው ሆነው የሚቆጠሩ ነበሩ፤ በእነዚያ ጊዜአትም በዓለም ላይ ታላላቅ ተግባራትን ለመከወን ችለዋል:: ከዚያ በኋላ ግን የኦቶማን ቱርክ በአካባቢው መግነንና የአውሮፓውያኑ የመስቀል ጦረኞች ድንገተኛ ተግባር የዓለምንም ሆነ የእስልምናን ታሪክ እጅግ ለወጠው:: በተለይ ከ11ኛው እስከ 13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ ኢየሩሳሌምን ከሙስሊም አገዛዝና ተጽእኖ ነፃ ለማውጣት በማለም የተካሄደው «የመስቀል ጦርነት» በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መኻል መራራ ጥላቻ ጥሎ ከማለፉም በላይ፣ በዓለም ታሪክ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም:: ከዚያ ዘመን ታሪክ ውስጥ

ሐምሌ 15 1099 የመስቀል ጦረኞቹ ኢየሩሳሌም ደርሰው ያደረጉት ደግሞ እጅግ የሚያሳፍርና የሚዘገንን ነው:: «ክርስቲያኖቹ» በቀጥታ የሰለሞን ቤተ መቅደስ ተሠርቶበት በነበረበት ስፍራ ወዳለውና ለሙስሊሞቹ ሦስተኛ ቅዱስ ስፍራ ወደሆነው መስኪድ በመዝለቅ፣ ከወርቅና ከብር የተሠሩ ዕቃዎችን ዘረፉ:: ከዚያም በኢየሩሳሌምና በአካባቢው ያገኟቸውን ሙስሊምና አይሁዶችን ልዩነት ሳያደርጉ ያለርህራሔ አረዱ:: በወቅቱ የነበረውን ኹነት የታዘበ አንድ የታሪክ ጸሐፊ ሁኔታውን ሲገልጥ *«በከተማ ውስጥ በአሰቃቂ ሁኔታ የተቆራረጡ የሰው የአካል ብልቶች በየሚዳው ተጥለው ይታዩ ነበር»* ማለቱ፣ ክስተቱ ምን ያህል አሰቃቂ እንደነበር የሚገልጥ ነው::

ያም ሆኖ የመስቀል ጦረኞቹ ድላቸውን ዘላቂ ለማድረግ አቅም አልነበራቸውም:: ከሙስሊሞቹ ጋር ከሁለት መቶ ዓመታት ላላነሰ ጊዜ ያደረጉት ጦርነትም፣ አካባቢውን ከማወክና ደም ከማፍሰስ በቀር፣ ኢየሩሳሌምን ከእጃቸው ለመንጠቅ ስላላስቻላቸው ወደ ኋላ ሽንፈታቸውን አምነው መቀበልን መረጡ:: ሙስሊሞቹም ቢሆኑ በእነዚያ ዓመታት ኃይላቸው ከፉኛ ስለተዳከመ፣ ወደ አውሮፓ የሚያደርጉት ግስጋሴ በአጭሩ ተገታ:: ከዚያ በኋላ በአካባቢው የገነነው የኦቶማን ቱርክም ለአዲሱ ዓለም መወለድ ምክንያት መሆን ጀመረ:: ምንም እንኳ ቱርኮቹ ራሳቸው ሙስሊም ቢሆኑም አረብ ባለመሆናቸው የተነሣ፣ እስከዚያ ዘመን ድረስ እስልምናና የአረብ ብሔርተኝነት የነበራቸውን ቁርኝት በመጠኑ ሊያፋቱት ችለዋል:: ይኼም ጊዜ የእስልምና አመራር ለመጀመሪያ ጊዜ አረብ ባልሆነ አገርና ሕዝብ የተወሰደበት ዘመን ሆኖ በታሪክ ይታወሳል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የኦቶማን ቱርክ አገዛዝ ተጽዕኖ፣ ለአራት መቶ ዓመታት ያህል በአካባቢው የዘለቀ ሲሆን፣ የአረቡ ዓለም በተራው፣ አንድ ወቅት አውሮፓ እንዳቀላፋችው ዓይነት እንቅልፍ አንቀላፋ::

ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ የደረሰው ሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ግን የአረቡ ዓለምንም ሆነ መካከለኛው ምሥራቅን ከረጅም ጊዜ እንቅልፉ የሚቀሰቅስና እስልምናን እንደ ገና የሚያነቃቃ ሁለት ነገሮችን ይዞ ከተፍ አለ:: ከእነርሱም አንዱ፣ በአረብ ምድር በገፍ





የተገኘው ነዳጅ ዘይት ሲሆን፣ ሁለተኛው ነገር ደግሞ በፍልስጥኤም ምድር የእስራኤል መንግሥት እንደገና መመሥረት ናቸው::

ከላይ ያነሣናቸው አሳቦች እንደተጠበቁ ሆነው በአንጻራዊነት ሲታይ ከየትኛውም ዘመን ይልቅ እስልምና በአሁኑ ዘመን አንድነቱ ጥብቅ እየሆነ የሄደ ይመስላል:: ስለዚህም በኢራንና በሳውድ አረቢያ በሱኒና በሻኢት መኻል ያለው ልዩነት ያን ያህል ጎልቶ አይሰማም:: በሌላም በኩል ግን የእስልምና ተጽዕኖ ፈጣሪነት ዕለት ተዕለት እያየለ መሄዱ እየታየ ነው:: ምናልባት ይህ አንድነትና ተጽእኖ ፈጣሪነት ዓለምን ወደማይቀረው የጎግ ማጎግ ጦርነት ይመራት ይሆን? በእርግጥ ይኼ ወደፊት የሚታይ ነው የሚሆነው::

## ነዳጅ ዘይትና መካከለኛው ምሥራቅ[22]

በወርሀ ሰኔ 1932 ከካሊፎርኒያ የመጣ አንድ ቡድን በባሕሬን በረሀማ ስፍራ የውኃ ቁፋሮ ለማድረግ ለዘጠኝ ወራት በዚያ ቆይቶ ነበር:: ነገር ግን ከበረሀው ሙቀትና ዝንብ በቀር አንዳች የሚፈነጥቅ ነገር ባለመገኘቱ ቆፋሪዎቹ በየዕለቱ እየታከቱ ሄዱ:: በወቅቱ ሳውዲ አረቢያን ጨምሮ ስድስቱ የፋርስ ባሕረ ሰላጤ ትንንሽ አገሮች[23] እጅግ ኋላ ቀርና ሥልጣኔ ያልገባቸው በመሆናቸው የአሜሪካውያኑን ቆይታ አሰልቺ አድርጎት ኖሯል:: የዓረቡ ዓለምም የኦቶማን ቱርክ መግነን ተከትሎ ከተጫነው ረጅም እንቅልፍ ገና አለመንቃቱ ይታይ ነበር:: እንዲያውም አንዳንድ መንግሥታት ከውጪ የሚመጣ ማናቸውንም ዓይነት ባህል ላለመቀበል ለዓመታት በራቸውን ዘግተው ከመቆየታቸው የተነሣ፣ የቀረው ዓለም እነርሱን፣ እነርሱም ሌላውን ዓለም ሳለማወቅ የተስማሙ መስሎ ይታይ ነበር::

እነዚያ ከካሊፎርኒያ የመጡ ውኃ ፈላጊዎች የመቆፈሪያ ማሺናቸው የመጨረሻ አካል ሁለት ሺ ጫማ ወደ መሬት ዘልቆ ገብቶ፣ ዐለቱን አልፎ እልም ሲል፣ የዘጠኝ ወራት ልፋታቸው ውጤት ያገኘ መስሎአቸው እጅግ ደስ ብሏቸው ነበር:: ሆኖም ወጥቶ የታየው ነገር የናፈቁት ውኃ ባለመሆኑ ብዙዎቹ ቅር ተሰኙ:: በእርግጥ በዚያን ጊዜ ለእነርሱ በጣም የሚያስፈልጋቸው አንድ ነገር፣ ውኃና ውኃ ብቻ ነበር:: በመሆኑም በዚያ «ተስፋ ቢስ» በሚመስል ቀን በውኃ ፋንታ የተገኘው ጥቁር ጭቃ፣ ከአካባቢው አልፎ የዓለምን ታሪክና የኃይል ሚዛን የሚያዛባ ታላቅ ሀብት ይሆናል ብሎ ማንም የጠረጠረ አልነበረም:: ሰኔ 1932 ግን በአረቡ ዓለም ለመጀመሪያ ጊዜ የነዳጅ ዘይት የተገኘበት ዓመት ሆኖ በታሪክ ሲያወስ ይኖራል::

[22] አብዛኛዎቹ አሳቦችን የተወሰዱት፣ The Arabs: Journeys Beyond the mirage: David Lamb 1987 ነው
[23] ሳውዲ አረቢያ፣ ኳታር፣ ኩዌት፣ ኦማን፣ የተባበሩት አረብ ኢሚሬትስና ባሕሬን ናቸው





አረቦቹ ነዳጅ ዘይት ያገኙት ውኃ ፈልገው ሲቆፍሩ መሆኑ እጅግ የሚደንቅ ነው:: እውነት ለመናገር ከስልሳና ከሰባ ዓመታት በፊት የነበረው የብዙ የዓረብ አገራት ኑሮ በዛሬው ጊዜ ከሠሐራ በታች ካሉ ድኻ የአፍሪካ አገራት ኑሮ ጋር የሚመጣጠን ነበር፣ ቢባል አልተጋነነም:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከአረቡ ዓለም ሥልጡን እንደሆኑ የሚቆጠሩት ሕዝቦች፣ ግብጻውያንና ሊባኖሳውያን የነበሩ ሲሆን፣ ከእነርሱ ቀጥሎ ሦርያውያን፣ ኢራቃውያንና የሰሜን አፍሪካ አገራት ሕዝቦች ይጠቀሳሉ:: በፋርስ ባህረ ሰላጤ በሚገኙት አገራት የሚኖሩ ሕዝቦች ግን ከሁሉም ይልቅ «ኋላ ቀር ናቸው» ተብሎ ይታሰብ ነበር:: የዛሬን አያድርገውና፣ አያሌ የአረብ ነጋዴዎች የግመሎቻቸውንና የፍየሎቻቸውን ጭራ የሚከተሉ ከመሆናቸውም በላይ፣ ለዓለም ፖለቲካና ሥልጣኔ ያን ያህል ግድ የሌላቸው ነበሩ:: በአካባቢው በነበሩ አገሮች ሁሉ፣ የመሠረተ ልማት አውታር «ጨርሶ የለም» በሚባልበት ደረጃ ላይ ነው የነበረው:: የየአገራቱ ነገሥታትም በጭቃ በተሠሩ ቤተ መንግሥቶቻቸው ውስጥ ነበር የሚኖሩት::

ዛሬ ግን ያ ታሪክ ፍጹም ተለውጦ አረቦች የዓለምን ፖለቲካና ኢኮኖሚ መዘውር በእጃቸው የያዙ መስሎ እንዲሰማቸው ሆነዋል:: በዚህ ምክንያት በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚገኝ ፖለቲከኛ፣ ወደደም ጠላም ስለመካከለኛው ምሥራቅ ውሎና አዳር በትኩረት እንዲያስብ ተገዷል። ምን ይኼ ብቻ! በዛሬው ጊዜ ከቤት እመቤት እስከ ታላቅ ባለሀብት ድረስ ያለ የማንኛውም ሰው ኑሮ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የዚያ አካባቢ ጥገኛ ሆኗል:

አንድ ቀን ከአንድ ሰው ጋር ስለዚህ የሀብት መትረፍረፍ እንሥተን ስንነጋገር፣ ጉዳዩ እግዚአብሔር ለኢስማኤል ከሰጠው ጽኑ ተስፋና በረከት ጋር የተያያዘ መሆኑን እንደሚያምን ነገረኝ:: እኔም «ማን ያውቃል? ይሆን ይሆናል» ከማለት በቀር ምንም አልመለስኩለትም:: ወዲያው ግን በአንድ ወቅት የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ጎልዳሜይር የተናገሩትን አስታወስኩ፤ ሴትየዋ እግዚአብሔር፣ ይኼን የተትረፈረፈ ሀብት የሞላበትን ምድር አልፎ ሕዝቡን ማስፈሩ ቅር እንዳሰኛቸው ተናግረው ነበር፣ ይባላል፤ ደግሞም አንዳንድ አክራሪ

አይሁዳውያን፣ በቀድሞ ዘመን ስለአሴር የተነገረውን ጠቅሰው፣ ከሺ ዓመታት በፊት የአሴር ነገድ በሰፈረበት ቦታ ቁፋሮ ቢደረግ ዘይት እንደሚገኝ ያልማሉ፣ ይባላል::[24]

በመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ዘይት መገኘቱ ዓለም ለስፍራው ያለው ትኩረት ወዲያው ከፍ እንዲል አድርጎታል:: በመሠረቱ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ አገራት በብርቱ ነዳጅ እየፈለጉ የነበረ ሲሆን፣ በአውሮፓ፣ በአሜሪካና በጃፓን በነዳጅ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች በገፍ መመረት ጀምረው ነበር፤ እንግሊዝን የመሳሰሉ አገሮችም የጦር መርከቦቻቸው ከድንጋይ ከሰል ይልቅ፣ በነዳጅ ቢንቀሳቀሱ የበለጠ ፈጣንና ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ ተረዱ፤ በመሆኑም በእነዚያ «ባልሰለጠኑ» ሰዎች አገር የተገኘው ነዳጅ ለምዕራባውያኑ ከጓሮአቸው እንዳገኙት ያህል አስደሳች ሆነላቸው:: ስለዚህም በገፍ እያወጡ ወደ አገራቸው መላክ ጀመሩ:: በመሆኑም በአሜሪካ ገበያ፣ ለዓመታት አንድ በርሜል ድፍድፍ ነዳጅ በአምሳ ሳንቲም ብቻ ይቸበቸብ የነበረ ሲሆን፣ ኩባንያዎቹ ለነዳጁ ባለቤት አገሮች የሚከፍሉት ገንዘብ ግን እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም:: ለተወሰኑ ዓመታትም፣ ነዳጁን አውጥተው ለመውሰድ አካባቢውን ለሚያስተዳድሩ ሡልጣኖች ጥቂት ጉርሻ መስጠት ብቻ ነበር የሚጠበቅባቸው::

አረቦቹም ቢሆኑ ድንገት የፈለቀላቸውን የተትረፈረፈ ሀብት ከባህልና ከሃይማኖታቸው ጋር አጣጥመው እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ቶሎ ባለማወቃቸው፣ ለረጅም ጊዜ ተቸግረው ታይተዋል:: በአንድ በኩል ገንዘብ የሚያመጣው ሥልጣኔ ለዘመናት የጠበቁትን ባህልና ሃይማኖት እንዳያስጥላቸው ሲፈሩ፣ በሌላ በኩል ከእስራኤል አንጻር የገጠማቸውን ብርቱ ፈተና ለመቋቋም ነዳጁ ብቸኛ አቅማቸው እንደ ሆነ ተረዱ:: ይኼም ቀላል የማይባል አጣብቂኝ ውስጥ ከተታቸው:: ግራ መጋባቱ ጠፉፍ ሲልላቸውም፣ አብዛኛዎቹ አገራት ኩባንያዎቹን ከምዕራባውያን እጅ እየቀሙ ወደ ራሳቸው ይዞታ ማዛወር ጀመሩ:: ቀጥሎም ብዙ የአረብ አገራት አባል የሆኑበትን «የነዳጅ አውጪና ላኪ

[24] ዘዳ33:24:: አሴር ከሴሎች ልጆች ይልቅ የተባረከ ነው፤ ... እግሩንም በዘይት ውስጥ ያጥልቅ





አገራት ኅብረት» ማለትም «ኦፔክን» በይፋ መሠረቱ::[25] በወቅቱ ከአስራ ሦስቱ ከኦፔክ አባል መንግሥታት ውስጥ ሰባቱ አረቦች ሲሆኑ፣ ሦስቱ ደግሞ ሙሉ ለሙሉና በከፊል የሙስሊም አገራት ነበሩ::[26] ከዚያም አረቦቹ በኦፔክ በኩል በነዳጅ ምርትና ገበያ ላይ ውሳኔ ሰጪ ለመሆንም ሞከሩ:: ለዚህም በተከታታይ የተደረገውን የአረብ እስራኤል ጦርነት ተከትሎ በ1962 አቅማቸውን የፈተሹበት ተግባር ይጠቀሳል፤ ሆኖም ማዕቀቡ ከሸማቾቹ ይልቅ፣ ራሳቸው ሻጮቹን በጽኑ ስለጎዳቸው የመጀመሪያው ጥረታቸው ያሰቡትን ያህል ውጤት ሳያስገኝላቸው ቀረ::

ሆኖም ተስፋ አልቆረጡም፤ ስለዚህ በ1973 አቅርቦቱን በመቀነስ፣ ዋጋውን በአራት እጥፍ አንረው እንደገና ብቅ ሲሉ፣ ኃይላቸው ምን ላይ እንደ ደረሰ ዓለም በሚገባ አወቀ:: ቢሆንም በወቅቱ የአረቦቹ ዋነኛ ስሌት የነበረው አሳብ ተሳክቷል ማለት አይቻልም:: በጊዜው እነርሱ ያሰቡት *«ማዕቀቡ በእጅጉ የሚጎዳው እያንዳንዱ የምዕራቡ ዓለም ዜጋ፣ መንግሥቱ ለእስራኤል የሚያደርገው ድጋፍ፣ በራሱ ላይ ችግር እንዳመጣበት ሲያውቅ፣ እስራኤልን ከመርዳት እንዲታቀብ ያስጨንቀዋል»* የሚል የነበረ ቢሆንም፣ ከምዕራባውያን ሕዝቦች ያገኙት ምላሽ ግን ከጠበቁት ተቃራኒ ነበር የሆነው:: እናም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አብዛኛው የምዕራቡ ዓለም ሕዝብ ለአረቦች ያለው ጥላቻ እጅግ ናረ፤ እንደ ጨካኝና ጠረኛም ስለቆጠራቸው በጠላትነት ያያቸው ጀመር:: ያም ሆኖ አረቦቹ በዓለም ላይ ያላቸው አቅምና ጉልበት ምን ያህል እንደሆነ ፈትነው ያረጋገጡበት ወቅት ቢኖር 1973 ነበር፣ ቢባል ማጋነን አይሆንም:: በዚያ ላይ እስከ 1979 ድረስ ባሉት ዓመታት፣ ነዳጅ ዘይት ባልተጠበቀ ፍጥነት ማሻቀቡን ቀጥሎ፣ ዋጋው በበርሜል ከ3 ወደ 39 ዶላር ተወረወረ::

[25] OPEC: Organization of Petroleum Exporters Country.
[26] ሳውዲ አረቢያ፣ ኢራቅ፣ የተባበሩት አረብ ኢሚሬቶች፣ ኩዌት፣ ሊቢያ፣ አልጀሪያ፣ ኳታር፣ የአረብ አገራት ሲሆኑ፣ ኢራንና ኢንዶኔዥያ፣ ሙሉ ለሙሉ ናይጄሪያ፣ ከፊል ሙስሊም አገራት ናቸው:: ከእነዚህ መኻል ሙስሊምና አረብ ያልሆኑት፣ ኢኳዶር፣ ቬነዙዌላና ጋቦን ብቻ ናቸው::

በአንጻሩ በእነዚያ ዓመታት በነዳጅ አምራች አገራት ውስጥ ያለው የሕዝቡ ኑሮ በሚያስደንቅ ሁኔታ ተለወጠ፤ ያልጠበቁትን ገንዘብ ያገኙት እነዚያ «ድኻና ያልሠለጠኑ» ሕዝቦች ስንፍናን ጨምሮ በሽቀጥ ገበያ ያገኙትን ሁሉንም ነገር ገዙ። የሚገርመው ግን በነዳጅ ዘይት ሀብታቸው የሚታወቁት ሰባቱ የፋርስ ባሕረ ሰላጤው አገሮች በተከታታይ በተደረጉ የእስራኤልና የአረቦች ጦርነት በቀጥታ እጃቸውን የማስገባት ፍላጎት አለማሳየታቸው ነው። ከእነዚህ አገራት ውጪ ያለውና ቁጥሩ እጅግ የሚበዛው የአረብ ማኅበረሰብ ግን ነዳጁን ለውዝግቡ ዋነኛ ጉልበት አድርጎ ለመጠቀም ጓጉቶ ነበር። ይሁን እንጂ በተለይ አክራሪ የአረብ ብሔርተኞች ያሰቡትን ያህል ስኬት ሊያገኙ አልቻሉም። ለምሳሌ ትልቋ የነዳጅ አምራች አገር የሆነችው ሳውዲ አረቢያ፣ ከምዕራባውያን ጋር ያላትን ግንኙነት በተለየ ብልሀት ይዛ ጽኑ መሠረት ላይ እንዲቆም ከማድረጓም በላይ፣ በቤተሰብ የዘር ሀረግ የተሳሰረው ንጉሣዊው የሥልጣን አወቃቀር ይዞታም ጥብቅ ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን የተከተለ በመሆኑ፣ በግራም በቀኝም ያሉትን ለማቻቻልና ተረጋግታ ለመጓዝ አስችሏታል። በሌላ በኩል አካባቢውን የዓለም ሀብት እንደሆነ የሚቆጥሩ ሌሎች አገሮች፣ ይኼ ሀብት በየትኛውም አምባገነን መሪ ተጽዕኖ ስር እንዳይወድቅ በብርቱ ተከላክለዋል። ለዚህም ነው በ1991 ኢራቅ ኩዌትን በወረረች ጊዜ መላው ዓለም ከኢራቅ ተቃራኒ ሆኖ የተሰለፈው።

በአሁኑ ጊዜ ግን ከአረቦቹ በተጨማሪ አንዳንድ ነዳጅ አምራች የሆኑ የሙስሊም አገራት፣ በአረብ እስራኤል ውዝግብ ጉዳይ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆናቸው እየታየ ነው። በተለይም ከ1979 ጀምሮ ኢራን በዋናነት የምትጠቀስ አገር ሆናለች፤ በዚያው ዓመት በስደት ከነበሩበት ፈረንሳይ የተመለሱት «አያቶላ ሩሆላህ ኾሚኒ» ሥልጣን ላይ ከወጡ ጊዜ ጀምሮ ኢራን በአክራሪ ሻኢቶች እጅ ወድቃለች። በ1980፣ ሳዳም ሁሴን «ጠብ ያለሽ በዳቦ» ብለው ኢራንን ወረሩ። ምዕራባውያንን ጨምሮ፣ በአብዛኛው ሱኒ የሆነው የዓረቡ ዓለምም አካባቢው በኢራን ዓይነት አብዮት እንዳይጥለቀለቅ ስጋት ስላደረበት ያልተቆጠበ ድጋፉን ለሳዳም ሰጠ። በተለይ አረቦቹ ከእስራኤል እንኳ





ይልቅ፣ ኢራን ዋነኛ ስጋት ሆና ስለታየቻቸው ለኢራቅ ሁለንተናዊ ድጋፍ ከማድረግ አልተቆጠቡም ነበር። ጦርነቱ ግን በሁለቱም በኩል የብዙ ንጹሐንን ሕይወት ቀጥፎ፣ ኢኮኖሚያቸውን ከማንኮታኮቱ በቀር፣ ይህ ነው የሚባል ተጨባጭ ውጤት ሳይገኝበት ከስምንት ዓመታት በኋላ ተጠናቀቀ። ሆኖም ጦርነቱ፣ ለነዳጅ ዘይት ዋጋ መናር ያደረገው አስተዋጽኦ ቀላል የሚባል አይደለም።

ከእነዚያ ዓመታት ጀምሮ የነዳጅ ዘይት ዋጋ አንዴ ከፍ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ዝቅ እያለ ሲዋዥቅ ያለንበት ዘመን ላይ ደርሷል፤ በተለይ በ2008 ማንም ባልገመተው ጊዜ ዋጋው፣ በበርሜል 147 ዶላር የመድረሱ ምስጢር ግራ የሚያጋባ ሆኖ ነበር። በጊዜው በዓለም የኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት ግስጋሴው ቶሎ ባይገታ ኖሮ ማቆሚያ ያለው አይመስልም ነበር። በቅርብ ጊዜ ደግሞ በተለይ በሰሜን አፍሪካ በተከሰተው ፖለቲካዊ አለመረጋጋት የተነሣ እንደገና ዋጋው እያሻቀበ ነው።

ምንም እንኳ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከዓለም የነዳጅ ዘይት ምርት ውስጥ ከሦስት እጅ አንዱን የምትጠቀመው አሜሪካ ብትሆንም፣ አውሮፓም በበኩሏ ከፍተኛ የነዳጅ ዘይት ፍላጎት እንዳላት ታይቷል፤ ይሁን እንጂ ኢኮኖሚያቸው በታላቅ ፍጥነት እያደገ የሚገኘው የሩቅ ምሥራቅ አገሮች፣ ከሕዝብ ብዛታቸው ጋር ተደምሮ ፍላጎታቸው ሊጠረቃ እንደማይችል ገና ከአሁኑ እየታየ ነው። በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ይኖራል ከሚባለው ስድስት ቢሊዮን ሕዝብ የቻይናና የሕንድ ብቻውን 2.5 ቢሊዮን ያህል እንደሚሆን እያሰብን 300 ሚሊዮን ሕዝብ ብቻ እንዳላት ከሚነገረው አሜሪካ ጋር ያላቸውን ልዩነት ብናነጻጽረው፣ ጉዳዩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደ ሆነ ፍንትው ብሎ ይታየናል። የቻይናና የሕንድ የነዳጅ ፍላጎት የአሜሪካንን ያህል እንኳ ቢደርስ፣ ዓለም ነዳጁን ከየት ታመጣው ይሆን? የሚለውን ጥያቄ መመለስ በራሱ ቀላል አይደለም። በሕንድና በቻይና ያሉ ሕዝቦች፣ የነፍስ ወከፍ የምጣኔ ሀብት አቅም በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ በመሆኑ፣ የኃይል ፍላጎታቸው በየቀኑ እየናረ ነው። ሌላው ቀርቶ ይህ መጽሐፍ በተጻፈባቸው ሁለት ዓመታት ውስጥ የቻይና

ኢኮኖሚ ከአሜሪካ ቀጥሎ የዓለማችን ግዙፍ ኢኮኖሚ ሆኗል፤ እንደሚባለው ከሆነ ደግሞ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ቻይና የመሪነቱን ስፍራ ትቆጣጠራለች።

ሌላው አስገራሚ ጉዳይ አረቦቹ ይሄን ሁሉ ነዳጅ እያወጡ ለራሳቸው ፍጆታ የሚጠቀሙት መጠን ግን እጅግ በጣም ጥቂት ብቻ መሆኑ ነው። ከእነርሱ በተቃራኒ ያለችው አውሮፓ ግን ከሰሜኑ ክፍል በስተቀር ምንም ዓይነት የነዳጅ ሀብት የሌላት ሲሆን፣ ፍጆታዋ የትየለሌ ነው። ምንም እንኳ ሩሲያ ከዋነኛ ነዳጅ አምራች አገሮች አንዷ ሆና ብትጠቀስም ከድሮ ጀምሮ ከምዕራባውያን ጋር ያላት ወዳጅነት የሚያወላዳ ባለመሆኑ፣ አውሮፓውያን የሚተማመኑባት አይደለችም። አሜሪካም ብትሆን በከርሰ ምድሯ ከማንም በላይ ነዳጅ እንዳላት ቢነገርም አውጥታ ለመጠቀም የፈቀደችው የተወሰነ መጠን ብቻ ነው ይባላል፤ ይኼም ከሚያስፈልጋት አንጻር ሲሰላ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። በእርግጥ አሁን፣ አሁን በአንዳንድ የአፍሪካ አገሮች በተወሰነ መጠን ነዳጅ መኖሩ ታይቷል፤ ነገር ግን እነዚህ አገሮች ሽብርና ውዝግብ የማያጣቸው በመሆናቸው የአቅርቦቱን አስተማማኝነት ጥያቄ ውስጥ የሚጥል ነው።

ነገሩ ይኼን ያህል አሳሳቢ ቢሆንም፣ ዓለማችን እስከ ዛሬ ድረስ ከነዳጅ ዘይት ተደጋፊነት ሊያወጣት የሚችል አማራጭ የኃይል አቅርቦት በበቂ ሁኔታ አለማዘጋጀቷ የሚገርም ነው። በመሆኑም ወደድንም ጠላንም በሚመጡት ጊዜአት በዓለም ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና የሃይማኖት ሥርዓት ውስጥ ነዳጅ ዘይት የሚጫወተው ሚና እያደገ የሚሄድ መሆኑ አይቀርም። ይህ ማለት ደግሞ መካከለኛው ምሥራቅ የዓለም ሁሉ ዓይንና ጆሮ ማረፊያ እንደሆነ ይቀያል ማለት ነው።





ምዕራፍ ፳፬

# ተስፋይቱ ምድር

መኖሪያ ቤቴም ሆነ ቢሮዬ አዲስ አበባ ካለው የእስራኤል ኤምባሲ ብዙም በማይርቅ ስፍራ ስለሆነ ኤምባሲውን በየቀኑ የማየት ዕድል አለኝ። ምንም እንኳ የተለየ ነገር ባላይም በዚያች ትንሽ አገር ኤምባሲ በኩል ባለፍኩ ቁጥር ግቢውን ትኩር ብዬ አየዋለሁ።

የእስራኤል ኤምባሲ የተሠራው ከፍ ካለ ኮረብታ ላይ ስለሆነና ተፈጥሮ ራሱ የሠራለት መከላከያ ስላለው ነው መሰል፣ የሽብርተኞች ስጋት እንዳለባቸው አገራት ኤምባሲዎች የኮንክሪት ግጭት መከላከያ ግድብ አልተደረገለትም፤ ከቅጥር ግቢ ውጭ ሆነው የሚጠብቁ የፌደራሉ ፖሊሶችና የኤምባሲው ጥበቃዎች ግን በመንገዱ ግራና ቀኝ የሚያልፍ የሚያገድመውን ሰውና ተሽከርካሪ ዘወትር በንቃት ይመለከታሉ። የግቢው አጥር ከሚነሣበት እስከሚያበቃበት ድረስ መኪና ማቆምም ሆነ ከአጥሩ አንጻር ባለው የመንገድ ጠርዝ በእግር መጓዝ ክልክል ነው። በግንቡ ላይ ፎቶግራፍ ማንሣትና ቪድዮ መቅረጽ እንደማይቻል የሚያስጠነቅቅ ማስታወቂያ በተለያየ መጠን ተለጥፎ ይታያል። በዋናው መግቢያ በር ከሙሴ ዘመን ጀምሮ የእስራኤላውያን ዓርማ ሆኖ እያገለገለ ያለው የመቅረዝ ምስል በግልጥ ይታያል። ግቢው ግን በዛፎች የተከበበ ስለሆነ በውስጥ ምን እንዳለ ገልጦ ለመናገር አስቸጋሪ ነው። ባለ ዳዊት ኮከቧ ነጭና ሰማያዊ ቀለማት ያሏት የትንሿ አገር ሰንደቅ ዓላማም በዛፎቹ መኻል ዘወትር በኩራት ስትውለበለብ ትታያለች።

በበኩሌ፣ ከየትኛውም አገር ይልቅ ልጎበኛት የምናፍቃት አገር፣ እስራኤል ናት። እስከዚያው ግን፣ ወደ እርሷ ደርሰው ከተመለሱ ወይም እዚያው ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ስለዚያች አስገራሚ አገር በማውጋት እዘልቃለሁ። ካለሁበት ወደ ኋላ ተመልሼ ሳስብ ከልጅነቴ ጀምሮ ስለእስራኤል ብዙ እንዳነበብኩና እንደሰማሁ አስታውሳለሁ።